የእግዚአብሔር ዕቅድ ለዓለም

በ ቶም ወልድኬር

ምዕራፍ ሁለት

ሶስት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርቶች ለታዳጊ ልጆች

በአጭሩ የማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከ 7-12 በተቀመጡት ጥያቄዎች ላይ በመመስረት

ምዕራፍ ሁለት፡ የእግዚአብሔር ዕቅድ ለዓለም

የማውጫ ሰንጠረዥ

ለመምሕራን የተዘጋጀ መቅድም……..

ምዕራፍ 1፡ እግዚአብሔር ኹሉን ዓቅዶአል…….

ምዕራፍ 2፡ እግዚአብሔር ኹሉን ፈጥሮአል……

ምዕራፍ 3፡ እግዚአብሔር ኹሉን ይቆጣጠራል……

አባሪ፡ የታዳጊዎቹ መልመጃ…….... ……

መቅድም ለመምህራን

እግዚአብሔር እጅግ ለተዋበ ጎላፊነት ታማኝ አድርጎ ቆጥሮሀል (ይሄም፣ ለእግዚአብሔር ክብር እና አገልግሎት ይሆን ዘንድ የማይጠፉ ነፍሳትን ማሰልጠን)። ምንአልባትም ለሀላፊነትህ ያለህ ታማኝ መሰጠት በአንተ እጅ ላሉት ታዳጊዎች የዘላለም ድነትና በምድር ላለባቸው ውጊያ ወሳኝ መሰረት ይሆናል። በጥንቃቄ የተሞላው የእምነት ትዕዛዝህ ታዳጊዎቹን እያጎለበተ ፣ የሕያውና እውነተኛ አምላክን ቤተክርስቲያን ለረጅም ዘመናት እንዲያገለግሉ ሊያስታጥቃቸው ይችላል።

ወደዚህ ጠቃሚ ተግባር ፣ የእምነት ስራ እና ስለፍቅር የሚሆን ድካም እንደሆነ እያሰብክ ቅረብ። ለእያንዳንዱ ምዕራፍ ስትዘጋጅ ፣ በትጋትና በብዙ ጸሎት ይሁን። እንዲሁ ከመሸምደድና መልሶቹን ከመያዝ ይልቅ ፣ የማቴሪያሎቹን ጠቃሚነት ተረድተው ወደልባቸው እንዲያስገቡት ተፅዕኖ አድርግባቸው። የእምነት አንቀጽን ማጥናትና መጽሐፍ ቅዱስን በማወቅ ማደግ ለአሁንም ሆነ ለሕይወት ዘመናቸው ኹሉ እንዴት እንደሚጠብቃቸው ፣ እንደሚያጠነክራቸውና እንደሚያበረታታቸው ትኩረት እየሰጠ አስተምራቸው።

በእምነትና በጸሎት ፣ ከድካምህ ብዙ ፍሬ አግኝ። ታዳጊዎችህ አድገው “የተባረክህ” ይበሉህ (ምሳ 31፡28). በእርግጥም ለመንግስቱ ለሚሆንና ትልቅ ዋጋ ላለው ትጋትህ እግዚአብሔር በብዙ ይባርክህ።

የዌስትሚኒስተር አጭሩ የእምነት መግለጫ

በ1643፣ የእንግሊዙ ፓርላማ አንድ ወሳኝ ነገር አደረገ።ፓርላማው፣ 121 ፓስተሮችና 30 ሹመት የሌላቸውን ሰዎች የጠራ ነው ፤ ከእነሱም መካከል በአለም ዙሪያ የሚታወቁ ታላላቅ የስነመለኮት ሰዎች ነበሩበት። የተገናኙትም ፣የእምነት አንቀጽ ሊቀርጹ እና ለቤተክርስቲያን የአገዛዝ ስርዓት ሊፈጥሩ ነበረ ፤ በኋላ ላይ ጥረቱ የአምልኮ መሪነትን ፣ የእምነት አዋጅ እና ሁለት የእምነት መግለጫዎችን መለደ ፤ ረዥሙ የእምነት መግለጫ ለጥልቅ ጥናት ሲሆን አጭሩ ደግሞ ፈያጅ የሆኑትን ጉዳዮች ለማስተማር ያገለግላል። ለረዥም አመታት የተደረገው ተደጋጋሚው ስብሰባቸው የዌስትሚኒስትር ጉባዔ በመባል ታወቀ።

በእግዚአብሔር መግቦት ፣ ዛሬ ላይ የእምነት መግለጫው ፣ ወሳኝ የኾኑትን የክርስትና አስተምሕሮዎች የያዘ ጠቃሚ እጣሬ ኾኖ ያገለግላል። በሚያሳዝን ኹኔታ ግን፣ የዘመኗ ቤተክርስቲያን በእምነት መግለጫው ውስጥ እንደተካተቱት ዓይነት ርቱዕ ክርስቲያናዊ አስተምሕሮዎች ብዙ ቦታ የላትም። በተለይ ታዳጊዎች ለሕይወትና ለተግባር ጠቃሚ የሆኑ ጠንካራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምሕርቶችን ካላገኙ በጣም ይቸገራሉ። ቤተክርስቲያናትን ፣ የክርስቲያን ትምሕርት ቤቶችን እና ወላጆችን ለማበረታታትና መሰረታቸውን ለማጠንከር ፣ ዓለም አቀፍ የልጆች አገልግሎት (CMI) የአጭሩን የእምነት መግለጫ የሚደግፉ ማቴሪያሎችን እያዘጋጀ ያከፋፍላል።

<u>የተከታታይ ትምሕርቶች አወቃቀር</u>

የታዳጊዎቹ ተከታታይ ትምሕርት ዘጠኝ ክፍሎች (መጻሕፍት) ይዟል።

ክፍል 1 የእግዚአግሔር መገለጥ ለሰው ልጆች

ክፍል 2 የእግዚአብሔር ዕቅድ ለዓለም

ክፍል 3 የሰው ልጆች ኀጢያት እና ውድቀት

ክፍል 4 የእግዚአብሔር መግቦት ለኀጢያተኞች

ክፍል 5 የእግዚአብሔር አስደናቂ ጸጋ

ክፍል 6 ለእግዚአብሔር ሊኖርህ የሚገባው ግዴታ

ክፍል 7 የአንተ ግዴታ ለሌሎች

ክፍል 8 የእግዚአብሔር የጸጋው መንገድ

ክፍል 9 የጌታ ጸሎት

እያንዳንዱ ክፍል ከ ሶስት እስከ ስምንት ምዕራፎችን ይይዛል። እያንዳነዱ ምዕራፍ በሶስት የተከፈለ ሲኾን ፣ የእምነት መግለቸጫ ፣ የጥቅስ ጥናትና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርቶችን የያዘ ነው። የመጨረሻዎቹ ኹለቱ ክፍላት (የጥቅስ ጥናት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርቶች) የእምነት መግለጫዎው ውስጥ ያሉትን ማቴሪያሎች ደግመው የሚያስታውሱና የሚደግፉ ናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስን ትምሕርቶችና የጥቅስ ሽምደዳን በምታስተምሩበት ወቅት ፣ ታዳጊዎቹ የሚገጥማቸውን የሕይወት ተግዳሮቶችና የተለያዩ ጉዳዮችን መጋፈጥ እንዲችሉ ፣ የእምነት መግለጫው ፋይዳ እና መጽሐፍ ቅዱስ ላይ አትኩሮት አድርጉ።

ትምሕርቱን በተመለከተ የሚቀርቡ ሐሳቦች እና ማሳሰቢያዎች

ከማስተማርዎ አስቀድሞ ፣ አጠቃላይ ምዕራፉን በጥንቃቄ ያጥኑት ። የትምሕርቱን ዓላማ እና የእምነት መግለጫውን አስቀድሞ ማወቅ ፣ ስለ ጽሑፉ ግልጽ የሆነ አጠቃላይ መረዳትን ይሰጣል። ትምሕርቶን በእውነተኛ የክርስትና አስተምሕሮ ላይ ይመስርቱ። በተጨማሪም ፣ ሌሎቹ ምዕራፎችና ክፍላት በሚዳስሱት ርዕሰ ጉዳዮች ላለመወሰድ ፣ አትኩሮትን በመጠበቅ ጥንቃቄ አድርጉ።

የትምሕርቱ ዓላማ በእያንዳንዱ ምዕራፍ መግቢያ ላይ ይገኛል። ለትምሕርቱ ዓላማ ትኩረት ባለመስጠት ፣ በፍጥነት ወደ ይዘቱ መዝለቅ ወይም ለራስ አረዳድና የጊዜ አመዳደብ እጅግ ታማኝ የመሆንን ፈተና መቋቋም ያስፈልጋል።ታዳጊዎቹ የተጠቀሰውን የትምሕርቱን ዓላማ በሚገባ ሳያሳኩ ፣ በፍጥነት ማቴሪያሉን ከመጨረስ ይልቅ ፣ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ጊዜያትን በአንድ ምዕራፍ ላይ መቆየት የተሻለ ነው። በአንዳንድ የእምነት መግለጫው ጥያቄና መልስ ውስጥ ፣ ምንአልባት ታዳጊዎቹ መረዳትን የሚያደነቃቀፍ ፣ የቃላትና የአረፍተ ነገር አወቃቀር ሊገጥማቸው ይችላል። ከባባድ ቃላትን በመፈለግና ፣ የእምነት መግለጫውን እንደገና በመፃፍ ግንዛቤአቸውን ማሳደግ ይችላሉ። ምንም እንኳን የእምነት መግለጫውን በቃል መሸምደድ ትልቅ ጥቅም ቢኖረውም ፣ ትርጉሙን ግልፅና ቀጥተኛ በኾነ ቋንቋ ማብራራት የበለጠ ይጠቅማል። በእርግጥ ፣ በቂ ግንዛቤ ያልተያዘባቸውን ቃላት እንዲሁ መሸምደድ ፣ የመንፈሳዊ ዐድገት አቅምን ይወስናል። ያለሽምደዳ መረዳት ፣ ያለ መረዳት ከመሸምደድ የተሻለ ዋጋ አለው። የመወያያ ጥያቄዎችና እነሱን ተከትሎ የተቀመጡ በተለየ ቅርፀ - ፊደል የተሰየሙ መልሶች በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ ባሉ ክፍላት ተቀምጧል። እነዚህ የመወያያ ጥያቄዎች ፣ ታዳጊዎቹ የትምሕርቱን ዓላማ መገንዘባቸውን ለመረዳት የሚጠቅሙ ናቸው። እነዚህን ጥያቄዎች በተለያየ መንገድ መጠቀም ይቻላል ፤ አንደኛው መንገድ ፣ ከእያንዳንዱ ምዕራፍ ትምሕርት በኋላ ጥያቄዎቹን ለውይይት ማቅረብ ነው። ትክክል ያልሆነ እና ያልተሟላ ምላሽ ሲኖር ፣ ልጆቹን ማገዝ ያስፈልጋል።

በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ፣ የዝማሬ ግጥም ዝርዝር ተቀምጧል። ዋና ዋና ነጥቦቹ በጣም ግልጽ እንዲሆኑ ፣ ከተቀመጡት ውስጥ አንድ መዝሙር ወይም ተጨማሪ ሌሎች መዝሙሮችን አዘምር ፤ ወይም አንዱን ግጥም እንደመጨረሻ ጸሎት የማቅረብ አማራጭም መጠቀም ይቻላል። ትሪኒቲ ሐይሚናል (1990) ከነዚህ አማራጮች ውስጥ አብዛኞቹን ያካትታል። በመጨረሻም ፣ ዓለም አቀፉ የልጆች አገልግሎት (CMI) ባዘጋጀው የኮምፒውተር የዝግጅት ማቅረቢያ በመጠቀም ፣ የአንተንና የልጆቹን የመማር ማስተማር ሂደት ማቀላጠፍ ይኖርብሀል። በኮምፒውተር የተዘጋጀ የዝግጅት ማቅረቢያ ለእያንዳንዱ ክፍል እና ምእራፍ ተዘጋጅቶ ቀርቧል። በዝግጅት ማቅረቢያው እንዴት መገልገል እንደምንችል የሚረዱን ማስታወሻዎች ከዋናው ጽሑፍ በተናጠል ለብቻቸው ተቀምጠዋል።

<u>ለተጨማሪ መረጃ የሚጠቅሙ ምንጮች</u>

Palmer, Edwin H. *The Five Points of Calvinism. Grand Rapids, MI: Baker Book House,* 1999.

Vincent, Thomas. *The Shorter Catechism Explained from Scripture*. Carlisle, PA: Banner of Truth Trust, 2010.

Vos, Johannes G. *The Westminster Larger Catechism:* A Commentary. Edited by G. I. Williamson. Phillipsburg, NJ: *Presbyterian and Reformed Publishing Company*, 2002.

Williamson, G. I. *The Westminster Confession of Faith for Study Classes*. Phillipsburg, NJ: Presbyterian and Reformed Publishing Company, 2004.

Williamson, G. I. *The Westminster Shorter Catechism for Study Classes.* Phillipsburg, NJ: Presbyterian and Reformed Publishing Company, 2003.

ክፍል ኹለት ፡ የእግዚአብሔር ዕቅድ ለዓለም ኹሉ

ምዕራፍ 1

እግዚአብሔር ኹሉንም ነገር አቅዷአል።

ዓላማ ፡- ሙሉ የኾነውን ፣ የማይለወጠውን እና ግልጽ የኾነውን የእግዚአብሔርን ለፍጥረቱ ያለውን ዕቅድ ለመረዳት ።

የእምነት መግለጫ ፡- ጥያቄ ፡ የእግዚአብሔር ድንጋጌዎች ምንድናቸው ?

መልስ፡- እግዚአብሔር የደነገገው፣ ኹሉን ነገር አስቀድሞ የወሰነው፣ እንደፈቃዱ ምክር የሆነ የዘላለም ዓላማው እና ለክብሩ እንደሚውል ነገር ነው።

ጥያቄ፡- እግዚአብሔር ድንጋጌውን እንዴት ይፈጽማል ?

መልስ፡- እግዚአብሔር ድንጋጌውን የሚፈጽመው በፍጥረት ስራውና በመግቦቱ ነው።

የጥቅስ ጥናት፡- ኤፌ 1፡4፣ 11 “ዓለም ሳይፈጠር ፣ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን.....ኹሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሰራው እንደ እርሱ ዕቅድ አስቀድሞ የተወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል።”

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት ፡- እግዚአብሔር ኹሉን ደንግጓል።

ዓለማ፡- ሙሉ የኾነውን ፣ የማይለወጠውን እና ግልጽ የኾነውን የእግዚአብሔርን ለፍጥረቱ ያለውን ዕቅድ ለመረዳት ፡

ዓላማ፡- እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ያለውን ሙሉ ፣ ልከኛ እና የማይለወጥ ዕቅድ ለመረዳት።

የእምነት መግለጫ፡- ጥያቄ፡- የእግዚአብሔር ድንጋጌዎች ምንድናቸው ?

መልስ፡- የእግዚአብሔር ድንጋጌዎች ፣ የዘላለም ዓላማው እንደፈቃዱ ምክር የሚኾን እና ለክብሩ የሚውል አድርጎ የሚኾነውን ነገር ኹሉ አስቀድሞ ወስኗል።

ጥያቄ፡- እግዚአብሔር ድንጋጌውን እንዴት ይፈጽማል?

መልስ፡- እግዚአብሔር ድንጋጌውን በፍጥረት ስራ እና መግቦት ውስጥ ይፈጽማል።

መዝገበ ቃላትን ወይም ኢንተርኔትን በመጠቀም ታዳጊዎቹ እነዚህን ቃላት እንዲፈልጉ ጠይቃቸው (ቃላቱም ፡- ድንጋጌዎች ፣ ምክር ፣ አስቀድሞ መወሰን ፣ መፈጸም ፣ ተፈጥሮ እና መግቦት)። የእያንዳንዱን ቃላት ትርጉም እንዲያነቡ ፍቀድላቸው እና ትርጉማቸውን የተጻፈውን ሳያዩ ፣ በራሳቸው ቃላት መግለጽ እንዲችሉ አድርጋቸው። እያንዳነዱን ቃላት በሚገባ እስኪገነዘቡ ድረስ ፣ የተጻፈውን ትርጉም እና በራሳቸው ቃላት የተረጎሙትን ለያይተው ማስቀመጥ እንዲችሉ ንገራቸው። ሁልጊዜ የተፃፈውን ትርጉም ብቻ ሚደጋግሙት ከኾነ ፣ ትርጉሙን አንድ ጊዜ ብቻ ካዩት በኋላ በራሳቸው ቃላት እንዲገልጡት ዕዘዛቸው። በመቀጠልም ፣ የእምነት መግለጫውን ጥያቄና መልስ ደጋግመው ካነበቡ በኋላ ፣ በራሳቸው ቃላት መግለጥ በሚችሉት መጠን ስለ እግዚአብሔር ድንጋጌዎች ማብራራት እንዲችሉ ጠይቃቸው።

በመቀጠልም ፣ የኹለቱን የእምነት መግለጫዎች ጥያቄና መልስ ደግመው መጻፍ እንዲችሉ ፣ ቃላቶቹ ላይ ባላቸው የተሻለ መረዳት ላይ በመመስረት እንዲያሰፉት እዘዛቸው።

ከስር ያለው ምሳሌ ፣ ጥያቄውን ደግሞ መጻፍ ምን እንደሚመስል ያሳያል።

ጥያቄ፡- እግዚአብሔር የሚተገብረውን ነገር እንዴት ያቅዳል?

መልስ፡- እግዚአብሔር ማንንም ሳያማክር ከፍጥረት አስቀድሞ ኹሉንም ነገር ለራሱ ክብር ሊያደርግ ያቅዳል።

ጥያቄ ፡- እግዚአብሔር እቅዱን እንዴት ይፈጽማል?

መልስ፡- እግዚአብሔ ዘላለማዊ ዕቅዱን የሚፈጽመው ኹሉንም በፍጥረት ስራው ፣ በጥቃውና በክብካቤው ነው።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት

ታዳጊዎቹን ከእምነት መግለጫውጋ የሚሄድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንዲፈልጉ ጠይቃቸው

ኢዮብ 14 ፣ 5 "የሰው ዕድሜ አስቀድሞ የተወሰነ ነው ፤ የወራቱንም ብዛት ወስነህ አስቀምጠሀል ፤ ሊያልፈውም የማይችለውን ገደብ አኖርህለት።"

የእግዚአብሔር ድንጋጌ..... የፈቃዱ ምክር.....የሚኾነው ነገር ኹሉ አስቀድሞ መወሰን

መዝ 33፡11"የእግዚአብሔር ሐሳብ ግን ለዘላለም ይጸናል ፤ የልቡም ሐሳብ ለትውልድ ኹሉ ነው።"

የእግዚአብሔር ድንጋጌ..... የዘላለም ዓለማው

ምሳ 16፡9 "ሰው በልቡ መንገዱን ያቅዳል ፣ እግዚአብሔር ግን ርምጃውን ይወስንለታል።"

የእግዚአብሄር ድንጋጌ.....የፈቃዱ ምክር.....የሚሆነው ኹሉ አስቀድሞ የተወሰነ

ኢሳ 46፣ 10 "የመጨረሻውን ከመጀመሪያው፣ ገና የሚመጣውን ከጥንቱ ተናግሬአለሁ፤ ዐላማዬ የጸና ነው፤ ደስ የሚያሰኘኝንም አደርጋለሁ ብዬአለሁ።"

የእግዚአብሔር ድንጋጌ.....የዘላለም ዕቅዱ.....የፈቃዱ ምክር.....የሚኾነው ኹሉ አስቀድሞ የተወሰነ

ሐዋ 2፣23፣ “እግዚአብሔር በጥንት ውሳኔውና በቀደመው ዕውቀቱ ይህን ሰው አሳልፎ በእጃቹ ሰጣችሁ፤ እናንተም በክፉ ሰዎች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት።”

የእግዚአብሔር ድንጋጌ.....የዘላለም አላማው.....የኾነው ኹሉ አስቀድሞ የተወሰነ

ሮሜ 11፣34 “የጌታን ልብ ያወቀ ማነው; አማካሪውስ የነበረ ማነው?”

የእግዚአብሔር ድንጋጌ....ለራሱ ክብር.....የፍጥረት ስራ እና መግቦቱ

ኤፌ 1፣4 “በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በእርሱ መርጦናልና።”

የእግዚአብሔር ድንጋጌ.....የዘላለም ዕቅዱ.....የሚሆነው ኹሉ አስቀድሞ የተወሰነ ነው....የመግቦቱ ስራ

ኤፌ 1፡11 “እንደ ፈቃዱ ምክር መሠረት ኹሉን እንደሚሰራው እንደ እርሱ ዕቅድ አስቀድሞ የተወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል”

የእግዚአብሔርድንጋጌ...የዘላለም ዓላማው...የሚኾነውኹሉ....አስቀድሞ የተወሰ.....ድንጋጌውን ይፈጽማል።

ኤፌ 2፡10 " ምክንያቱም እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ስራ እንድንሰራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ስራዎች ነን።"

የእግዚአብሔር ድንጋጌ.....ዘላለማዊ ዓላማው....የሚኾነውን ነገር ኹሉ ወስኖታል.....የፍጥረት ስራና መግቦቱ

<u>የግብዣ መርሀ ግብር ዕቅድ</u>

ታዳጊዎቹ ፣ የልደት፣ የምርቃት ወይም የአመት በዓል ግብዣ ለጓደኞቻቸው ወይም ለቤተሰብ አባላቶቻቸው እንዲያዘጋጁ ንገራቸው። (እንደ አማራጭ፣ ሽርሽር ወይም የጋራ የካምፕ ጉዞ እንዲያቅዱ ፍቀድላቸው) መግዛት ለሚፈልጉት ነገር የዋጋ ዝርዝር እና መስራት ለሚፈልጉት ነገር የዕቅድ ዝርዝር አዘጋጅላቸው። የሚያስቡትን ነገር እንዲመራቸው ፣ እነዚህን ጥያቄዎች አቅርብላቸው፡-

ማንን እና እንዴት ነው ምትጋብዛቸው?

ርዕሱ ምንድነው?

ምን አይነት ማስዋቢያ እንዲሆን ትፈልጋለህ ; የግብዣ ስጦታዎች ይኖሩሀል?

በእረፍት ጊዜ ምን ዓይነት አገልግሎት ትሰጣለህ ?

ምን ዓይነት ጨዋታዎችን ትጫወታለህ ?

ከቤት ውጭ ላለ ዝግጅት፣ ዝናብ ቢመጣ ምን ታደርጋለህ

አንዳንድ ነገሮችን አስቀድሞ እንዲያዘጋጁ እና ካለቀ በኃላ ቦታውን እንዲያጸዱ የአንዳንድ ሰዎችን እገዛ ትጠይቃለህ (ወይም ኀላፊነታቸው አድርገው እንዲወስዱት ትሰጣቸዋለህ)

ዕቅድህን ከመተግበርህ አስቀድመህ ከማንጋ ምክክር ታደርጋለህ;

ለሚከተሉት ሐሳቦች ምላሽ ከሰጡ በኃላ ፣ የግብዣ መርሀ ግብር ዕቅዳቸው ከ እግዚአብሔር ድንጋጌዎችጋ ያለውን ምስስሎሽ እንዲገነዘቡት እርዳቸው።

1. **እግዚአብሔር በአምሳሉ ፈጥሮሃል። ምንም እንኳን ኀጥያት ያንን ቢያበላሸውም፣ ብዙዎቹ የሀሳብህና**

የአድራጎትህ መንገድ ያንን አምሳል ያንጸባርቃል።(በክፍል 1፣ ምዕራፍ 1 ላይ ያለውን የተበላሸ አምሳል ጉዳይ አስታውስ) የአንተ የግብዣ መርሀ ግብር እቅድ በምን ዓይነት መንገድ ነው የእግዚአብሔርን መልክ ማንፀባረቅ የሚችለው; ወይም እቅድህን ታላ ላይ ስትተገብረው ያንን መልክ ማንፀባረቅ ይችላል;

ትውስታህን ለማነቃቃት እንደገና የእምነት መግለጫውን ጥያቄና መልስ ደግመህ እየው።

ሀ. የአንተ ትንንሽ ነገሮችን የማቀድና የመተግበር አቅምህ የእግዚአብሔርን ኹሉን ነገር የማቀድና የመተግበር አቅምን የሚያሳይ ነው።

ለ. ምንም እንኪን እቅድህን ገና አልፈጸምከውም - ልትፈጽመው ግን ትችላለህ። ይሄ ነገሮችን አቅዶ የመፈጸም አቅም ከእግዚአብሔር ጋር ተመሳሳይ ነው።

ሐ. ልክ እግዚአብሔር ምርጦቹን የራሱ ሕዝብ እንዲኾኑ አድርጎ እንደመረጣቸው (ኤፌ 1፣ 11) ፣ አንተም ወደ ግብዣው እንዲመጡ ያሰብካቸውን ጠርተሃቸዋል።

መ. ልክ እግዚአብሔር ለሕዝቡ መልካምን ነገር እንደሚሰጣቸው ኹሉ ፣ አንተም ለጋበዝካቸው ሰዎች መልካም ነገር ልትሰጣቸው ተዘጋጅተሀል።

ሠ. ግብዣውን ካቀድክ በኃላ ፣ ማከናውን እንድትችል ትመኛለህ። እንዲያ ከሆነ ፣ ፕሮግራሙ በተሳካ መልኩ እንዲሄድልህና ለእንግዶቹ መልካም እንክብካቤን መስጠት ትፈልጋለህ። በሌላ አነጋገር በጣም መልካም የኾነ አስተናጋጅ መሆን ፈልገሃል። እግዚአብሔር ፍጥረቱን ጠብቆ ፣ በእንክብካቤ የሚያስፈልገውን ነገር ይሰጠዋል።

2. የአንተ ለዝግጅቱ ያወጣኸው ዕቅድና በኃላ ላይ የሚኖርህ አፈጻጸም ፣ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ካለው እቅድና አሰራርያ እንዴት ባለ መልኩ ነው የሚለያየው;

ሀ. በጥንቃቄ ካቀድክ በኃላ እንኳን ፣ አንድ አንድ ነገሮችን ልትዘነጋ ትችላለህ። በተመሳሳይ መልኩ ፣ ወደፊት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን አስቀድመህ መገመት ልትቸገር ትችላለህ (ለምሳሌ ፣ ድመት እንግዶች ከመምጣታቸው አስቀድሞ ፣ ባጌጠ መልኩ የተዘጋጀውን ኬክ ልትልሰው እንደምትችል ፣ አስቀድመህ ላትገምት ትችላለህ) ነገር ግን ፣ እግዚአብሔር አንዳች ነገርን እንዲህ ላለ ዕድል አሳልፎ አይተውም ፤ እቅዱም ኾነ አፈጻጸሙ ፍጹም ነው።

ለ. እቅድህ ያልተጠበቁ ክንውኖችንና ችግሮች ሲያጋጥሙት ይቀየሩ ይኾናል (ለምሳሌ ፣ ምናልባት ባለቀ ሰአት ፣ ድመቷን ውጪ አድርገህ ፣ ተቀያሪ ሌላ ኬክ መግዛት ይኖርብህ ይሆናል። ነገር ግን ፣ እግዚአብሔር አስቀድሞ ሊኾን ያለውን ኹሉ በትክክል ያያል እንጂ ልክ እንዳንተ ያቀደውን ነገር አያበላሽም። የእግዚአብሔር ዕቅድ በፍጹም አይቀየርም ፤ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ያቀደው ኹሉ ይሰምራል። እንደ ጠቢብና ኹሉን ዓዋቂ አምላክ ፣ የአንተን ዕቅድ መቀየር ቀድሞ ላሰበው ለራሱ ዓለማ ይጠቀምበታል።

ሐ. እቅድህን መያዝ የጀመርከው በኾነ ቀን እና በኾነ ጊዜ ነው። በተቃራኒው ፣ እግዚአብሔር እቅዱን የያዘው ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ ነው።

መ. ምናልባት ፣ ለግብዣው ዝግጅት አንዳንድ ሰዎችን በምክር እንዲያግዙህ ጠይቀኻቸዋል። ነገር ግን ፣ እግዚአብሔር ማንንም አያማክርም። እቅዶችን በራሱ ያወጣና እንደፈቃዱ ምክር ኹሉን ይፈጽማል።

ሠ. የግብዣው አከባበር መብራት አብርተህ ለተሳካለት ሰው ልታከብር ትችላለህ። የእግዚአብሔር እቅድ ግን ኹሉን ለራሱ ክብር ማድረግ ላይ ነው።

3. ግብዣህን ስታቅድም ኾነ ዝግጅቱን ስታሳምር ፣ እቅዱ የአንተ ብቻ ነበረ ወይስ የእግዚአብሔር ዕቅድ አካል ነበረ; ከምላሽህ በፊት 2ኛ ዜና 18፡19 እና ቁ 33ን ተመልከት

ሀ. የአንተ እቅድና ምርጫ ሊመስል ይችላል። ነገር ግን ፣ እያንዳንዱ ውሳኔ ውስጥ እግዚአብሔር የራሱን እቅድ እየፈጸመ ነው። አጋጣሚ የተባሉቱ ነገሮች እንኳን ሳይቀሩ ፣ እግዚአብሔር ኹሉን ለራሱ እቅድ ሊጠቀምብት ይችላል። ለምሳሌ ፣ 2ኛ ዜና 18፡19ን ተመልከት “እግዚአብሔርም ፣ የእስራኤል ንጉሥ አክዓብ በሬማት ገለዓድ ላይ ዘምቶ እዚያው እንዲሞት ማን ያሳስተው; አለ። አንዱ አንድ ሐሳብ ሌላውም ሌላ ሐሳብ አቀረበ” እግዚአብሔር እንዳለው ፣ አክዓብ ወደ ውጊያው ቦታ ሔደ ግን በሞት ፍርሃት ምክንያት ፣ ራሱን ሊደብቅ በመቻሉ ጠላቶቹ ሊያገኙት አልቻሉም። ነገር ግን ፣ 2ኛ ዜና 18፡33 እንደሚያሳየው ፣ “አንድ ሰው ፣ ቀስቱን በነሲቡ ቢያስፈነጥረው ፣ በጥሩሩ መጋጠሚያዎች መካከል አልፎ የእስራኤልን ንጉስ ወጋው”። በኃላ ላይም በዚያን ቀን ሞተ።

4. ግብዣን በማቀድና በማሰናዳት ውስጥ ለእግዚአብሔር ክብር ማድረግን እንዴት ትችላለህ;

1ኛ ቆሮ 10፡31 እንደሚለው ፣ “የምታደርጉትን ነገር በሙሉ ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት”። ድርጊትህን በሙሉ የእግዚአብሔርን መልካምነት ለማንጸባረቅ ስታደርግ ፣ ለእግዚአብሔር ክብርን ማምጣትና ሎሎቹም ይሄንን ክብር እንዲያዩት እድል መስጠት ትችላለህ። ግብዣ ስታሰናዳ ፣ በሰዎች የተከበቡ ልጆች ወይም የሚቀርቡህ ጓደኞችህን ሳይሆን ጓደኛ አልባ ልጆችን ጋብዛቸው። ለጤና የሚመችና ንጹህ በኾነ መንገድ አሰናዳ። ከራስህ ደስታ ይልቅ የሌሎችን ደስታ የምታስቀድም እጅግ መልካምና ቸር ተቀባይ ለመኾን አቅድ። እነዚህ እቅዶች እግዚአብሔርን የሚያስደስቱና የሚያከብሩ ናቸው።

<u>የእምነት መግለጫ ጥያቄዎች</u>

1. በእምነት መግለጫው መሠረት ፣ እግዚአብሔር ለምን ኹሉን ዓቀደ; ለምንስ ያቀደው ኹሉ እንዲኾን አስቀድሞ ወሰነ?

እግዚአብሔር ኹሉን ለራሱ ክብር አድርጓአል። ያ ማለት ግን እግዚአብሔር ልክ ሲያቅድ ወይም ያቀደውን ሲፈጽም ከብሮአል ማለት አይደለም። ይልቁን ፣ እግዚአብሔር ድሮም ኾነ ወደፊት የከበረ ነው። እግዚአብሔር ኹሉን ሲያቅድና ሲፈጽም ፣ የሚፈጽመው በፍጹም ክብሩ ውስጥ ኾኖ ነው (ሮሜ 11፡36)

2. እንደፈቃዱ ምክር ማለት ምን ማለት ነው?

በአጋጣሚና በዕድል ምክንያት የሚ ኾን ነገር የለም ፤ እግዚአብሔር ኹሉን ነገር እንደ ዕቅዱና እንደ ዓላማው እንዲ ኾን ደንግጓአል ፤ ይሄንንም ሲያደርግ ማንንም አላማከረም (ሮሜ 11፡34-36)

3. እግዚአብሔር የሚኾነውን ነገር ኹሉ አስቀድሞ ስለወሰነ ፣ የሰው ልጆች ኀጢያትን እንዲያደርጉ አስቀድሞ ወስኗል; እናም ሰዎች ኀጥያትን እንዲያደርጉ በመግፋት ዕቅዱን ተፈጻሚ ያደርጋል; ወይም በአጭሩ ለመግለጽ ፣ እግዚአብሔር የኀጢያት ደራሲ ነው?

የሰው ልጅ ኀጥያት ሊሰራ እንደሚችል፣ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ዕቅድ ከግምት አስገብቶታል። ነገር ግን ፣ እግዚአብሔር ከዓለም መፈጠር በፊት ፣ ለ ደህንነት ስለመረጠን ፣ የእግዚአብሔር ዕቅድ የሰውን ልጅ ከኀጢያት ማዳን እና መዋጀትንም ያጠቃልላል (ኤፌ1፡4)። አስታውስ ፣ እግዚአብሔር አዳምን የፈጠረው ፍጹም ከኀጢያት አልባ አድርጎት ነው። ልክ እግዚአብሔር ማንንም ለኀጢያት እንደማይትን ኹሉ አዳምንም አልፈተነውም ነበረ (ያዕ 1፡13)። ስለዚህ ፣ እግዚአብሔር ራሱ ምክንያት ካልኾነ፣ ኀጢያት እንዴት ተፈጠረ ; ሰይጣን አዳም ኀጢያት እንዲሰራ ፈተነው ፣ አዳምም ከመታዘዝ ይልቅ በኀጢያት ወደቀ (ዘፍ 3፡1 -5፣ ያዕ 1፡14 –15፣ 1ኛ ዩሐ 3፡8)። የኀጢያት አምጪው ሰይጣን እንጂ እግዚአብሔር አይደለም።

4. እግዚአብሔር ድንጋጌውናና ዕቅዱን እንዴት ነው የሚፈጽመው?

እግዚአብሔር ኹሉን ነገር ይፈጥራል ፣ ይጠብቃልም ይንከባከባል። በእነዚህ ድርጊቶቹ ፣ የራሱን ድንጋጌዎች ይፈጽማል።

5. እግዚአብሔር ኹሉን ይፈጥራል። ሰዎችም አንዳንድ ነገሮችን ይፈጥራሉ። ግን ፣ የእግዚአብሔር የፍጥረት ስራ ከአንተ እንዴት ይለያል?

በመጀመሪያ ደረጃ፣ አንተ አንድ ነገር ስትሰራም ኾነ ስትገነባ ፣ ከመጀመሪያውም የተፈጠረ ማቴሪያል ተጠቅመህ ነው ፤ ለምሳሌ ፣ እንጨት ፣ ሸክላ ፣ ሲሚንቶ ፣ ዱቄት ፣ ስኳር እና ቂቤ። ነገር ግን እግዚአብሔር ዓለማትን ሲፈጥር ፣ ከምንም አንስቶ ነው የፈጠረው - ከምንም (ዕብ 11፡3)። በኹለተኛ ደረጃ ፣ ሰው አንድን ነገር ሲፈጥር ፣ ብዙ ጊዜን ይወስዳል። በተቃራኒው ፣ እግዚአብሔር ነገሮችን ወደ መኖር ለማምጣት ከተናገረ በኃላ ወዲያው ይፈጠራሉ (ዘፍ 1፡3 ፣ መዝ 33፡9)

6. መግቦት ምንድነው?

መግቦት ክብካቤን የማቅረብ ስራ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ፣ የእግዚአብሔርን ለፍጥረቱ ያለውን የፍቅር እንክብካቤ ያሳያል።

<u>የቃል ጥናት ጥቅስ</u>

ኤፌ 1፡4፤11 “በፊቱ ቅዱሳንና በፍቅር እንሆን ዘንድ ዓለም ሳይፈጠር በፊት በእርሱ መርጦናልና.....ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሰራው እንደ እርሱ እቅድ አስቀድሞ የተወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል።”

እግዚአብሔር ጥቂቶችን ከአለም ጅማሬ አስቀድሞ መርጦአል። ማንም ይሔንን የማዳን ውሳኔ እንዲወስድ እግዚአብሔርን ጫና አላደረገበትም። በዘላለም ዕቅዱ መሠረት ፣ ክርስቶስ ኃጢያታቸውን ተሸክሞ እንዲወስድ እና ነጻ እንዲያወጣቸው አቅዶ ነበረ። የራሳቸው ከሆነ ስራ በተቃራኒ ፣ እግዚአብሔር ነፃ በሆነና ክፍያ በሌለው በጸጋው በኩል አድኖአቸዋል። ከመፈጠራቸው አስቀድሞ ከዘላለም በፊት እግዚአብሔር መርጦአቸዋል ፤ ደህንነታቸው በአጠቃላይ በእግዚአብሔር እጅ ላይ ነው።በክርስቶስ ከመለወጣቸው አስቀድሞ፣ በኀጥያት ፍርድ በታች የሆኑና ለመንፈሳዊ ሞት ኩነኔ ተላልፈው የተሰጡ ነበሩ። ዳሩ ግን ፣ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ መሠረት ፣ የክርስቶስ ሞት አጸደቃቸው፤ ጻድቃን አላቸው ፤ በዚህም ምክንያት ኀጢያት አልባና ኀጢያትን ተከትሎ ከሚመጣው አስፈሪው ሞት ተረፉ። ክርስቶስ ከመንፈሳዊ ሞት አዳናቸው ፤ ከቀደመው ፣ ከአሁኑና ከሚመጣው ኀጢያት ኹሉ አዳናቸው። በኀጢያት የተጨማለቀውን ልብሳቸውን አውልቆ ፣ የጽድቅን መጎናጸፊያ ሰጣቸው።

እግዚአብሔር ቅዱስና ነውር አልባ እንዲኾኑ መረጣቸው። ቅዱስ ማለት የተለየ ማለት ነው ፤ እግዚአብሔር

እነርሱን ሕይወታቸውን ከሌሎች ለይተው እንዲኖሩና ፣ ሲያስቡም ኾነ ሲመላለሱ ክርስቲያን ካልሆኑት በተለየ መልኩ እንዲኾን ይጠብቃል። “ቅዱሳን ኹኑ ምክንያቱም እኔ አምላካችሁ ቅዱስ ስለኾንኩ” (ዘሌ 19፡2)። ነውር አልባ ሲል ኀጢያት አልባ ፍጹም ሕይወት ማለቱ አይደለም። ይልቁን ፣ ኀጢያቱን በየጊዜው የሚናዘዝና ንስኀ የሚገባን ሰው ነው የሚናገረው። በኀጢያት ጉዳይ ምንም ሐሳብ የሌለውና ግድ የለሽ ሳይኾን በእግዚአብሔር ዘንድ መዝገብ ያስቀመጠ ነው። “ስለዚህ ወዳጆች ሆይ ፣ እነዚህን ሁሉ ነገሮች የምትጠባበቁ ስለ ሆናችሁ ፣ ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ ከእርሱ ጋር በሰላም እንድትገኙ ትጉ”(2ኛ ጴጥ 3፡14)። የቅድስና እና ነውር አልባ ኑሮአቸው ከክርስቶስ መልክታ የተስማማ ሲሆን ለጥሪያቸው የሚገባን ሕይወት መኖር እንዲችሉም ይረዳቸዋል። “እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወስኖአልና” (ሮሜ 8፡29)። “ለተጠራችሁበት ጥሪ የሚገባ ኑሮን ኑሩ” (ኤፌ 4፡1)። እግዚአብሔር ቅዱስና ነውር አልባ አድርጎ የሰራቸው ስራ የእርሱ ፍጹም ፈቃዱ አካል ነው። ሉዓላዊው አምላክ የሚኾነውን ነገር ኹሉ ያቅዳልም ይቆጣጠራል። ሕይወት አስቸጋሪና ግራ የሚያጋባ ሲኾን ፣ በዚህ እውነት ያርፋሉ - እየሱስ ጌታ ነው ፤ እግዚአብሔር ኹሉን ተቆጣጥሮአል። እግዚአብሔር ኹሉን እንደፈቃዱ ምክር ስላቀደና ለራሱ ክብር ስለሚያደርገው ፣ ለእነሱ ያለው መልካም እና የፍቅር ዓላማው አይጨናገፍም።

<u>የጥቅስ ጥናት ጥያቄዎች</u>

1. እግዚአብሔር ማንን እንደሚመርጥ መቼ ነው ያሰበው?
   እግዚአብሔር ዓለማትን ሳይፈጥር አስቀድሞ የሚድነውን አስቀድሞ መርጦአል።
2. ስራ እና ድርጊት እንዴት ነው የእግዚአብሔርን የማዳን ውሳኔ ሊነካ የሚችለው?
   እግዚአብሔር የሚያድነው በጸጋ ላይ በመመስረት እንጂ በስራ ወይም በድርጊት አይደለም። ስለዚህ ፣ የሰዎች መልካምም ኾነ መጥፎ ስራዎች ለእግዚአብሔር የማዳን ውሳኔ ላይ ምክንያቶች አይደሉም።
3. ቅዱስ ማለት ምንድነው?

ብዙ ሰዎች የሚያስቡት ቅዱስ ማለት ቀጥተኛ እንደማለት አድርገው ነው ፤ በተወሰነ መልኩ ልክ ነው። ነገር ግን ቃል በቃል ትርጉሙ "መለየት" ማለት ነው። ሕይወትን መለየት በዚያም ምክንያት ከኀጢያት መራቅ ማለት ቅዱስ መሽን ነው።

4. ነውር አልባ ኾኖ ለመኖር ፣ በፍጽምና እና ከኀጥያት አልባ መኖር አለብህ?
   በመጽሐፍ ቅዱስ ኀጢያት አልባ መሆን ማለት ኀጢያት አልባ ፍጽምና አይደለም። ይልቁን ፣ ነውር አልባ መሆን ማለት በቆሚነት ንስሃ መግባትና የኀጢያትን ኑዛዜ ይይዛል ፤ በዚህም ምክንያት ግለሰቡ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ሕብረት ይጠባቃል።
5. "እየሱስ ጌታ ነው እና እግዚአብሔር ኹሉን ተቆጣጥሮአል"። ይሔ አረፍተ ነገር ምን ማለት ነው?
   የሚሽነው ነገር ኹሉ ምንም ያክል አስቸጋሪና ግራ ሚያጋባ ይኹን ፣ የእግዚአብሔር ዕቅድ አካል ነው። ልክ እንደ ጌታ ፣ እየሱስ የሕይወታችን ባለቤት ነው። እንደ አምላክ ፣ ኹሉን ይቆጣጠራል። ስለዚህም ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ምንም ቢፈጠር በእርሱ ያርፋል ፤ እርሱንም ይታመናል።

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት ፡ እግዚአብሔር ኹሉን ደንግጎአል።</u>

በመጽሐፈ እዮብ ላይ በመመስረት የቀረበውን ይህንን እጥርጥር አንብብ ወይም በተግባር ግለጠው። በአንጻሩ ፣ ሚናዎቹን ለይተ ስጣቸውና ታዳጊዎቹ ይህንኑ ክፍል እንዲያነቡና በተግባር እንዲገልጡት አድርጋቸው። በዚህ ትረካ ውስጥ የእግዚአብሔርን የፍዘጥረቱንና የመግቦቱን ስራ እንዲያውቁ ተገዳደራቸው። (ማስታወሻ ፡- ትዕይንት 1 እና 2 ሚመስለው የእዮብ 1 እና 2 ክስተት ሲፈጸም ተደርጎ እንደነበረ ውይይት ነው።)

<u>ትዕይንት 1፡ የሰይጣን የመጀመሪያው ምክር</u>

ምንአልባት ይህንን ጥያቄ ጠይቀሃል፡- “መልካም ሰዎች ለምንድነው መከራ የሚደርስባቸው;” ለረዥም ዘመናት የሰው ልጅ እንዲህ አይነት እንቆቅልሾችን ሲጠይቅ ቆይቶአል። በእርግጥ በአብርሃምም ዘመን የዚህ ድራማ ጀግናው ገጸባህሪይ ይህንኑ ተመሳሳይ ጥያቄ ሲያቀርብ ነበረ። የመጀመሪያው ትዕይንት ሲከፈት ፣ ሰይጣን አብረውት ካሉ አጋንንቶች ጋር ትርጉም የለሽ ነገር ሲቀባጥር ነው የሚታየው።

ሰይጣን ፡- መላእክቶቹ ባሉበት ከእግዚአብሔር ጋር ሳወራ ነበረ ። የተፈጠረውን ገምቱ እስኪ; የእግዚአብሔር አገልጋይ የኾነውን እዮብን እንድፈትነው ፈቃድ አገኘሁ። በጣም ላስጨንቀው እችላለሁ ከዚያም በኃላ እግዚአብሔርን እንዲሳደብ ላደርገው።

የመጀመሪያው አጋንንት፡- (አረመኔአዊ በኾነ ደስታ እጁን ፈተገ) ኦ! ይሔማ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነው የሚኾነው - በእርግጥ ለእኛ እንጂ ደስታው ለእዮብ አይደለም። የሚወደውን አገልጋዩን እንድትፈትን ግን እንዴት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ልታገኝ ቻልክ?

ሰይጣን፡- እግዚአብሔር እኔን ስለ እዮብ የማስበውን ነገር ጠየቀኝ ። እናም እንዴት ነቀፋ አልባ እና ቀጥተኛ እንደኾነ ነገረኝ። አዎ! ይሔ በጣም የሚያበሳጨና የሚያሳምም ነው።

2ኛው አጋንንት፡- አዎ! ሰዎች ሲሔዱ ፣ ኢዮብ ቀጥተኛ ሰው ነው። ግን እንዴት ብለህ እዚህኛው ሐሳብ ላይ ደረስክ?

ሰይጣን ፡- እሱ እንደ ኢዮብ ባለጠጋ ካደረገው ማንኛውም ሰው ጻድቅ እንደሚኾን ለእግዚአብሔር ነገርኩት ። ከዚያም በኃላ ፣ ተግዳሮቱን ቀጠልኩት።

እግዚአብሔርን እንዲህ ብዬ
ጠየቅኩት ፡- በረከቱን ኹሉ ከእርሱ
ላይ ብወስድበትና እዮብን ብቻውን
ባስቀረው ፣ በእርግጠኝነት
እግዚአብሔርን በፊቱ ይሰድበውና
ከእርሱጋ ያለውን ነገር ያቆማል።

አጋንንት 1፡- ነገር ግን ፣ ይኸውልህ ሰይጣን ፣ እግዚአብሔር እኩይን በሰዎች ላይ አያመጣም። አግዚአብሔር ራሱ ይህንን በደንብ እንሚያውቀው ፣ ይሔ የአንተ ስራ ነው።

ሰይጣን፡- አዎ! በትክክል! ቅድም እንዳልኩት ፣ ሰውነቱን እንዳልጎዳበት ከሚል ትዕዛዝ በቀር ፣ በወደድኩት መንገድ ኢዮብን እንድፈትነው ከእግዚአብሔር ፈቃድ አግኝቼአለሁ። ስለዚህ ፣ ኑ እንጀምር ስራችንን እናንተ አጋንታዊ ወዳጆቼ። የእዮብን ጥሪት ለማጥፋት ሰውንና ተፈጥሮን እንጠቀማለን ፤ ልጆቹንም እንገድልበታለን። ከዚህ በኃላ እግዚአብሔርን ለመውደድ ምንም ምክንያት ሳይኖረው ሲቀር ፣ በእርግጠኝነት ይረግመዋል ፤ ከዚያም ዋናውን ድል እንጎናጸፋለን።

አጋንንት 2፡- ከሚያበሳጭ ሳቅጋ ኢዮብ መጣንልህ አሉት።

ትዕይንት 2፡- የኢዮብ አራቱ አደጋዎች

ተራኪው፡- ከጥቂት ቀናት በኃላ፣ ኢዮብ በቤቱ ተቀምጦ ስለ እግዚአብሔር መልካምነት ፣ ስለትልቁ ፍቅሩ እና ስለማይቆጠረው በረከቱ ያሰላስል ነበረ። በድንገት አንድ አገልጋይ ገባ እና ከሐሳቡ አወጣው።

የመጀመሪያው መልዕክተኛ፡- እያለከለከ እና ብዙ እየተነፈሰ ወደ ኢዮብ መጣና “ኢዮብ መጥፎ ዜና አለኝ ፤ መሬትህን በማረስ ላይ እያለን ሳባዊያን አጠቁን ። በሬዎችህንና አህዮችህን ሰረቁ ፤ ከእኔ በቀር ያሉ አገልጋዮችህንም ገደሉ።”

2ኛው መልዕክተኛ ፡- እያለከለከ እና ብዙ እየተነፈሰ ወደ ኢዮብ መጣና “ከሰማይ እሳት ወድቆ ኹሉንም በጎችህንና እረኞቹን በላቸው ፤ ከእኔ በቀር። እኔ ብቻ አመለጥኩኝ።

3ኛው መልዕክተኛ፡- እጁን እያወናጨፈ ወደ ኢዮብ መጣና ፣ ሶስት ክፍል ከለዳዊያን መጡና ግመሎችን ሰረቁ። ከእኔ በቀር ያሉ አገልጋዮችህንም ገደሉ ።

4ኛው መልዕክተኛ፡- በቁጭትና በሐዘን ደረቱን እየደቃ ወደ ኢዮብ መጣና ፡ - ሴት ልጆችህና ወንድ ልጆችህ አንድ ላይ እየበሉና እየጠጡ እያለ መብረቅ ቤቱን መታው። ጣራው ወደቀ፣ ግድግዳውም ፈረሰ። ከእኔ በቀር ኹሉም ሞቱ

ኢዮብ፡- በእንባ ተሞልቶ በመሬት ላይ ሰገደ። ምንም ሳልይዝ ወደ እዚህ ምድር መጣሁኝ። ምንም ሳልይዝም እሔዳለሁ። እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሳ። የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይኹን።

ሰይጣን፡- አንድ ጥግ ላይ ቆመና እጁን ወገቡ ላይ በማድረግ ማጉተምተም ጀመረ። እንዲህ አልነበረም መናገር ያለበት። እቅዴ እየተበላሸ ነው። የእዮብ ሕይወት የሚበላሽበት እና እግዚአብሔርን የሚሰድብበት ሌላ መንገድ መፈለግ አለብኝ።

<u>ሶስተኛው ትዕይንት ፡ -</u> <u>የሰይጣን ኹለተኛው ምክር</u>

ሰይጣን፡- የሲያል ወዳጆቼ ወደዚህ ተሰብሰቡና ስሙኝ፡- ከእግዚአብሔርታ ከነበረኝ ኹለተኛው ስብሰባ መመለሴ ነው። እናም አሁን የኢዮብን ውድቀት ለማፍጠን በጣም ቀላል መንገድ አለኝ። አሁን በእርግጠኝነት እግዚአብሔርን ይሰድባል።

አጋንንት 1፡- ይሄ ምንድነው; ስለዚህ ነገር ንገረኝ?

ሰይጣን፡- መልካም ፣ ኢዮብን ለመስበር የወሰድኩት የመጀመሪያው ሙከራ ባለመስራቱ በጣም ተናድጄአለሁ። ኢዬብ ምንም እንኳን ልጅ አልባ እና ደሃ ቢኾንም ፣ አሁንም ጻድቅ እና ቅን መኾነኑን እግዚአብሔር አስታውሶኛል ፤ ይሔ ትክክል መሆኑን ማመን አለብኝ። ከዚያ ግን አዲስ ብልሀ የኾነ ሰይጣናዊ ሐሳብ ነበረኝ ፤ እናም በፍጥነት ለእግዚአብሔር አቀረብኩት።

አጋንንት 2፡- ንገረን እርሱ ሐሳብ ምን ነበረ?

ሰይጣን ፡- በኢዮብ ስጋ ላይ ክፉ ደዌ እንዳመጣበት እግዚአብሔርን ጠየቅኩት ። የሰው ልጆች ሊቆቆሙት የማይችሉት አንድ ነገር ቢኖር ፣ የማያቆርጥ ከፍተኛ ሕመምን ነው።

አጋንንት 1፡- ተዲያ እግዚአብሔር አካላዊ ደዌን ኢዮብ ላይ እንድታመጣበት ፈቀደልህ?

ሰይጣን፡- አዎ! ሕይወቱን ሊያሳጣው ከሚችለው ነገር ያነሰ የቱኛውንም ዓይነት ሀመም በስጋው ላይ እንዳመጣበት ፈቅዶልኛል። ስለዚህ ፣ ከራሱ እስከ እግሩ ድረስ በእባጭ እንምታው። ከእባጭ በላይ ሊያስጨንቀውና ሊያበሳጨው መጥፎ ሊኾንበት የሚችል ነገር የለም።

አጋንንት 2፡- ኦ! ይሔ በጣም ደስ የሚል ክፉ ሐሳብ ነው። የእግር እሳት ሊኾን የሚችል ምን ዓይነት የጠላት መዝናኛ የሚሰጠን። ከእዮብጋ ኹለተኛ ዙር !

<u>አራተኛው ትዕይንት ፡-</u> <u>የኢዮብ ሚስት</u>

ተራኪው፡- ባልና ሚስቶች በመልካምም ኾነ መጥፎ ጊዜ እንዲዋደዱና እንዲደጋገፉ እግዚአብሔር ይጠብቃል። በኢዮብ ሕመም ወቅት ከታየችበት ጥቂት ጊዜ ውጪ ስለኢዮብ ሚስት ብዙ የምናውቀው ነገር የለም። ቃለቶቿ ኢዮብን የሚያበረታ ይኹን ወይ እግዚአብሔርን የሚያስደስት እናንተ ፍረዱ ።

ኢዮብ፡- አካላቱን በገል አየፋቀ ያቃስታል። ወዮ! አስከዛሬ ከማውቀው ነገር ኹሉ በላይ ይኼ እባጭ ብዙ እያሰቃየኝ ነው።

የኢዮብ ሚስት፡- እስካሁን በእግዚአብሔር ታምናለህ; ለምን እግዚአብሔረን ሰድበኸው አትሞትም?

ኢዮብ፡- እባክሽን በገበያ መሐል እንዳሉት እንደነዚያ ሞኝ ሴቶች አትሁኚ። እግዚአብሔር የሰጠኝን መልካም ነገር ኹሉ ተቀብዬአለሁ ፤ ችግሩንስ ለምን አልቀበለውም; እግዚአብሔር ሕይወት ጣፋጭ እንደኾነች ቃል አልገባልንም።

የኢዮብ ሚስት፡- ጭንቅላቶቿን እየነቀነቀች እና እያጉተመተመች በብስጭት እየወጣች ፣ እኔ ይሔንን ፈጽሞ ልገነዘበው አልችልም።

<u>አምስተኛው ትዕይንት ፡-</u> <u>የኢዮብ ሶስቱ ወዳጆች</u>

ተራኪው፡- በፍጹም ሚስቱ ኢዮብን ልታበረታታው አልቻለችም። አበረታታቸዋለች; በእርግጥ የበለጠ የተመሳቀለ እንዲኾን አድርጋው ይኾናል። ነገር ግን፣ የደረሰበትን ችግር ሲሰሙ ሊጎበኙት የመጡ ሶስት ጓደኞች ነበሩት ፤ ኤልፋዝ ፣ በልዳዶስና ሶፋር ይባላሉ። ጥልቅ የኾነ ሐዘናቸውን ለመግለጽ ራሳቸው ላይ አመድ ነስንሰው ልብሳቸውን ይቀዱ ነበረ። (ተራኪው ሲናገር ፣ ሶስቱ ሰዎች ቀርበው ልብሳቸውን

እየቀደዱና አመድ እየነሰነሱ በኢዮብ እግር ስር ተቀመጡ ፤ ነገር ግን ምንም አይናገሩም ነበረ።) የሚያጽናናም ኾነ የሚተች ቃላት ሳይናገሩ ለሰባት ቀናት አብረውት ቁጭ አሉ። በሰባተኛው ቀን ኢዮብ ዝምታውን ሰበረ።

ኢዮብ፡- ወዮ! ለምን በተወለድኩበት ቀን አልሞትኩም። በስቃይ እንዲያሳልፍ ሕይወት ለምን ለሰው ልጅ ተሰጠች; በዚህ ስቃይ ከምኖር ብሞት እመርጣለሁ።

ኤልፋዝ፡- ኢዮብ እባክህን ትዕግስት የሌለህ አትሁን። አንት ሁልጊዜ ቀጥተኛ ሰው ትመስል ነበረ፤ የሚሰናከሉትን የምታነሳ እና ሌሎች በጽድቅ ጎዳና እንዲሄዱ የምትመክር። ነገር ግን፣ የእኔ ልምድ የሚያሳየኝ ፣ እግዚአብሔር በጎጥያት የሚሔዱትን እንደሚቀጣቸው ነው። እኔ አንተን ብሆን ኖሮ ጎጢያቴን ለእግዚአብሔር እናዘዘው ነበረ። አስታውስ ፣ እግዚአብሔር ሰዎችን ሲየስተካክል ፣ ለበረከት አስቦ ነው።

ኢዮብ ለኤልፋዝ፡- ተስፋ የቆረጠ ሰው የወዳጆቹ መሰጠትና እና ርህራሔ ነው የሚያስፈልገው። እኔ ሕይወቴን መርምሬአለሁ ፤ ሕየይወቴን ለዚህ የዳረገኝን ነገር አላገኘሁም። ከቻልክ ፣ ስህተት የሰራሁበትን ቦታ አሳየኝ። በዝምታ ሰምቼህ ሁሉን አንተ እንዳልከኝ አደርጋለሁ።

ኢዮብ ለእግዚአብሔር፡- ኤልፋዝ ዝም ሲል ኢዮብ መጸለይ ጀመረ። ቅርፊትና ትሎች ሰውነቴን ሸፈኑት ፤ ሰውነቴም አመረቀዘ። ስቃዬ በለሊት ሳይቀር ይቀሰቅሰኛል። የምግብ ፍላጎት የለኝም ፤ የምበላው ኹሉ ይወጣል። ሕይወቴን ናቅኪት ፤ ሞትንም እሻታለሁ።

በልዳዶስ፡- ኢዮብ እንደዚህ ማውራት አቁምና የድሮ ጓደኛህ የኾንኩትን በልዳዶስን ስማኝ። አንተ እነዳልከው ንጹህና ቀጥተኛ ሰው ከሆንክ ፣ እግዚአብሔር ሕይወትህን ይመልሰዋል። ትፈወስማለህ። እሱ ነውር አልባ የኾኑት ላይ ስቃዩን አያበዛም። ነገር ግን፣ አስታውስ መብረቅ በወረደ ጊዜ ልጆችህን እግዚአብሔር በጎጢያታቸው ምክንያት እንደቀጣቸው። አንት ያልነጻህና በክፋት ያለህ ከኾንክ እግዚአብሔር ሕይወትህን እንደሚያጠፋው እወቅ። ልክ አተክልተኛ በጥሩ ሁኔታ ያደገውን አረም ከመሬት ላይ ከነቀለው በኃላ አፈሩ የተነቀለውን አረም ይረሳዋል።

ኢዮብ፡- ነገር ግን ፣ ማነው በእሱ ፊት ሙሉ በሙሉ ነቀፋ አልባ የሚሆነው; የእግዚአብሔር ሀይልና ጥበብ ታላቅ ነው ። እኔ ከእሱጋ አልከራከርም። እኔ ከጎጢያት ውጪ ነኝ ብል እንኪን የገዛ ራሴ አፍ

ይኮንነኛል። በተጨማሪም ፣ እኔ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ኀጢያተኞችን የሚቀጣና ጻድቃንን ደግሞ የሚያበለጽግ ነው ብዬ አላምንም። በጣም ተቃራኒውን አይቼ አውቃለሁ ፤ ክፉ የሆነው ሲበለጽግና መልካም የሆነው ሲሰቃይ።

ሶፋር፡- በኀይል እየተነፈሰና እየተንሳራደደ ፣ በእርግጠኝነት የራስህን ንግግር መስማት ትወዳለህ። አሁን ግን የሶፋርን ንግግር ስማ። "ለስቃዬ ሚዳርገኝን ምንም ነገር አላደረግኩም" አልክ። ነገር ግን በዚህ ጉዳይ የእግዚአብሔርን አተያይ መስማት እፈልጋለሁ። እግዚአብሔርን ብዙ ጊዜ እንደበደልክ እኔ እወራረዳለሁ ፤ አንዳንዱን አሱ ይቅር ቢልህም። ይኸውልህ ፣ ኀጢያትህን ብትናዘዝ ፣ እግዚአብሔር ይመልስሀል ፤ እንደገናም በሰላም እና እረፍት መተኛት ትችላለህ። በእረፍት የተሞላ ምሽት በጣም ጥሩ ድምጽ አለው ፤ አይደለም?

ኢዮብ ለራሱ፡- ብቻውን እያጉተመተመ ፣ እንዲህ ባሉ ወዳጆች ተከቦ ፣ ማን ጠላት ያስፈልገዋል?

ኢዮብ ለጓደኞቹ ፡- በጥልቅ ሐዘን ውስጥ ኾኖ፣ ወዳጆቼ የእናንተ ሕይወት ያለስቃይ ኾኖ ምነው ምንም ሳይመስላችሁ በእኔ ሕይወት የምትሳለቁት; ያላችሁ ጥበብ ሁሉ አብሮአችሑ እንደሚጠፋ ልታውቁ ይገባል። ትልቅ መረዳት እንዳላቸው ሆናችሁ ፣ ብዙ ቃላትን ተናገራቹ ፤ ግን እነዚህን ግልጽ ነገሮችን ማነው የማያውቀው; እግዚአብሔር ለእኔም አዕምሮን ሰጥቶኛል ፤ እናንተ የምትሉትን ኹሉ አስቀድሜ አውቃለሁ። ነገር ግን ፣ እኔን ያለመረጃ ጥፋተኛ አድርጋችሁኝ በሀሰት ቀባችሁኝ። እናንት የማይጠቅሙ አካሚዎችና የሰው ስቃይና ሕመምን የምታባብሱ አጽናኞች ናችሁ። ጠቢባን መሆን ከፈለጋችሁ ፣ ዝም በሉ እና ስሙ። ሀብት እና ብልጥግናን እንደ እግዚአብሔር የጉብኝት ምልክት አድርጋችሁ ታደንቃላችሁ። ድህነትንና ስቃይን ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ፍርድ አድርጋችሁ ነው ምትረዱት። ነገር ግን እግዚአብሔር ኹልጊዜ እንደዚያ አይደለም ፤ እርሱ አንዳንድ ጊዜ ክፉ የሆነው እንዲበለጥግና መልካሙ ደግሞ እንዲቸገር ይፈቅዳል። ጥበብና ሀይል የእርሱ ናቸው፤ ሁሉም ነገር የሚሆነው እንደፈቃዱ ምክር ነው። ከወዳጆቹ ብዙ ዝምታ በኃላ ፣ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ ፣ በተስፋ መቁረጥ እጁን አነሳና ፣ ለእናንተ ቃላቶቼን አባከንኩ። ጉዳዬን በእግዚአብሔር ፊት እና ለእሱ ብቻ አቀርባለሁ። ቢገድለኝም ፣ እኔ እሱን መታመኔን አሳቆምም ። ምክንያቱም ቤዛዬ ሕያው እንደሆነ አውቃለሁ። እንደ ፈራጅ በምድሩ ላይ አንድ ቀን ይቆማል ፤ በራሴ አይኖች አየዋለሁ ። ኦ! ልቤ እንዴት እንደሚናፍቅ ያንን ቀን ፤ እኔን የሚያጸድቅበትን።

ኢዮብ ለእግዚአብሔር ፡- ተንበርክኮ እና እጁን አጣምሮ ወደ እላይ እያየ ፣ ኦ! ጌታዬ ፣ ፊትህን ከእኔ አትሰውር ፤ እርስ በርሳችን እንነጋገር። እባክህን ይሔንን አስፈሪ መከራ ከላዬ ላይ አንሳው። ከባዱን እጅህን ከላዬ ላይ አንስተህ ፣ ከሚያስጨንቀው ፍርሃት ገላግለኝ። (ጸሎቱን አቆርጦ ወደታች ካቀረቀረ በኃላ ፣ እንደገና ወደ ላይ ቀና አለና ጸሎቱን ቀጠለ።) እያንዳንዱ ሰው መቼ እንደሚሞት አንት ታውቃለህ። ጊዜው አጭር እና በችግር የተሞላ ነው። ነገር ግን ሰው ከሞተ በኃላ ፣ እንደገና መኖር ይችላል; እኔ እንደዛ አምናለሁ። ከእዚኛው ሕይወት ስትጠራኝ ፣ ጎጢያቶቼን ትሸፍናለህ።

<u>ትዕይንት 6 ፡-</u> <u>የኢዮብ አራተኛው ጓደኛ</u>

ተራኪው፡- የኢዮብ ወዳጆች እንዲህ እያሉ ለረዥም ሰዓታት ተሟገቱት። ኢዮብ ግብዝ እንደሆነ እየነገሩትና የሆነው ነገር ሁሉ በትክክል ፍትሃዊ መሆኑን ያረጋግጡለት ቀጠሉ። ኢዮብም ያንን ክስ ልክ አለመሆኑን ፍጹም ባይሆን እንኳን ፣ ጎጥእ አለመሆኑን እያቀረበ ይከራከር ነበረ። ጎጢያት ነቅሰው አውጥተው እንዲያሳዩት ወዳጆቹን ቢጠይቃቸውም እነሱ ግን ይህንን ጥያቄ ችላ ይሉት ነበረ። የእዮብን ጎጢያት ማሳየት አውጥቶ ማሳየት አይፈልጉም ነበር፤ በዚያ ላይ እግዚአብሔር ጎጥያተኞች እንዲበለጥጉ እና ጻድቃን ደግሞ እንዲሰቃዩ የመፍቀዱን የኢዮብን ምልከታ ለመዳሰስ ፍቀዳኞች አልነበሩም። በዚህም ምክንያት ፣ መሰረት አልባ ለሆነ ድምዳሜ እና ፍርድ ይቸኩሉ ነበረ። "ኢዮብ እየተሰቃየ ያለው ጎጢያት ሰርቶ ስለኾነ እና በእግዚአብሔር ፊት በኩነኔ ስላለ ነው።" ይላሉ። ነገር ግን ፣ ከሁሉ በጣም የሚያንስ ወጣት በመካከላቸው ተቀምጦ ነበረ ፤ የሱ ስም ኤሊሁ ይባላል።

ኤሊሁ ለወዳጆቹ፡- እኔ ወጣት ነኝ ፤ ነገር ግን እናንተ ሶስታችሁ ከእኔ የበለጠ ረዥም ዘመን ኖራችዋል። ከአክብሮት የተነሳ ፣ እስካሁን ሳላወራ ቆይቻለሁ ፤ ታላላቆቼ ጥበብን ለኢዮብ እንዲያስተምሩ ብዬ። ነገር ግን ፣ ማናችሁም የኢዮብን ክርክር አልመለሳችሁለትም ወይም ልክ አለመሆኑን በአሳማኝ መልኩ አልነገራችሁትም። አሁን እናንተ ዝም ብላችኃልና እኔ ልናገር። ሁሉን የሚችል አምላክ ፣ መረዳትን እሱ ለፈቀደው ኹሉ ሰጥቶታል ፤ አንዳንድ ጊዜም ለታናናሾች ሳይቀር ጥበብን ይሰጣል።

ኤሊሁ ለኢዮብ፡- ኢዮብ ስማኝ ። ንጹህና ጎጢያት አልባ እንደሆንክ ስትናገር ሰምቼሀለሁ። ፍትህን እየካድክ ፣ እግዚአብሔር ያለምክንያት ስህተትን እንደሚያወጣ ተናግረሃል። በዚህ ጉዳይ ተሳስተሃል ፤

ምክንያቱም ፣ እግዚአብሔር ከሰው ይበልጣል እናም የእሱ መንገድ ሁልጊዜም ንጹህና ትክክል ብቻ ነው። እናም ፣ እግዚአብሔር ጸሎትን አይመልስም ብለህ ታጉረመርማለህ። ነገር ግን እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ ይናገራል ፤ ሰው ግን ይህንን አይመለከትም። አንዳንድ ጊዜ በህልም ይናገራል ፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በህመም ውስጥ። ምናልልት አንድ መልካም ነገር በሕይወትህ ሊፈጽም ስላሰበ ፣ በዚህ ስቃይ ውስጥም እየተናገረህ ይሆናል። እግዚአብሔርን ለማስደሰት ባደረግከው ሙከራ ውስጥ ፣ ምንም ነገር እንዳላገኘህ ሆነህ ትቃወማለህ። ኢዮብ፣ ተጠንቀቅ ፣ በስቃይ ውስጥ ለማለፍ ክፋትን አንተ አልመረጥክም። እግዚአብሔር ፍትህ አልባ እንደሆነ አድርገህ ለመክሰስ እየሞከርክ ነው። ነገር ግን ፣ ኹሉን ቻዩ ስህተትን በፍጹም አይሰራም። ስለዚህ ፣ የአመጽን ነገር በእግዚአብሔር ላይ ለመናገር ተጠንቀቅ። እግዚአብሔር ፍትሀዊ ፣ ታላቅ ፣ ጻድቅ እና ዘላለማዊ ነው። እርሱ ስህተትን አይሰራም ፤ መንገዱም ኹሉ ከአንተ መረዳት ያልፋል። ኢዮብ ፣ ቁምና የእሱን ድንቅ ተመልከት። እርሱ ፣ በረዶው እንዲወድቅ ያደርጋል ፤ መብረቅና ነጎድጓድንም ይቆጣጠራል። የአየሩን ሁኔታ መቆጣጠር ትችላለህ ኢዮብ; አስደናቂ ስለሆነው ታላቅነቱ ፣ ስለ ከበረው ኀይሉ ፣ ስለ ፍትሁ እና ስለ ታላቁ ጽድቅ ፣ ሁሉን ቻዩን አምላክ ልናከብረው ይገባል ፤ ከእኛ በተያያዘ ያለውን የእሱን ቀጥተኛነት ልንጠይቀው አይገባም።

ትዕይንት 7፡- <u>የእግዚአብሔር ምክር ቤት</u>

ተራኪው፡- ኢዮብ ሶስቱንም ወዳጆቹን ዝም ቢያሰኛቸውም ፣ ንጽሕናውን በተመለከተ ግን ሊያሳምናቸው አልቻለም። ምንም እንኳን ኤሊሁ ኢዮብን ዝም ቢያሰኘውም ፣ በራሱ ሀዘን ዙሪ በመሆን ፣ ኢዮብ እግዚአብሔርን የመውቀሱን ኩነኔ አልተናዘዘም። በመጨረሻም ፣ እግዚአብሔር ተናገረ። ለኢዮብ በቀጥታ ከመመለስ ይልቅ ፣ የቱኛውም ሰው ሊመልስ የማይችላቸውን ተከታታይ ጥያቄዎች አቀረበለት። በምላሹም ፣ ኢዮብ የእግዚአብሔር መንገድ በጣም የተሻለ ነው አለ።

እግዚአብሔር ለኢዮብ፡- በባዶ ቃላቶችህ ፣ የዘላለም ዓላማዬን ለምን ታጨልማለህ; ኢዮብ እኔ አለምን ስፈጥር አንተ የት ነበርክ; ለባሕር ገደብን ማን አደረገ; ፀሀይ እንድትወጣ ማድረግ ትችላለህ; የበረዶ ግግርና ዝናብ እንዲወድቅ ፣ ንፋስ እንዲነፍስ; በሰማዩ ላይ ብሩህ የኾኑ ህብረ ክዋክብት እንዲወጡ ማድረግስ ትችላለህ; የተራራውን ፍየል መቆጣጠር ትችላለህ ፣ የምድረበዳውን አህያስ፣ ወይንም ጠንካራውን በሬ ; ለፈረስ አንተ ጉልበትን ሰጥተኸዋል; ጭልፊትና

ንስርስ በአንተ ትዕዛዝ ነው የሚመጥቁት; (ትነሽ ቆየና) ፣ ኹሉን ቻዩን ልትቃወም ትችላለህ ? ከእኔጋ ስለተከራከርክ ፣ መልስ ስጠኝ።

ኢዮብ፡- (በታላቅ ፀፀት በግንባሩ ወደቀ) እኔ የማልጠቅም ነኝ። ኦ! አምላኬ ፣ ለዚህ መመለስ አልችልም።

እግዚአብሔር ለኢዮብ፡- ኢዮብ ፣ ተነስና ራስህን ደግፍ፤ እኔ እጠይቅሃለሁ ፤ አንተም መልስልኝ። የእኔን ፍትህ ጥያቄ ውስጥ በመክተት ፣ ራስህን አጽድቀህ እኔን ትኮንነኛለህ; እንደእኔ ሀይል ካለህ ፣ ራስህን በክብር ፣ በፍርሃትና በታላቅነት ተላበስ። ኩሩ የሆነውን ዝቅ አድርግ ፤ ክፉንም ሰው አጥፋ። እኚህን ታላላቅ ስራዎች መስራት ከቻልክ ፣ ራስህን ማጽደቅ እንደምትችል እኔ አምናለሁ።

ኢዮብ፡- ኦ! አምላኬ አንተ ብቻህን ሁሉን ማድረግ ትችላለህ። ዕቅድህን ሚያጨነግፍ ማንም የለም። እኔ ስለማልረዳቸው ነገሮች ተናገርኩ ፤ ለእኔ እጅግ አስደናቂ ስለሆኑ ነገሮች። ነገር ግን ፣ አሁን አንተን አየሁህም ሰማሁህም። አሁን ራሴን እንቃለሁ ፤ አመድን ነስንሼም ንስሃ እገባለሁ።

እግዚአብሔር ለ ኢዮብ ወዳጆች፡- ኤልፋዝ ፣ በልዳዶስና ሶፋር ፣ እኔን ባለተገባ መልኩ ለአገልጋዬ ለኢዮብ በማቅረባችሁ በጣም ተበሳጭቼአለሁ። የሚቃጠልን መስዋዕት ሂዱና አቅርቡ ኢዮብም ይጸልይላችኃል። ርህራሄን ባለማሳየታቹና በግዴለሽነት በመናገራቹ ፣ የኢዮብን ጸሎት ስለምሰማ ፣ በእናንተ ላይ በቁጣ አልፈርድም። (በጎፍረት አንገታቸውን ደፍተው ፣ ከፊቱ ዘወር አሉ።)

ተራኪው፡- እግዚአብሔር እንደተናገረው ፣ ሶስቱ ሰዎች አደረጉ ፤ ኢዮብም ጸለየላቸው። ከዚያም ፣ እግዚአብሔር ኢዮብን ባረከው ፤ ቀድሞ ከነበረው ሐብቱ ሁሉ እጥፍ አድርጎ ሰጠው። ደግሞም፣ እግዚአብሔር ፣ ሰባት ወንድ ልጆችንና ሶስት ቆነጃጅት ሴቶችን ሰጠው። ብዙ ረዥም ዘመናትን ኖሮ ፣ የልጅ ልጆችንም አየ። ሞተም ፤ ነፍሱም ፍጹም ደስታዋን በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ አገኘች።

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት ጥያቄዎች</u>

1. ኢዮብ ምን ዓይነት ሰው ነበረ?
   ቀጥቀኛ እና እግዚአብሔርን የሚፈራ ነበረ።
2. ኢዮብ መቼ ነው የኖረው?
   በአብርሃም ዘመን ነው የኖረው

3. ሰይጣን በኢዮብ ላይ ያመጣቸው የመጀመሪያዎቹ መቅሰፍቶች ምንድናቸው?
   ያለው ሀብት ኹሉ እንዲሰረቅና እንዲጠፋ ፣ አገልጋዮቹና ልጆቹም እንዲሞቱ እግዚአብሔር ፈቀደ።
4. ሀብቱን ፣ አገልጋዮቹን እና ልጆቹን በማጣቱ ምክንያት የኢዮብ ምላሽ እንዴት ነበረ?
   ራቁቴን ከእናቴ ማህጸን ወጥቼአለሁ ፤ ራቁቴንም እመለሳለሁ። እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሳ ፣ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን።
5. ምን አይነት ጥፋት ነው በኢዮብ አስከትሎ የተከሰተው;
   ሰይጣን ኢዮብን አስከፊ በሆነ እባጭ እንዲመታው እግዚአብሔር ፈቀደ።
6. በመከራው ምክንያት ሚስቱ ኢዮብ ፣ እግዚአብሔርን እንዲሰድበው ተናግራው ነበረ። የኢዮብ ምላሽ ምንድን ነበረ?
   ኢዮብ የሚስቱን ምክር የሞኝ ምክር ብሎ ከጠራው በኃላ ፣ " ከእግዚአብሔር መልካሙን ተቀበልን ፤ ክፉውንስ አንቀበልም" ኢዮ 2፡10
7. የኢዮብ ሶስቱ ወዳጆች እኚህ ነገሮች እርሱ ላይ እንዴት እንደተከሰተ አሰቡ?
   ኀጢያት በማድረጉ ምክንያት እግዚአብሔር ቀጣው ብለው
8. የኢዮብን ሁኔታ በሚመለከት ፣ የእነሱ ግምገማ ምን ዓይነት ስህተት ነበረው?
   ሁሉም ህመም በኀጥያት ምክንያት ይሆናል ብለው በስህተት አሰቡ። በጣም አናሳ ርህራሄ በማሳየት ኢዮብን በጭካኔ ተያያዙት።
9. በድራማው ውስጥ የታዩትን ቢያንስ ኹለት የፍጥረት ድርጊቶችን ግለጥ
   እግዚአብሔር ዓለማትን ፈጠረ (የምድርን መሠረት መሠረተ) ፣ ለባሕር ገደብን ሰጠ ፤ ክዋክብትን በሰማያት ላይ አደረገ።
10. ቢያንስ ኹለት በድራማው ውስጥ ከተገለጡ መሀከል የእግዚአብሔርን የመግቦት ስራ ስም ጥቀስ
    እግዚአብሔር አየሩን ያዛል፣ እንስሳትን ይቆጣጠራል ፣ ከኃያሉን የሚጋጨውን ኩሩውን ዝቅ ያደርጋል።
11. እግዚአብሔር ሌሎቹ የኢዮብ ወዳጆች ላይ እንዳደረገው ፣ ለምንድነው ኤሊሁ ላይ ጠንካራ ትችትን ያላቀረበበት?

ኤሊሁ እውነትን ነው የተናገረው። ከሌሎቹ በተቃራኒ ፣ የኢዮብ ስቃይ የመጣው ባልተናዘዘው ኃጢያቱ ምክንያት እንደሆነ አላለም። በተጨማሪም ፣ እግዚአብሔርን ከመውቀስና በራስ ሐዘን ውስጥ ከመስጠም ይልቅ ፣ የእግዚአብሔርን ታላቅነት እንዲያስብ ግስጸታል።

12. ኢዮብ ላይ የሆነውን ሁሉ ሲቆጣጠር የነበረው ማነው?

እግዚአብሔር ኹሉን ተቆጣጥሮአል። ሰይጣን ያደረገው እግዚአብሔር የፈቀደውን ነገር ብቻ ነው።

13. ኢዮብ ላይ ይሄ ሁሉ መቅሰፍት እንዲመጣ እግዚአብሔር ለምን ፈቀደ?

እግዚአብሔር ይህ ሁሉ ስቃይ ኢዮብ ላይ እንዲመጣ የፈቀደው ኢዮብንም ኾነ ሌሎቹን ስለ ሉዓላዊነቱ ፣ ስለ ኀይሉ ፣ስለፍቅሩና እንክብካቤው እንዲማሩ ስለፈቀደ ነው።

በመዝሚያው ላይ ፣ ከእነዚህ መካከል ፣ አንድ ወይም ኹለት መዝሙር ዘምሩ። እንደ አማራጭ ፣ አንድ የዝማሬ ግጥም እንደ መዝሚያ ጸሎት አድርገህ ለማንበብ ተጠቀም።

1. “ኤልሻዳይ” ።
2. “አባት ኾይ ሕይወቴን በሙሉ አውቃለሁ” ።
3. ኦ አባቴ! አንተ ሉዓላዊ ነህ።

ክፍል ሁለት፡-

የእግዚአብሔር ዕቅድ ለዓለም ኹሉ

ምዕራፍ 2፡- እግዚአብሔር ኹሉን ፈጥሮአል።

ዓላማ ፡- እግዚአብሔር ኹሉን ነገር ከምንም እንደፈጠረ እና ሰውንም በራሱ አምሳል እንደሰራው ለማወቅ።

የእምነት መግለጫ፡- ጥያቄ፡- የፍጥረት ስራ ምንድነው?

መልስ፡- የፍጥረት ስራ ማለት እግዚአብሔር በስድስት ቀናት ውስጥ ኹሉን ነገር ከምንም አንስቶ በሐይሉ ቃል መልካም አድርጎ የሰራበት ነው።

የጥቅስ ጥናት፡- ዕብ 11፡3 “ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠሩ በእምነት እንረዳለን ፤ ስለዚህ የሚታየው ነገር የተፈጠረው ከሚታየው እንዳለሆነ እንገነዘባለን።”

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት፡- እግዚአብሔር ኹሉን ፈጠሮአል።

ዓላማ፡-

እግዚአብሔር ኸሉን ነገር ከምንም እንደፈጠረ እና ሰውንም በራሱ አምሳል እንደሰራው ለማወቅ

የእምነት መግለጫ፡-

ጥያቄ፡- የፍጥረት ስራ ምንድነው?

መልስ፡- የፍጥረት ስራ ማለት እግዚአብሔር በስድስት ቀናት ውስጥ ኹሉን ነገር ከምንም አንስቶ በሐይሉ ቃል መልካም አድርጎ የሰራበት ነው።

ጥያቄ፡- እግዚአብሔር ሰውን እንዴት ነው የሰራው?

መልስ፡- እግዚአብሔር ሰውን ወንድ እና ሴት አደርጎ ሰራው፤ በራሱ አምሳል፤ በእውቀት ፣ በጽድቅ ፣ በቅድስና እና ተፈጥሮ ላይ ባለው አገዛዝ።

መዝገበ ቃላትን ወይም ኢንተርኔትን በመጠቀም ፣ እነዚህን ቃላት ታዳጊዎቹ እንዲፈልጉአቸው ጠይቃቸው ፤ ፍጥረት ፣መልክ፣ እውቀት፣ ጽድቅ፣ ቅድስና እና አገዛዝ። እያንዳንዱን ትርጉም እንዲያነቡ ፍቀድላቸው እና በራሳቸው ቃላት የተጻፈውን ሳያዩ እንዲተረጉሙት አድርጋቸው። ተጽፎ በተቀመጠው ትርጉም እና በራሳቸው ትርጉም መሀከል ያለውን ልዩነት እንዲያዩት ንገራቸው ፤ እያንዳንዱን ቃላት በደንብ መረዳት እስኪችሉ ድረስ። በእያንዳንዱ ጊዜ የተጻፈውን ትርጉም ብቻ ሚደጋግሙት ከሆነ ፣ ሁሉንም ትርጉም ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው እንዲያነቡት አድርጋቸው እና በራሳቸው ቃል መተርጎም እንዲችሉ እዘዛቸው። በመቀጠልም ፣ የእምነት መግለጫውን ጥያቄና መልስ ደጋግመው ካነበቡት በኃላ፣ በራሳቸው ቃላት ስለፍጥጥት እንዲናገሩ ጠይቃቸው።

በመቀጠልም ፣ ታዳጊዎቹን የኹለቱን የእምነት መግለጫ ጥያቄና መልሶች በራሳቸው ቃላት መግለጥ እንዲችሉ አድርጋቸው። ቃላቶቹን በሚመለከት ባላቸው ጥሩ መረዳት ላይ በመመስረት

እንዲያሰፉት ንገራቸው። ከታች ያለው ምሳሌ የሚያሳየው ፣ ደግሞ የመጻፍ ሙከራ ምን እንደሚመስል ነው።

ጥያቄ፡- እግዚአብሔር እንዴት ነው ኹሉን የፈጠረው?

መልስ፡- እግዚአብሔር ከምንም በመነሳት ፣ ኹሉን ነገር በስድስት ቀናት ውስጥ ወደመኖር አመጣው፤ እናም በእያንዳንዱ መንገድ አጠቃላይ ፍጥረቱ አስደናቂ ነው።

ጥያቄ፡- እግዚአብሔር ሰዎችን እንዴት ፈጠረ?

መልስ፡- እግዚአብሔርን ወንድና ሴት ሰዎችን በራሱ አምሳል ፈጠረ፤ እውቀትን ሰጣቸውና በሁሉም ፍጥረት ላይ ስልጣን እንዲኖራቸው አደረገ። የሰው ልጆችን ንጹህና ኀጥያት አልባ አድረጎ ፣ እርሱን እንዲያገለግሉት ለያቸው።

<u>መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ</u>

የእምነት መግለጫው የሚደገፍበትን እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንዲፈልጉት ጠይቃቸው። ዘፍ 1፡1 “በመጀመሪያው እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ”

የፍጥረት ስራ

ዘፍ 1፡27-28 ፣ “ስለዚህ ፣ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አምሳል ፈጠረ ፣ በራሱ መልክም ፈጠረው፤ ወንድ እና ሴት አድርጎ ሰራቸው። እግዚአብሔር ባረካቸው ፤ እንዲህም አለ “ፍሬአማ ሁኑ ፣ ብዙም ። ምድርን ሙሉአት ግዙአትም። በባሕር ላይ ያለውን አሳ፣ በአየር ላይ ያለውንም አእዋፋት ፣ በምድርም ላይ የሚንቀሳቀሱትን የቱኛውንም እንስሳት ሁሉ ግዙ።”

እግዚአብሔር በራሱ አምሳል ፣ ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠረ፤ በፍጥረት ላይ ካላቸው አገዛዝ

ዘፍ 1፡31 “እግዚአብሔርም የሰራውን ኹሉ አየ ፤ ሁሉም መልካም ነበረ። እናም ፣ መሸም ነጋም ስድስተኛ ቀን።”

በስድስት ቀናት ውስጥ ፣ ኹሉም በጣም መልካም ኾነ

ነህ 9፡6 “አንተ ብቻ እግዚአብሔር ነህ። ሰማያትን ከሰማያት በላይ ያሉትን ሰማያትና የክዋክብቶችን ሰራዊት ሁሉ ፣ ምድርንና በላይዋ ያለውን ሁሉ ፣ ባሕሮችንና በውስጣቸው ያሉትን ሁሉ ፈጥረሀል። ለሁሉም ሕይወትን ትሰጣለህ፤ የሰማይ ሰራዊትም ይደግዱልሃል።”

የፍጥረት ስራ

ኢሳ 42፡5 “ሰማያትን የሰራ የዘረጋቸውም ፣ ምድርንና በውስጧ ያሉትን ሁሉ ያበጀ፣ ለሕዝቧ እስትንፋስን ፣ ለሚኖሩባትም ሕይወትን የሚሰጥ ፣ ጌታ እግዚአብሔር እንደዚህ ይላል።”

የፍጥረት ስራ.....እግዚአብሔር ሰውን ሰራ

ኤፌ 4፡24 “እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንድትለብሱ ነው”

በራሱ አምሳል....በእውቀት ፣ ጽድቅ እና ቅድስና

ቆላ 1፡16-17” ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፤ በሰማይና በምድር ያሉ ፣ የሚታዩና የማይታዩ ፣ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ሀይላት፣ ገዦች ቢሆኑ ወይም ባለስልጣናት ፣ ሁሉም ነገር በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል። እርሱ ከሁሉ በፊት ነው ፤ ሁሉም ነገር ተያይዞ የጸናው በእርሱ ነው።”

የፍጥረት ስራ

ቆላ 3፡10 “የፈጣሪውን መልክ እንዲመስል ፣ በእውቀት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል።”

በራሱ አምሳል ፣ በእውቀት

ዕብ 11፡3 “ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠሩ በእምነት እንረዳለን። ስለዚህ የሚታየው ነገር የተፈጠረው ከሚታየው እንዳልሆነ እንገነዘባለን።”

ከምንም የወጣ የእግዚአብሔር ስራ ፣ በሐይሉ ቃል

ራዕ 4፡11 “ጌታችንና አምላካችን ሆይ፣ ክብርና ሞገስ፣ ኀይልም ልትቀበል ይገባሃል። አንተ ሁሉን ፈጥረሀልና፤ በፈቃድህም ተፈጥረዋልና ፤ ሆነዋልናም።”

የፍጥረት ስራ

<u>የእምነት መግለጫ ጥያቄዎች</u>

1. ዕብ 11፡3 እና የዚህኛውን ምዕራፍ የመጀመሪያ የእምነት መግለጫ መልስ ከግምት በማስገባት ፣ የፍጥረት ስራንና ሰው የሚሰራቸውን እንደ ቤት ያሉ ነገሮችን ልዩነት እንዴት ታየዋለህ;
   እግዚአብሔር ኹሉን ነገር ከምንም ፈጠረው። በተቃራኒው ፣ የሰው ልጅ ግን አስቀድሞ በእግዚአብሔር የፍጥረት ስራ ውስት አስቀድሞ የነበሩ ነገሮችን ተጠቅሞ ነው የሚሰራው።
2. ይሕ የፍጥረት ስራ ስለእግዚአብሔር ምን ይናገራል?
   እግዚአብሔር ከምንም አስቀድሞ ይኖር ነበረ። አሁንም ፣ ከፍጥረት ስራው በልዩነት ይኖራል።
3. የዚህን ምዕራፍ የመጀመሪያ የእምነት መግለጫ እና መዝ 33፡9ን ከግምት በማስገባት ፣ በእግዚአብሔር የፍጥረት ስራ እና በሰው ልጆች ስራ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
   እግዚአብሔር ዝም ብሎ ይናገርና ፣ “የኀይሉ ቃል” ነገሮችን ወደ መኖር ያመጣል። እግዚአብሔር ትዕዛዝ ባወጣበት ቅጽበት የሌሉ ነገሮች ወደመኖር ይመጣሉ። በተቃራኒው ፣ የሰው ልጅ አንድን ነገር ለመስራት ጊዜ ያስፈልገዋል። ተናግሮ ነገሮችን ወደ መኖር ለማምጣት ኃይል አልባ ነው።
4. “በስድስት ቀናት ውስጥ” ማለት ምን ማለት ?

   የዚህ ሀረግ ተፈጥሮአዊ አነባበብ የሚያሳየው ፣ በስድስት ተከታታይ 24 ሰዐት ጊዜአት ውስጥ እንደፈጠረው ነው ። ብዙ ክርስቲያኖች ይህንን አይነት አፈታት ነው የያዙት ። ነገር ግን ፣ ሌሎች ክርስቲያኖች “ቀን” የሚለውን ቃል የሚረዱት ረዥም የጊዜ ስፋት ያለው እንደሆነ አድርገው ነው (መዝ 90 ፣4 እና 2ኛ ጴጥ 3፡8 ላይ በመመስረት)። ምንም እንኳን ክርስቲያኖች በዚህ ነጥብ ላይ ቢለያዩም ፣ ኹሉም እግዚአብሔር ፍጥረትን ኹሉ መስራቱንና ከፈጣሪነት ኀይሉ ተነጥሎ የሚታይ አንዳች ነገር እንደሌለ ያምናሉ።

5. ተሰርቶ ስላለቀው የእግዚአብሔር የፍጥረት ስራ መለኪይ ምን ታውቃለህ?
   በጣም መልካም ነበረ (ዘፍ 1፡31) ። "በጣም ጥሩ" የሚለው ቃል የሚያሳየው ፣ ውበት ፣ ተመጋግቦተና ፍጽምና።
6. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፣ እግዚአብሔር ሰዎችን ለመፍጠር ከፍተኛ ትኩረት የሰጠው ለምንድነው?
   ኹሉም የእግዚአብሔር ፍጥረት ኹለንተናዊ ዓለማውን የሚያሳካው ፣ በሰው ልጆች አገዛዝ ስር ነው። እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በራሱ አምሳል ፈጠረና ፣ ምድርን እንዲያስተዳድርና የተቀረውን ፍጥረት ኹሉ እንዲገዛ አዘዘው (ዘፍ 1፡26 -28)። ፍጥረት ያለ እግዚአብሔር ማለት ያለካፒቴኑ እንደሚሔድ ትልቅ መርከብ ነው።

7. *"በፍጥረት ኹሉ ላይ እንዲገዛ" ማለት ምን ማለት ነው?*

እዚህጋ ፍጥረት የሚለው ቃል የሚያሳየው ከእንስሳቱ የሚያልፍ ነገር ነው። በሰው አገዛዝ ስር ላለ አጠቃላይ ነገር ሊውል የሚቸል ቃል ነው። በፍጥረት ጅማሬ እግዚአብሔር የሰው ልጅን ፣ እንዲገዛና አጠቃላዩን ምድር እንዲያስተዳድር አዘዘው (ዘፍ 1፡28) ። የሰው ልጅ በሳይንሳዊ ፣ ኪነጥበባዊና በንግድ መንገድ አድርጎ አንዳንድ ነገሮችን ሲፈጥር እና ሲያገኝ ፣ ይሔንን ትዕዛዝ አሳክቶአል (መዝ 8፡5-8)።

8 . ዘፍ 2፡19 -20 እንደሚለው ፣ ለእግዚአብሔር ባለው መታዘዝ ፣ ለተፈጠሩ ነገሮች ስምን አወጣላቸው። እንዴት አይነት የኾነን የእግዚአብሔር አይነት ችሎታን ነው አዳም ያሳየው?

እግዚአብሔር በሁሉም ፍጥረት ላይ ይነግሳል። በተመሳሳይ መልኩ፣ አዳም በፍጥረት ላይ ያለውን አገዛዝ በመለማመድ እንደ እግዚአብሔር ይሰራል። ዘፍ 1፡26 እና 28 ን ይመልከቱ።

9 . ዘፍ 1፡27 እንደሚለው ፣ "እግዚአብሔር በራሱ አምሳል ሰውን ፈጠረ" ይሄ ማለት ምንድነው?

እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነፍስን ሰጠህ ፤ በተወሰነ መልኩ ፣ እንደ እግዚአብሔር የማሰብ ፣ የመሰማትና የማድረግን ችሎታ አግኝተሃል። ነፍስህና እንደ እግዚአብሔር አይነቱ ችሎታህ ከእንስሳት ይለይሃል።

10 . የሰው ልጅ አሁንም የእግዚአብሔር አምሳል አለው?

አዎ! የአንተ ዘላለማዊ ነፍስህ የእግዚአብሔርን ባሕሪይ ያንጸባርቃል። ነገር ግን ይሄ ነገር ፍጹም አይደለም ፤ የሰው ልጅ የኃጢያት ውድቀት ውስጥህ ያለውን የእግዚአብሔርን አምሳል አበላሽቶታል።

11 . መክ 7:29 ላይ በመመስረት ፣ እግዚአብሔር የሰው ልጅን እንዴት ነው የፈጠረው?

"ይሄንን ብቻ አገኘሁ ፤ እግዚአብሔር ሰውን ቀጥተኛ አድርጎ ፈጠረው ፤ ሰው ግን ብዙ ነገሮችን በማድረግ ጠፋ" እግዚአብሔር አዳምን ቀጥተኛ እና ንጹህ አልባ አድርጎ ሰራው። ነገር ግን እርሱ በእግዚአብሔር ላይ አመጸ።

12. በዘፍ 2:23 መሠረት አዳም ሔዋንን ለምንድነው "ሴት" ብሎ የጠራት; በዘፍ 3:20 መሰረትስ "ሔዋን" ብሎ ለምን ጠራት?

አዳም ሴት ብሎ የጠራት ፣ የአዳምን አንድ አጥንት በመጠቀም ፣ ከእርሱ አውጥቶ ስለሰራት ነው። ሔዋን ብሎ የጠራት ደግሞ ፣ የሰው ልጆች እናት በመሆኗና ወደ ፊት ለሚመጡ ሰዎች ሁሉ ሳይቀር ምንጭ በመሆኗ ነው።

13 . እግዚአብሔር ሁሉን መፍጠሩን መረዳት ለምን ይጠቅማል?

መጽሐፍ ቅዱስ ስለፍጥረት የሚናገረውን ከመረዳት መጉደል፣ ስለሌሎች የቃሉ ትምሕርት ያለንን መረዳት ወደ ጥርጣሬና ወደ ግራ መጋባት የሚመራ ነገር ነው። እንደ ራሱ የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስም በእያንዳንዱ በሚናገረው ነገር ላይ የሚታመን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ሚናገረው እግዚአብሔር ሁሉን ነገር አልፈጠረም ብለው ሰዎች የሚያምኑት ሃቅ ሊያስደንቃቸሁ አይገባም። የእግዚአብሔርን ቃል ሙሉ በሙሉ ማመናቹ ከየትኛውም አይነት ህጸጽ እና ስህተት ያድናችኃል።

የጥቅስ ጥናት

ዕብ 11:3 "ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተፈጠሩ ፣ በእምነት እንረዳለን ፤ ስለዚህ የሚታየው ነገር የተፈጠረው ከሚታየው እንዳልሆነ እንገነዘባለን።"

አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ከሳይንስ ጋ እንደሚጋጭ እና በአመክንዮአዊ መንገድ ሁለቱንም መቀበል እንደማይቻል ይናገራሉ። ነገር ግን ይሔ እውነት አይደለም። ሳይንስ በምርምርና በምልከታ የሚሆን፣ ስልታዊ የእውቀት ፍለጋ ነው። የቱኛውም አይነት ሳይንሳዊ ምርምር እና ምልከታ የመጽሐፍ ቅዱስን የፍጥረት ዘገባ ውድቅ ሊያደርግ አልቻለም።

በተመሰሰይ መልኩ ፣ የተኛውም ምርምርና ምልከታ ፣ የፍጥረትን ዘላለማዊ ኦባሬ ወይም የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሃሳብ እንደሚያሳየው ደግሞ ፣ የፍጥረትን በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ያለውን ልውጠት የሚያረጋግጥ ኾኖ አልተገኘም። ግጭት ይፈጠር ይኾናል ፣ ነገር ግን ፣ ይሔ የሚሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ ዘገባ እና በዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሀሳብ መካከል ነው። በዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሀሳብ የሚየምኑ ሰዎች ይሄንን የሚያምኑት ፣ ቁስ አካል ዘላለማዊ እንደሆነ ስለሚያምኑ እና እርስ በእርሳቸው የማይስማሙበት ቢሆንም ፣ በቢሊዮን አመታት ሂደት ፣ አሁን ወደ ደረሰበት እንደመጣ ስለሚያስቡ ነው። ይሔ እምነት የተጀመረው እግዚአብሔርን እንደ ፈጣሪ ለማሰብ ባልፈለገ ንጽረተ ዓለም እና ለማብራራትም የሚፈልገው የተፈጠረው ነገር ሁሉ የተፈጠረው ፣ ያለ አስደናቂ እቅድ ፣ እገዛ እና ዓላማ እንደሆነ በማመን ነው።

ዝግመተ ለውጥ የሚናገረው ፣ ቁስ አካል ፣ ከጥንተ ዘላለም እንደተጀመረ እና ያለምንም አስደናቂ ኃይል እና ቅንብር ፣ ራሱን ዛሬ ወዳለበት ሁኔታ እንዳሸጋገረ ነው። የጥቅስ ጥናቱ ከዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሀሳብጋር የሚጋጭ ነው። እርሱ የሚናገረው " እግዚአብሔር ዓለማትን ካለመኖር ወደመኖር በትዕዛዝ ማምጣቱን ነው"። ዝግመተ ለውጥና መጽሐፍ ቅዱስ ኹለቱም እኩል ትክክል ሊሆኑ አይችሉም። ሰዎች እምነታቸውን ምን ላይ ማድረግ እንዳለባቸው ራሳቸው መምረጥ አለባቸው። የመጀመሪያው የዘፍጥረት መጽሐፍ የሚያብራራው ፣ የስድስቱን ቀን የፍጥረትን ስራ እና ፍጥረት እንዴት እንደመጣ ለማሳየት ፣ "እግዚአብሔር እንዲ አለ" የሚለውን ሐረግ በተደጋጋሚ በመጠቀም ነው። ፍጥረት የመጠው፣ ከእግዚአብሔር ንይለኛ ቃል የተነሳ ነው ፤ እርሱ ኹሉን ነገር ተናግሮ ወደ መኖር አመጣው። ለምሳሌ ፣ በመጀመሪያው ቀን ፣ እግዚአብሔር ብርሃን ይኹን አለ ፤ ብርሃንም ኾነ (ዘፍ 1:3)። ፍጥረት እንዴት እንደተከሰተ አድምጥ ፤ " በጌታ ቃል ሰማያት ኹሉ ተሰሩ ፤ ከአፉም እስትንፋስ የክዋክብት ሰራዊት.....እርሱ ተናግሮአልና ኾኑ ፤ አዝዞአልና ጸኑ።" (መዝ 33:6 እና 9)

ዘፍ 1፣ መዝ 33 እና የጥቅስ ጥናቱ እንደሚናገረው ፣ እግዚአብሔር በ6ቱ ቀናት ውስጥ ካደረገው ፣ ሕይወት አልባ ነገሮችን ከማዘዝና ተፈጥሮአዊ ኃይላትን ከማቀናጀት በተጨማሪ ብዙ እንዳደረገ ነው። እንደፍጥረት ጌታ ፣ ዓለማትን ከምንም ወደመኖር አምጥቶአል። ነገሮች እንዲከሰቱ ፣ አውጆ ሆኖለታል። የእግዚአብሔር ቃል የሚያሳየው በፍጥረት ውስጥ የተገለጠውን የእርሱን አስደናቂ ቃል ነው። ያዘዘው ኹሉ ይኾናል። ስለፍጥረት

መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ላይ በመመስረት ፣ ኹሉን ቻዩ ሲናገር መስማት የለብህም; ከምንም አንስቶ ኹሉን የመፍጠሩን እውነት ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ሐይል አማካይነት አንተን እንዲያሳምንህ ጸልይ።

<u>የጥቅስ ጥናት ጥያቄዎች</u>

1. እግዚአብሔር ኹሉን ከምንም የመፍጠሩን እውነታ ለመገንዘብ ፣ ምን ሊኖርህ ይገባል?
   በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሚኾን እምነትን ሊኖርህ ይገባል።
2. የጥቅስ ጥናቱ የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሐሳብን የሚቃረን ነው?
   አዎ! መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ፣ ዕብ 11:3 ላይ እግዚብሔር ዓለማትን መደመኖር እንዲመጡ አዘዘ ፣ ሆነም። የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሐሳብ እንደሚናገረው ፣ ዓለማት ለዘላለም ይኖር ከነበረ ቁስ አካል በልውጠት የተገኙ አይደሉም።
3. የመጽሐፍ ቅዱስ የፍጥረት አተያይ ከሳይንስ ጋር የሚጋጭ ነው?
   በፍጹም! ነገር ግን ፣ ከዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሐሳብጋ ይጋጫል። ወይም ፣ የቱኛውም ንጽረተ ዓለም ከእግዚአብሔር ነው የሚጀምረው።

   <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት ፡ እግዚአብሔር ኹሉን ነገር ፈጥሮአል።</u>

   ታዋቂው እንግሊዛዊ የሒሳብና የፊዚክስ ሊቁ ፣ ክቡር አይዛክ ኒውተን እግዚአብሔር አለማትን እንደሰራ ያምናል። ኒውተን የእንቅስቃሴና የስበት ሒሳባዊ ሕግጋትን የፈጠረው ፣ የፍጥረት ታሪክ ሲያጠና ነበረ። እነዚህ ህግጋት የሚያብራሩት ፣ ፕላኔቶችና ሌሎች ሰማያዊ አካላት በእግዚአብሔር አለም ውስጥ እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ ሲሆን ይህም ግኝት በወቅቱ ከነበሩ ሳይንሳዊ ግኝቶች ኹሉ ትልቁ ኾኖ ተመዝግቦ አልፎአል። የሚከተለው ፣ የኒውተን ኢ አማኒያን ጓደኛው ታሪክ ምንአልባት ተረት ይሖናል። ቢኾንም ፣ ይሄ የሚያብራራው ፣ እንድ ወጥ የሆነው መልክ የሌለው ቁስ አካል ራሱን ወደ አስደናቂ ቅርጽ ወዳለው ኦባሬ

ለውጦአል የሚለውን የአብዛኛውን የስነ ልውጠት አቀንቃኝ የሐሳብ ግጭት ነው።

ኒውተን ፣ በጣም በተዋበና በተጠበበ ሁኔታ የተሰራ የሚታየውን የጸሐይ ስርዓት የሚመስል ቅርጽ ያለው ሞዴል ለመስራት አሰበ ፤ ይሄም ሲያልቅ መኖሪያ ቤቱ ውስጥ የሚያስቀምጠው እንደሆነ አቅዶ ነበረ። ያሰበውን ካሳካ በኃላ በትልቁ ጠረጴዛ ላይ ተክሎ አስቀመጠው። ሰራተኛው የሰራው ሞዴል፣ በጣም የሚያስደንቅና ፣ የፕላኔቶቹን የተለያየ ቅርጽ የሚመስልና እርስ በርሳቸው ያላቸውን ቅርበት የሚወክል ብቻ አይደለም ፤ ነገር ግን ፣ እሽክርክሪቱ ሲዞር ፣ በምሕዋሩ ላይ የሚንቀሳቀሱትን ኹሉ ጨምሮ ነበረ የሰራው። በጣም አስደማሚና ለማሰብ ኹሉ የሚከብድ ገራሚ ስራ ነበረ ፤ በተለይም በሳይንስ ትምሕርት ቤት ውስጥ ለሚማሩ ሰዎች አስደናቂ ነበረ።

ይሔ በእንዲህ እንዳለ የኒውተን ኢአማኒና ሳይንስ የሚያጠና ጓደኛው አንድ ቀን ሊጎበኘው መጣ። የተሰራውን ሞዴል በመመልከት ፣ ግልጽ የኾነ አድናቆቱን መግለጽ ጀመረ ፤ “ኦ! ምን አይነት አስደናቂ ስራ ነው;” በጣም ተደነቀ። “ማነው የሰራው;” ወደጠያቂው በለሆሳስ እየተመለከተ ፣ አይዛክ “ ማንም አልሰራውም” ብሎ መለሰለት። ምርመራውን በመተው ፣ ጎብኚው ፊቱን አዞረ እና እንዲህ አለው። “በእርግጠኝነት ጥያቄዬን አልተረዳኸውም። ይሔንን የሰራው ማነው;” ኒውተንም ፣ ያለጥርጣሬ መሆኑን በደስታ በመግለጽ ፣ ጠንከር ባለድምጸት መመለሱን ቀጠለ “ ማንም አልኩን እኮ! የምትመለከተው ነገር አሁን ያለውን ቅርጽ የያዘው በራሱ ነው።” ጎብኚው ፣ በቁጣ እንዲህ አለ “ ሞኝ እንደሆንኩ ነው የምታስበው ፤ “ እርግጠኛ ነኝ አንድ ሰው ሰርቶታል ፣ እናም እርሱ በጣም ጎበዝ ነው ፤ ማን እንደሆነም እኔ ላውቀው እፈልጋለሁ።” ኒውተንም ከዚያ በኃላ ጠንከር ባለ ግን በጨዋ ቃል ይመልስለት ጀመረ። “ ይህች ነገር ፣ በጣም ትልቅ ለሆነው ህግጋቱንም ለምታውቀው ስርዓት

ትንሽዬ ተምሳሌት ናት፤ ይህቺ ትንሽዬ ስራ ያለ ንድፍ አውጭና ያለ ሰሪ የሆነች ናት ብዬ አንተን ላሳምንህ አልችልም። ነገር ግን ይህች ትንሽዬ ሞድ ልትመስለው የሞከረችው ግዙፉ ፍጥረተ ዓለም ያለንድፍ ዓውጪ እና ያለ ሰሪ እንደመጣ አድርገህ ነው የምታስበው። አሁን አስኪ ንገረኝ ፤ በምን አይነት ማብራሪያ ነው እንዲህ የማይመስል ድምዳሜ ላይ የደረስከው (Marshall and Sandra Hall, The Truth: God or Evolution? (Baker Book House: Grand Rapids, MI, 1974) as quoted in Creation Wiki, creationwiki.org/Isaac Newton, February 17, 2016.)

ልክ እንደ ክቡር አይዛክ ኒውተን ኹሉ ፣ ሌሎችም ባለፉት ዘመናት የኖሩ ታላላቅ ሳይንቲስቶች በዘፍጥረት የፍጥረት ትረካ ያምናሉ። ስለስድስቱ ቀናት የፍጥረት ትረካ እና በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር ምን እንደሰራ እንዲያነቡ ታዳጊዎቹን መጸሐፍ ቅዱሳቸውን ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ላይ እንዲከፍቱት እና እንዲያነቡት ጠይቃቸው።

<u>የፍጥረት የመጀመሪያ ቀን</u>

ዘፍ 1፡1 -2 ፣ “በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ፤ ምድርም ባዶ እና ቅርጽ አልባ ነበረች ፤ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ ። የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሐ ላይ ሰፍፎ ነበረ።” ከዝግመተ ለውጣዊ ንድፈ ሀሳብ ባለ ቀጥተኛ ተቃርኖ ፣ ዘፍጥረት እግዚአብሔር ዘላለማዊ እንደሆነ ያስቀምጣል።” በፍጥረት ጅማሮ ፣ እርሱ አስቀድሞ ነበረ ፤ በእርግጥ ከጥንተ ዘላለም አስቀድሞ ኖሮአል። እግዚአብሔር ሲኖር ፣ ጊዜ አልነበረም። በእርግጥ እግዚአብሔር የቁስ አካላትን ጥቃቅን በገሮች ፈጥሮ በራሳቸው በራሳቸው እየተለወጡ እንዲያድጉ አላደረጋቸውም። ይልቁን ፣ እግዚአብሔር ፣ መደበኛ ያልሆነ ውስብስብ ቁስ አካላትን ፈጥሮአል ፤ ሰማያት ፣ ምድር ፣ እናም ኃላ ላይ የሉት ምዕራፎች እንደሚያሳዩት ፣ በምድር ላይ ያሉትን ኹሉንም ፍጥረታት።

እነዚህ ክፍላት ፣ በመለኮት ውስጥ ያሉ ሶስቱም አካላት ኹሉንም ነገር ለመፍጠር በአንድነት እንደሰሩ የሚያሳይ

የመጀመሪያ ምልክት ነው። ብዙ ሰዎች ከፍጥረት ስራ ጋ በአንድነት የሚያዩት እግዚአብሔር አብን ብቻ ነው። ነገር ግን ፣ በፍጥረት መጀመሪያ የምናገኘው ፣ ኤሎሂም የሚለው የእግዚአብሔር ስም የሚያሳየው ብዙነትን ነው። ምንም እንኳን ፣ የዘፍጥረት መክፈቻ ምዕራፍ ስለ እግዚአብሔር ወልድ በግልጥ የሚጠቁም ባይሆንም ፣ ዩሐ 1፡3 እንደሚናገረው ፣ ቃለ አስደናቂ የፍጥረት ኃይሉን መጠቀሙን ነው። “በእርሱ በኩል (በቃል) ሁሉም ነገር ተፈጥሮአል፤ ከእርሱ በቀር ከተፈጠረው ነገር ኹሉ አንዳች አልሆነም።” ዩሐ 1፡14 እንደሚያሳየው ፣ ቃል ስጋ ሆነ ፤ በሰዎች መካከልም አደረ ። ስለዚህ ቃሉ ኢየሱስ ነበረ። (ቆላ 1፡16ን ይመልከቱ)። በቁጥር ኹለት ላይ ደገሞ ፣ መንፈስ ቅዱስ በውሃው ላይ ሰፍፎ እንደነበረ ይናገራል ፤ ይሔም የሚከላከል ፣ የሚጠነቀቅና በክብካቤ የሚጠብቅ መሆኑን ያሳያል። ስለዚህም ፣ ኃያሉ ስሉስ አሃዱ አምላክ ሰማያትንና ምድርን ኸሉ ፈጠረ።

ዘፍ 1፡3- 5 እንደሚያሳየው፣ “እግዚአብሔርም ፣ ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃንም ሆነ። እግዚአብሔር ብርሃኑ መልካም እንደሆነ አየ ፣ እግዚአብሔር ብርሃንና ጨለማን ለየ ። እግዚአብሔር ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው ፣ ጨለማውንም ሌሊት አለው። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ፣ አንድ ቀን።”

እነዚህ ቁጥሮች የሚያሳዩት የእግዚአብሔርን አስደናቂ የሐነውን የመፍጠር ኃይሉን ነው። እርሱ ተናገር ፤ ከዚያም ነገሮችም ሆኑ። ብርሃንን ጠራ ፣ ብርሃኑም መጣ። በተጨማሪም ፣ ልክ እንደሌሎቹ እግዚአብሔር እንደሰራቸው ፍጥረታት ብርሃኑ መልካም ነበረ (1ኛ ጢሞ 4፡4) ። ከዚያም ፣ በሁሉም ስፍራ እንዳይሐን ብርሃንን ለየው ፤ ሁሉንም ሳይሆን፣ አንዳንድ ክፍሎችን እንዲገልጥ። ጸሐይና ጨረቃን እንደ ብርሃን ምንጭ አድርጎ እግዚአብሔር አልፈጠረም ነበር ፤ እነርሱን በአራተኛው ቀን ሰራቸው። በመጀመሪያው ቀን ፣ በኃላ ላይ በተከሰቱ የብርሃን ምንጮች ሳይሆን ፣ በእግዚአብሔር በራሱ ትዕዛዝ ፣ ብርሃን ወደ ፈነጠቀ። የኋለኛ ቁጥሮቹን ለመጠቅለል ፣ እግዚአብሔር ተናገረ ፣

ብርሃንም ኾነ፣ እግዚአብሔር ዳግም ተናገረ ፣ ብርሃን ራሱን ለየ፣ የመጀመሪያው ቀን አለቀ።

<u>የኹለተኛው ቀን ፍጥረት</u>

ዘፍ 1፡6-8 ፣ “እግዚአብሔርም ፣ በውኆች መካከል ጠፈር ይሁን ፣ በውሃና በውሃ መካከልም ይክፈል አለ። እግዚአብሔርም ጠፈርን አደረገ፣ ከጠፈር በታችና ከጠፈር በላይ ያሉትንም ውኆች ለየ ፤ እንዲሁም ሆነ። እግዚአብሔር ጠፈርን ሰማይ ብሎ ጠራው። ማታም ሆነ ፣ ሁለተኛ ቀን።”

ከመጀመሪያው የፍጥረት ቀን በኃላ ፣ ውኃ አጠቃላይ መሬትን ሸፈነ። በሁለተኛውም ቀን እግዚአብሔር ጠፈርን ወይም ሰማይን ውሃን እንዲለይ አድርጎ ሰራው። የተወሰነው የውኃ አካል ከከባቢ አየር በታች እንዲቀር አደረግው። እስከ ሶስተኛው ቀን ድረስ ፣ የብስ አልተፈጠረም ነበረና ፣ ውሃው መሬትን እንዲሸፍን አደረገው። እግዚአብሔር የተቀረውን የውኃ አካል ከከባቢ አየር በላይ እንዲሆን አደረገው፤ ምንአልባት የዝናብ ደመና እንዲሆን እየሰራው ይሆናል። እግዚአብሔር ተናግሮ በመጀመሪያው ቀን ብርሃንን ከጨለማ እንደለየው ኹሉ ፣ በዚህ ኹለተኛ ቀንም እግዚአብሔር ተናግሮ ፣ ውኃን ለሁለት ከፍሎታል።

<u>የፍጥረት ሶስተኛ ቀን</u>

ዘፍ 1፡9 -10 ፣ “እግዚአብሔርም ከሰማይ በታች ያለው ውኃ በአንድ ስፍራ ይሰብሰብ፣ የብሱም ይገለጥ አለ፤ እንዲሁም ሆነ። እግዚአብሔርም የብሱን ምድር ብሎ ጠራው። የውኃ መከማቻውንም ባሕር አለው፤ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ።”

እግዚአብሔር ሁሉንም የውኃ አካል ከከባቢ አየር በታች ሰበሰበው ፤ በዚህም ምክንያት ሁሉንም የምድር ክፍል መሸፈኑ ቀረ። ምንአልባት መሬትን የሚያንቀጠቅጥ ረብሻ ፈጥሮአል ፤ ይሄም ተራሮችን ወዳለይ የሚገፋ እና ውኃ ወደ ስር እንዲፈስ የሚያደርግ ነው። እግዚአብሔር እነዴት እንደሰራው ከሚያሳየው እውነታ በዘለለ ፣

የውኃው መሰብሰብ ባሕሩን እና ደረቁን የብስ ለይቱአል።

ዘፍ 1፡11-13 *"እግዚአብሔርም ፦ ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ ፤ እንዲሁም ሆነ። ምድር ዘርን የሚሰጥ ሳርንና ቡቃያን እንደ ወገኑ ዘሩም ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እንደ ወገኑ አበቀለች። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ ፣ ሶስተኛ ቀን"*

እንደየወገኑ ሲል ኹለት ነገሮችን ያሳያል። የመጀመሪያው ፣ ዘሮች የሚራቡት እንደ የወገናቸው ነው። የአፕል ዘር ሁልጊዜ የሚያመርተው አፕልን ነው ፤ የቲማቲም ዘር ሁልዚሄ የሚያመርተው ቲማቲምን ነው። ነገር ግን ፣ ልዩነቶች እንደ የወገኑ የሚኾኑ ቢሆንም ፣ ሰዎች ሁሉንም አይነት የአፕልና የቲማቲም ዝርያ ያጣጥማሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር ስነ ሕይወታዊ ክልልን አስምሮአል ፤ ስለዚህም ሕይወት ያለቸው ነገሮች ከራሳቸው ወገን ውጪ ለውጥ ሊያካሂዱ አይችሉም። ኹለተኛ፣ የቱኛውም ዘር ከእግዚአብሔር የፍጥረት ስራ እና ንድፍ ውጭ መሆን አይችልም። እግዚአብሔር እስካሁን ድረስ የነበሩትንም ሆነ አሁን ያሉትን ዘሮች በአጠቃላይ በሶስተኛው ቀን የሰራቸው ናቸው።

<u>የአራተኛው ቀን ፍጥረት</u>

ዘፍ 1፡14-16 *"እግዚአብሔርም አለ ፣ ቀንና ሌሊትን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ ለምልክቶች ለዘመኖች ለዕለታት ለአመታትም ይሁኑ፤ በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር ብርሃናት ይሁኑ ፤ እንዲሁም ሆነ። እግዚአብሔርም ሁለት ታላላቆች ብርሃናትን አደረገ ትልቁ ብርሃን በቀን እንዲሰለጥን ፣ ትንሹም ብርሃን በሌሊት እንዲሰለጥን ክዋክብትንም ደግሞ አደረገ።"*

እግዚአብሔር ሁለት ታላላቅ ብርሃናትን አደረገ ፤ ጸሐዩ በቀን እንዲሰለጥንና ጨረቃ በሌሊት እንዲሰለጥን። እነዚህ ልዕለ ተፈጥሮአዊ አካላት ፣ ወቅቶች ፣ ቀናቶችና አመታት እንዲፈራረቁ በማድረግ ሰዎችን ያግዛሉ። ወቅቶችን በሚመለከት፣ እግዚአብሔር የመሬትን መዘውር ፣ ከጸሐይ ምሕዋርጋር እንዳይገጥም አድርጎአል። ስለዚህም ፣ መሬት በጸሐይ ዙሪያ ስትዞር፣ በክረምቱ ወቅት ፣ የሰሜኑ ንፍቀ ክበብ ለጸሐይ የቀረበ ይሆንና በበጋው ወቅት ደግሞ ለጸሐይ የቀረበ ይሆናል፤ ይሔው

ተመሳሳይ ነገር ለደቡቡም ንፍቀ ክበብ የሚሰራ ነው። እንደቀናቶቹ ኹሉ ፣ እግዚአብሔር መሬትን በራሱ መዘውር ላይ በማድረግ ፣ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ሕይወት ላለው ነገር ሁሉ አንድ ቀንና አንድ ማታን ይሰጣል። አመታትን በሚመለከት ደግሞ ፣ እግዚአብሔር ምድርን በጸሐይ ዙሪያ እንድትዞር አድርጎ፣ አንድ የመሬት ዙረት ሙሉ አንድ አመት እንዲፈጅ አድርጎአል።

ዘፍ 1፡16-19፡- *"ክዋክብትንም ደግሞ አደረገ። እግዚአብሔርም በምድር ላይ ያበሩ ዘንድ በሰማይ ጠፈር ላይ አኖራቸው፤ በቀንም በለሊትም እንዲሰለጥኑ ፣ ብርሃንና ጨለማንም እንዲለዩ፤ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ። ማታም ሆነ ጠዋትም ሆነ አራተኛ ቀን።*

በጥንት ዘመን ይኖሩ የነበሩ አህዛቦች ፣ ከአማልክቶቻቸው መሀከል ፣ ክዋክብትን የመቁጠር ባሕል ነበራቸው ፤ ክዋክብት ፣የሰው ልጆችን ዕጣ ፈንታና የአለማትን ጉዳይ ይቆጣጠራሉ ብለው ያምኑ ስለነበረ ነው። ዛሬ እንኳን ሳይቀር አስትሮሎጂስቶች እንደሚሉት ፣ የክዋክብት እንቅስቃሴና ቦታ እንዲሁም ሌሎች ልዕለ ተፈጥሮአዊ አካላት የፍጥረትን ወደፊት ይቆጣጠራሉ። እነዚህ ሁሉ ስሜት የማይሰጡ አስተሳሰቦች ፣ ክዋክብት ከእግዚአብሔር የፍጥረት ስራ የተለዩ ናቸው ብሎ ከሚያስብ አስተሳሰብ የወጡ ናቸው። በዘፍጥረት መጽሐፍ መሠረት፣ እግዚአብሔር ክዋክብትን ለሰው ልጆች ጥቅም ሲል ነው የሰራው።

<u>አምስተኛው የፍጥረት ቀን</u>

ዘፍጥረት 1፡20-23 *"እግዚአብሔርም አለ ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ ፣ ወፎችም ከምድር በላይ ከሰማይ ጠፈር በታች ይብረሩ። እግዚአብሔርም ታላላቆች አንበሪዎችን ፣ ውኃይቱ እንደ ወገኑ ያስገኝቻቸውንም ተንቀሳቃሾቹን ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ ፣ እንደ ወገኑ የሚበሩትን ወፎች ሁሉ ፈጠረ፤ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ። እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ ባረካቸው ፣ ብዙ ተባዙ የባሕርንም ውኃ ሙሏት ፤ ወፎችም በምድር ላይ ይብዙ። ማታም ሆነ ጠዋትም ሆነ አምስተኛ ቀን"*

እግዚአብሔር ባባሕር ፣ በወንዝና በምንጮች ውስጥ እንዲንቀሳቀሱ አሳዎችን ፣ አሳ ነባሪዎችንና በውኃ ላይ የሚንቀሳቀሱትን እንስሳት ሁሉ ፈጠራቸው። በተመሳሳይ ቀንም ፣ አየሩ ላይ እንዲበሩ አዕዋፋትን ፈጠራቸው። እግዚአብሔር እነዚህ እንስሳት እንዲራቡ ፣ ሰማይና ውኆችን ሁሉ እንዲሞሉ አዘዛቸው ፤ ነገር ግን ይሄንን ያደረገው እንደየወገናቸው እንዲሆኑ ነው። ዛሬ ምድር ፣ እግዚአብሔር

በአምስተኛው ቀን፣ በስልጣን ቃሉ በፈጠራቸው በውኃ በሚንቀሳቀሱና በአየር በሚበሩ ፍጥረታት ተሞልታለች።

<u>የፍጥረት ስድስተኛ ቀን</u>

እግዚአብሔርም "ምድር ሕያዋን ፍጡራንን እንየወገናቸው ፣ ከብቶችን በምድር ላይ የሚሳቡ ፍጡራንና የዱር እንስሳትን እያንዳንዱን እንደየወገኑ ታስገኝ" አለ ፤ እንዳለውም ሆነ። እግዚአብሔርም የዱር እንስሳትን እንደየወገናቸው ፣ እንዲሁም በምድር ላይ የሚሳቡ ፍጡራንን እንደየወገናቸው አደረገ። እግዚአብሔርም ይሄ መልካም እንደሆነ አየ።

እግዚአብሔር አጥቢዎችን ፣ ተሳቢዎችን፣ ነፍሳትንና ሌሎች እንስሳትን በደረቁ ምድር ላይ እንዲሆነ አደረገ። እንደ እጽዋቱ ፣ አሶችና አዕዋፋት እነዚህ በምድር ላይ ያሉ ፍጥረታት በየራሳቸው ወገን እንዲራቡ አደረጋቸው። አግዚአብሔር እነዚህ እንስሳት መልካም እንዲሆኑ አደረጋቸው ፤ ነገር ግን በማስከተል የፈጠረው ነገር ከዚህ የተሻለ ነበረ።

ዘፍ 1:26-27 "እግዚአብሔርም "ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአችን እንሥራ ፤ በባሕር ዓሦች ፣ በሰማይ ወፎች ፣ በከብቶች ፣ በምድር ሁሉ ላይ ፣ እንዲሁም በምድር በሚሳቡ ፍጡራን ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራቸው" አለ። ስለዚህ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ ፈጠረው ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።

እግዚአብሔር የሰው ዘርን ሁሉ በራሱ አምሳል ፈጠረው ፤ ሲፈጥረውም ፣በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ ሕያውና ዘላለማዊ ነፍስን በማድረግ ነው። አንዳንድ ባሕሎችና ሐይማኖቶች ሴቶችን ከወንዶች ያነሱ አድርገው ያዩአቸዋል። ነገር መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው፣ እግዚአብሔር ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን በራሱ አምሳል እንደፈጠራቸው ነው። ይሔም ማለት ፣ በተወሰነ መልኩ ፣ ሰዎች ፣ ሌሎች ፍጥረታቸው የሌላቸውን አይነት እንደ እግዚአብሔር የማሰብ ፣ የመሰማትና የማድረግ ችሎታ አላቸው።

ዘፍ 1:28-30 *"ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት ግዟትም ፤ የባሕር ዓሶች የሰማይ ወፎች እንዲሁም በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሕያዋን ፍጡራንን ሁሉ ግዟቸው " ብሎ ባረካቸው። እግዚአብሔርም እንዲህ አለ "በምድር ላይ ያሉትን ዘር የሚሰጡ ተክሎችን ሁሉ ፤ በፍሬአቸው ውስጥ ዘር ያለባቸውን ዛፎች ሁሉ ምግብ ይሆኑላቸው ዘንድ ሰጥቻቸዋለሁ። እንዲሁም ለምድር አራዊት ሁሉ ፣ ለሰማይ ወፎች ሁሉ ፣በምድር ላይ ለሚንቀሳቀሱ ሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ በምድር ላይ ለሚንቀሳቀሱ*

ሕያዋን ፍጡራን ሁሉ ማንኛውም ለምለም ተክል ምግብ እንዲሆናቸው ሰጥቻለሁ" እንዳለውም ሆነ።

አግዚአብሔር ምድርን እንዲሞሉ፣ እንዲገዙና በፍጥረት ሁሉ ላይ ገዥነት እንዲኖራቸው ባሕላዊ አደራ ሰጥቷቸዋል። እርሱም ከሰው ልጆች የሚወደድ አገዛዝን፣ መልካም የሆነ፣ ጥሩ ልብ ያላቸውን ነገስታትና አገዛዝን ሁሉ በአጠቃላይ ፍጥረት ላይና በእንስሳት ላይ ለማየት ይጠብቃል።

አግዚአበሔር በራሱ አምሳል ስለፈጠረው የሰው ልጅ ሊያደርግ የሚችለው አንዱ ነገር ፣ በሰው ልጅ ቁጥጥር ስር እንዲሆኑ አድርጎ ለፈጠራቸው ነገሮች አደራን መወጣት አንዱ ነው።

ዘፍ 1፡31 *"እግዚአብሔርም ያደረገውን አየ ፤ እነሆም መልካም ነበረ። መሸ ፣ ነጋም ስድስተኛ ቀን።"*

እግዚአብሔር ወደ ፍጥረቱ ሲመለከት ፣ እጅግ መላካም እንደሆነ ተናገረ። እንደ ፍጥረት አካል ፣ አንተን በሰራህ አሰራር ደስታን ያገኛል። ነገር ግን ፣ አንዳንድ ቀን፣ የማይመች፣ ግራ የገባውና ዋጋ ቢስ የመሆን ስሜት ሊሰማህ ይችላል። እንደዛ ከተሰማህ ፣ እግዚአብሔር እንደሰራህ ፣ እንደሚወድህና አንተም መልሰህ እንድትወደው እንደሚፈልግ አስታውስ። እግዚአብሔር ትልቅ ዋጋን በሕይወትህ አስቀምጧል ፤ ሊባርክህም ይፈልጋል። በእርግጥ ፣ ወደ የእግዚአብሔር ብትሆን፣ የእርሱ የተወደደ ርስትና የአይኑ ብሌን ነህ (ዘዳ 7፡6 ፤ 32፣10)

<u>ሰባተኛ ቀን</u>

ዘፍ 2፡2-3 ፣ *"በሰባተኛው ቀን ፣ እግዚአብሔር ሲሰራ የነበረውን ስራ ፈጸመ። ስለዚህም በሰባተኛውም ቀን ይሰራ ከነበረው ስራ ሁሉ አረፈ። እግዚብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ፣ ቀደሰውም። ምክንያቱም ይሰራ ከነበረው ስራ ሁሉ በእርሱ አርፎአልና"*

ሰራውን ሁሉ ካጠናቀቀ በኃላ፣ እግዚአብሔር አረፈ። እረፍት ያስፈልገው ነበረ; እግዚአብሔር ደከመው; በፍጹም ! ይልቁን ፣ ለሰው ልጆች የሚሰሩትን ስራ ካጠናቀቁ በኃላ ማረፍ እንዳለባቸው ለማስተማር ነበረ። እግዚአብሔር ሁልጊዜ እንድትሰሩ አልፈለገም። ስለዚህም፣ እያንዳንዱን ሰባተኛ ቀን

ለይቶ እንድታርፍበትና እግዚአብሔርን እንድታመልክ አድርጓል። ነገር ግን፣ በእርግጥ፣ እግዚአብሔር ሁልጊዜ እንድታርፍና እንድትጫወት አልፈለገም። በመጀመሪያ፣ እንድትተገብረው ፣ እግዚአብሔር የእረፍትንና የስራን ዑደት ገልጦ አሳይቷል ፤ ስድስት የስራ ቀናት እና አንድ የእረፍት ቀን በሳምንት። የመጀመሪያ ክፍለ ዘመን ክርስቲያኖች ፣ እሁድን እንደ ጌታ ቀን ያስቡት ነበረ ምክንያቱም ኢየሱስ ከሙታን መካከል የተነሳበት በመሆኑ።

<u>የጥናታዊ ጽሑፍ ስራ</u>

በቂ የሆነ ሳይንሳዊ ዝግጅትና ፍላጎት ያላቸው መምህራን ይሔንን ስራ ታዳጊዎቻቸውን ለማገዝ ሊሰጡ ይችላሉ። ስለ ግሪጎር ሜንድልና እርሱ ስላገኘው የውርስና የዘር ህጎች የተጻፉ ቢያንስ ሶስት መጣጥፎች ወይም ምዕራፎች እንዲያነቡ ጠይቃቸው። እንደ አማራጭ፣ የቴርሞዳይናሚክስ ሁለተኛን ሕግ እንዲያጠኑ ጠይቃቸው። ስለተማሩት ነገር አንድ ወይም ሁለት ገጽ ወረቀት እንዲጽፉና ምንጮቻቸውን ደግሞ በተናጠል መዘርዘር እንዲችሉ እዘዛቸው። እውቀታቸውን እንዲያካፍሉ ወደ መማሪያ ክፍሉ ጥራቸው። በተወሰነ መጠን ሳይንሳዊ ህግጋቱ ትክክል መሆናቸውን አንዳንድ ክስተቶች አስቀድሞ በተቀመጠላቸው ቅድመ ሁኔታ መሠረት እንደሚሆኑ በማሳየት አብራራ። ሳይንሳዊ ህግጋት ፣ ከዕሳቤ፣ ከግምት ፣ ከአስቀድሞ ትንበያ እና ከንድፈ ሃሳብ የተለዩ ናቸው። ለምሳሌ፣ የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሃሳብ ለገለጥ፣ ሊተገበር እና ሊረጋገጥ አይችልም እናም ስለዚህ ሳይንሳዊ ህግ አይደለም። የዘርን ጉዳይ ህግጋት አንደ ሀሳብ ብትሰጥ ፣ እንስሳትና እፅዋት ሁሉ በየራሳቸው ወገን የሚራቡበትን ያንን ህግ ለክፍል ውስጥ ውይይት አውጥተህ አሳይ። የቴርሞዳይናሚክስን ሁለተኛ ህግ ካወጣህ ደግሞ፣ ይሄ ህግ ለዝግመተ ልውጠታዊያኑ እንዴት ከባድ እንደሆነ አሳያቸው። ይሄ ህግ የሚለው የፍጥረት ስርዓት የሚጓዘው ወደ ስርዓት አልባ ሲሆን የዝግመተ ለውጥ ንድፍ ሀሳብ ግን ተቃራኒውን ያምናል።

<u>የተፈጥሮ ፕሮጀክት</u>

ታዳጊዎቹ፣ ቅጠሎችን ፣ አበቦችን ፣ ነፍሳትን እንዲሰበስቡና ንገራቸው፤ ነገር ግን በዚህ ድርጊታቸው የቱኛውንም አይነት (የሀገር ውስጥም ሆነ የክልላቸውን ህግጋት እንዳይተላለፉ

ንገራቸው ይሄም ለምሳሌ ፡- ከተከለከለ ቦታ የአበባን ቅጠል ማንሳት ሊሆን ይችላል።) እንደ አማራጭ ፣ አዕዋፋትን ፎቶ ማንሳት ይችላሉ። ስለተፈጥሮ የሚያወራን መጽሐፍ አቅርብላቸው ፤ በዚህም ምክንያት ታዳጊዎቹ እንስሳቱንና እጽዋቱን በሳይንሳዊ ወይም በላቲን ስማቸው መለየት ይችላሉ። ሳይንሳዊ ስም ሁለት ክፍሎችን እንደሚይዝ አብራራ ፤ ጂኖችንና ዘሮችን (ለምሳሌ ፡- ለኢንዲጎ ቡንቲንግ ፣ፓሴሪና ሲያኒያ የሚባል ስም አለው) በተጨማሪም ፣ ይሕያው ነገሮቹን ባሕሪያት ግለጽ። በአጠቃላይ ፣ በተመሳሳይ ጂን ውስጥ ያሉ እንስሳትና እፅዋት በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ የተገለጡትን ተመሳሳይ ወገኖች ለመፍጠር ፣ሊዳቀሉና ሊዋሃዱ እንደሚችሉ ንገራቸው። በሳይንሳዊ ስማቸው ላይ በመመስረት ፣ በተመሳሳይ ጂን ውስጥ ያሉ እንስሳትና እፅዋትን ምስስሎቸውን እንዲለዩ ጠይቃቸው። ነገር ግን፣ ሁሉም አይነት ምስስሎሽ ፣ በቀጥታና በቀላሉ የሚወሰድ አለመሆኑን ጥቀስ። ይህም ምስስሎሽ ሌሎች የዝግመተ ለውጥን ንድፈ ሃሳብ የሚከተሉ ሰዎች ከሚሉት የዘፈቀደ ልይዩነት ይልቅ፣ ከዘፍጥረት የፍጥረት ዘገባ ጋር ወጥ የሆነ ቅደም ተከተል ያለው እንደሆነ አብራራ።

<u>የጥበብ ፕሮጀክት</u>

ለዚህ እንቅስቃሴ ታዳጊዎቹን በተለያየ ቡድን ክፈላቸው፤ የአመራር ክህሎትንና ጥበባዊ ችሎታን በቡድናቱ መካከል እንደከፋፈልክ እርግጠኛ ሁን። እያንዳንዱን ቡድን አንድ የፍጥረትን ቀን እንዲመርጡና ፣ በሸራ፣ በግድግዳ ላይ በተወጠረ ስዕል እና በፓስተር ላይ እንዲስሉት ንገራቸው። እያንዳንዱን ቡድን በቂ ቀለምና ቀልም የመቀቢያ ብሩሽ ሰጥተሃቸው ሂደታቸውን ሁሉ እያገዝክ ተቆጣጠር። የተጠናቀቀውን የፍጥረት ስራ እግዚአብሔር “እጅግ መልካም” ብሎ እንደጠራው አሳስባቸው።

<u>የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት ጥያቄዎች</u>

1. የዘፍጥረት መጽሐፍ የፍጥረት ዘገባ ስለእግዚአብሔር ምን ይናገራል?
   እግዚአብሔር ዘላለማዊ እንደሆነና በሶስት አካላት እንደሚኖር ፡- ይሄም አብ፣ ወልድና መንፈስቅዱስ ነው።
2. መንፈስ ቅዱስ በፍጥረት ስራ ውስጥ ተሳትፎ እንደነበረው በምን አወቅህ; ዓላማውስ ምን ነበረ?

ዘፍ 1:2 እንደሚለው ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውኃው ላይ ሰፍፎ ነበረ። መስፈፍ የሚያሳየው የፍቅር እንክብካቤንና ጥበቃን ነው ፤ ልክ እናት የሆነች ወፍ ለልጇ እነደምትጠነቀቅ ።

3. እግዚአብሔር ወልድ በፍጥረት ስራ ውስጥ ተሳትፎ እንደነበረው እንዴት ነው የምናውቀው?

ዩሐ 1:1-3 እንደሚለው ፣ ቃል ከመጀመሪያውም ከእግዚአብሔር ጋር ይኖር እንደነበረ እና እርሱ ራሱ እግዚአብሔር እንደነበረ ነው። በተጨማሪም ፣ የእግዚአብሔር ቃል ሁሉን አድርጓአል፤ ከሆነው ሁሉ ያለእርሱ የሆነ የለም። ዩሐ 1:14 የሚያሳየው ቃልን እንደ እየሱስ ክርስቶስ ወይም እንደ እግዚአብሔር ወልድ ነው።

4. በሁለተኛው የፍጥረት ቀን ፣ እግዚአብሔር የውኃ አካላትን የሚለየውን ስፍራን ምን ብሎ ነው የጠራው?

እርሱ ጠፈር ወይም ሰማይ ብሎ ጠራው (ዘፍ 1:7) ። ይሔንን ስፍራ አንተ ከባቢ አየር ብለህ ልትጠራው ትቸላለህ።

5. ደረቅ የሆነው መሬት እንዲገለጥ እግዚአብሔር ምን አደረገ;

እግዚአብሔር ሲናገር፣ ዘፍ 1:9 እንደሚለው፣ ውኃው በአንድ ስፍራ ተከማቸ እና ደረቁ መሬትም ተገለጠ። ምንአልባት እግዚአብሔር ይሔንን ክምችት ተራሮቸን በፈጠረ ታላቅ የመሬት መናወጥ በኩል ፈጥሮት ይሆናል።

6. እግዚአብሔር በአራተኛው ቀን ምንን ነበረ የፈጠረው?

እግዚአብሔር ብርሃናትን ይሰጡ ዘንድ ጸሐይ ፣ ጨረቃና ክዋክብትን ሰራ።

7 . እነዚህ ሰማያዊ አካላት ምንድነው የሚያደርጉት?

ጸሐይና ጨረቃ ወቅቶቸን ፣ ቀናትንና አመታትን በመጠበቅ የሰው ልጆቸን ያግዛሉ።

8 . በየቱኛው ቀን ነው እግዚአብሔር ሰውን የሰራው?

እግዚአብሔር የሰው ልጅን በስድስተኛው ቀን ሰራው።

9 . እግዚአብሔር ከእንስሳት በተለየ መልኩ አድርጉ ሰውን እንዴት ሰራው?

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ እንደራሱ እንዲያስብ ፣ እንዲሰማውና እንዲተገብር አድርጎ በመልኩ ፈጠረው።

10 . እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ለምንድነው ያረፈው; የአንተስ ምላሽ ምንድነው መሆን ያለበት?

እግዚአብሔር የፍጥረቱን ስራ በስድስተኛው ቀን አጠናቀቀ፤ ይሄንንም ፣ በሰባተኛውም ቀን ለሰው ልጆች ከስድስት ቀን የስራ ውደት በኋላ ያርፉ ዘንድ አርዓያ እንዲያደርጉት ነው። በሳምንት አንድ ቀን ማረፍ ፣ እግዚአብሔርን ከሌሎች አማኞች ጋር ለማምለክ ዕድል ይሰጥሃል።

11. እግዚአብሔር ሁሉን ነገር እንደፈጠረ የሚናገረውን የመጽሐፍ ቅዱስን ትምሕርት የማይቀበሉ ሰዎች ምንድነው የሚያምኑት?

በዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሃሳብ ያምናሉ ፤ ቁስ አካል ከመጀመሪያውም የነበረ ሲሆን፣ አሁን ላይ ወዳለው መልክ የተቀየረው በብዙ የለውጥ ሒደቶች ውስጥ አልፎ ሲሆን ፣ ይሄም የሆነው፣ ያለ እግዚአብሔር እገዛ እና ያለምንም አስደናቂ ንድፍ እና እገዛ ነው።

12 . ዝግመተ ለውጣዊያን በእኚህ በሁለቱ ይከራከራሉ ፤ ሀ) እግዚአብሔር ሁልጊዜም አለ። ለ) እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ከምንም ፍጥሯል። ይሄንን አስተሳሰብ የእምነት ጉዳይ እንደሆነ እንጂ ሳይንሳዊ እንዳልሆነ ይከራከራሉ። ለእንዲህ አይነት ተገዳዳሪ ጥያቄዎች እንዴት ነው የምትመልሱት?

የዝግመተ ለውጥ ጽንሰሐሳብ ራሱ እምነትን የሚጠይቅ ነው ፤ እርሱንም በስፋት የሚዳስስ። ዝግመተ ለውጣዊያኑ ቁስ አካል ሁልጊዜም እንደነበረ ያምናሉ። ያም ማለት ቁስ አካል እንጂ እግዚአብሔር ዘላለማዊ እንዳልሆነ ያምናሉ ማለት ነው። ልክ ዝግመተ ለውጣዊያኑ የእግዚአብሔር ዘላለማዊነት እንደሚያስደንቃቸው ሁሉ ፣ የቁስ አካል ዘላለማዊነትም አማኞችን ያስደንቃቸዋል። የኋለኞቹ ፣ "ቁስ አካል ከየት መጣ;" ብለው ይጠይቁ ይሆናል። ደግሞም ፣ ሁሉን ቻይ ዘላለማዊ አምላክ ሁሉን እንደፈጠረ የሚናገረው አስተሳሰብ ነው ወይስ ነፍስ አልባና ፣ ተራ ቁስ አካል ራሱን ቀየረ ብሎ ማሰብ ነው የበለጠ እምነትን የሚጠይቀው; ቁስ አካል እና በሌላ አካል ያልተደገፈ ፍጡር አሁን ላይ ያሉተን ፍጥረታት ሁሉ አስገኝቷል የሚለው የዝግመተ ለውጥ ጽንሰ ሐሳብ የንድፈ ሐሳቡ አቀንቃኞች በተዋጣለት መልኩ ሊመልሱት የማይችሉት ጥያቄ እንደሆነ ቀርቷል።

13 . ዝግመተ ለውጣዊያኑ የሚከራከሩት ፣ መሬት ብዙ ሚሊዮን አመታት የቆየች እንደሆነች ሲሆን ይሄንንም መከራከሪያ ለማጠንከር ስነ ምድራዊ ማስረጃዎችን ያቀርባሉ። በእርግጥ ፣ የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሐሳብ ራሱን ለማብራራት እጅግ የረዘመ የጊዜ ቆይታን የሚጠይቅ ነው። ለዚህ ክርክር በፈጣሪ ምክንያት የፍጥረት መገኘትን የሚያምኑ ሰዎች እንዴት አድርገው ነው ምላሽ የሚሰጡት;

ዝግመተ ለውጣዊያኑ በብዙ ቢሊዮን የሚገመቱ አመታትን ቀድመው መገንዘብ ካልቻሉ ፣ የዝግመተ ለውጥ ንድፈ ሃሳብ አሳማኝነትን በማጣት ፣ ድጋፍ የጎደለው ይሆናል። ነገር ግን፣ ሁሉን ቻዩና በሁሉ ስፍራ የሚገኘው አምላክ ፣ ለምታየው ነገር ሁሉ ሌላ ማብራሪያን ይሰጥሃል። ስለእግዚአብሔር የፍጥረት ስራ እያንዳንዱን ጥልቅ ነገር ባታውቅ እንኳን ፣ ልክ አዳምን እንደ ልጅ ሳይሆን እንደ ትልቅ ሰው አድርጎ እንደፈጠረው ሁሉ ፣ መሬትንም እንደተጠናቀቀና ምንም እንደማይቀረው አድርጎ መስራትን አልተሳነውም። በተጨማሪም ፣ በዘፍጥረት መጽሐፍ ላይ እንዳለው ዓለምን ያጥለቀለቀው ጎርፍ ፣ ዛሬ በሚታየው መልኩ ፣የስነ ምድርን ቅርጽ የቀየረ ምክንያት እንደሆነ ብዙ አማኞች ይናገራሉ። እነርሱ እንደሚሉት፣ ስነ ምድራዊ ባሕሪይ አሁን ያለውን ቅርጽ የያዘው ፣ ድንገተኛ በሆነና በመጀመሪያ በተከሰተ አከገኛ ፍንዳታ ምክንያት እንደሆነ ያቀርባሉ።

14 . እምነታዊ ዝግመተ ለውጥ ምንድነው;

እምነታዊ ዝግመተ ለውጥ የሚያብራራው ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን የፍጥረት ትምሕርት እና የዝግመተ ለውጥን ማብራሪያ አንድ ላይ በማድረግ ነው። ይሔም ፣ እርሱ እንደሚለው ከሆነ ፣ እግዚአብሔር ቁስ አካልን ከፈጠረ በኋላ ፣አካላት አሁን ያሉበትን ቅርጽ እግዚአብሔር ራሱ በተቆጣጠረው ዝግመታዊ ሒደት አልፈው ደርሰዋል ብሎ ነው። በጣም ቀላል የሆኑ ቁስ አካላት በመጀመሪያ ከተፈጠሩ በኋለ ፣ አሁን ያሉበትን ውስብስብ መልክ በብዙ ሂደት አልፈው ደርሰዋል ብሎ ያስቀምጣል። ከብዙ ቢሊዮን አመታት በኋላ፣ እንደጦጣ ያሉ ትልልቅ አካል ያላቸው ሕያዋን ነገሮች ተከሰቱ፤ አነርሱንም ተከትሎ ሰው መጣ። በሆነኛው ጊዜም ፣ እግዚአብሔር አንድ አዲስን ነገር ሰራ ፤ እርሱም የሰውን ነፍስ ነው ፤ በሰው ሕይወት ውስጥም ጨመረው። በዚያም ቅጽበት ፣ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠረ።

15 . ስለ እምነታዊ ዝግመተ ለውጥ ምን ታስባለህ?

እምነታዊ ዝግመተ ለውጥ መጽሐፍ ቅዱስን ይቃረናል። ዘፍጥረት 2፡7 እንደሚለው ፣ "እግዚአብሔር አምላክ የሰውን ልጅ ከምድር አፈር አበጀው ፤ በአፍንጫውም የሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት ። ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።" ምንም እንኳን የሰው ልጅ ከጦጣ ዝርያ ወይም ከሌላ የጋራ ዘር እንደተገኘ ቢያምንም ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጅ ነፍስ አልባ ከሆነ አፈር እንደተበጀ እና በዚያም ቅጽበት እስትንፋሱን እፍ እንዳለበት ይናገራል። ሌላውን ማመን መጽሐፍ ቅዱስን የመካድ ያክል ጥፋት ሊያስከትል የሚችል አንሸራታች ስፍራ ላይ የመቆም ያክል አደገኛ ነገር ነው።

በመጨረሻም ከእነዚህ መዝሙራት መካከል አንዳቸውን ዘምር። ወይም እንደአማራጭ ፣ አንዱን የመዝሙር ግጥም ፣ እንደማጠቃለያ ጸሎት አድርገህ አንብበው።

1. "ሁሉም ነገር መልካም እና ያማረ ነው"
2. "ከያሕዌ የተዋበ ዙፋን ስር"
3. "እንዴት ታላቅ ነህ"

ክፍል 2

የእግዚአብሔር ዕቅድ ለዚህ ዓለም

ምዕራፍ 3
እግዚአብሔር ሁሉን ይቆጣጠራል

አላማ እግዚአብሔር ለክብሩ ሁሉን እንደሚቆጣጠርና እንደሚደግፍና ማመን

የእምነት መግለጫ (Catechism)[1]***ጥያቄ፡** የእግዚአብሔር የመግቦት ስራዎች ምን ምን ናቸው?

መልስ፡ የእግዚአብሔር የመግቦት ስራ፡- እግዚአብሔር ፍጥረታትንና እንቅስቃሴያቸውን ሁሉ የሚጠብቅበትና የሚያስተዳድርበት እጅግ ቅዱስ፣ ጠቢብ እና ብርቱ የሆነ አሰራሩ ነው።

ጥያቄ፡ እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረበት ስፍራ ለአዳም የገለጠው ልዩ የመግቦት ተግባር ምንድን ነው?

መልስ፡ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ከእርሱ ጋር የሕይወት ኪዳን ገብቷል፤ ይህ ቃልኪዳን በፍጹም መታዘዝ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ይኸውም አዳም መልካምና ክፉን ከምታስታውቀው የህይወት ዛፍ እንዳይበላ በመከልከል ነበር፤ ይህን ማድረግ ሞትን ያስከትል ነበርና።

የማሰላሰያ ጥቅስ ሮሜ 8፡28፤ “እግዚአብሔር፣ ለሚወዱትና እንደ ሐሳቡ ለተጠሩት፣ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲሠራ እንደሚያደርግላቸው እናውቃለን።”

የቃሉ ትምህርት <u>እግዚአብሔር ሁሉን ይሰራል</u>

[1] The Shorter Catechism, Q&A 11 and 12

ማስታወሻ

አላማ

እግዚብሔር ለክብሩ ሁሉን እንደሚቆጣጠርና እንደሚደግፍ ማመን

የእምነት መግለጫ

ጥያቄ፡ የእግዚአብሔር የመግቦት ስራዎች ምንድን ነው?

መልስ፡ የእግዚአብሔር የመግቦት ስራ፣ እግዚአብሔር ፍጥረታትንና እንቅስቃሴያቸውን ሁሉ የሚጠብቅበትና የሚያስተዳድርበት እጅግ ቅዱስ፣ ጠቢብ እና ብርቱ የሆነ አሰራሩ ነው።

ጥያቄ. እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረበት ስፍራ ለአዳም የገለጠው ልዩ የመግቦት ተግባር ምንድን ነው?

መልስ፡ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ከእርሱ ጋር የሕይወት ቃል ኪዳን ገብቷል፤ ይህ ቃልኪዳን በፍጹም መታዘዝ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ይኸውም አዳም መልካምና ክፉን ከምታስታውቀው የህይወት ዛፍ እንዳይበላ በመከልከል ነበር፤ ይህን ማድረግ ሞትን ያስከትል ነበርና።

መዝገበ ቃላት ወይም ኢንተርኔት በመጠቀም ታዳጊዎች የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ እንዲያጠኑ አድርግ፡- መግቦት፣ መጠበቅ፣ ማስተዳደር፣ መኖሪያ/ስፍራ እና ቃልኪዳን ። የእያንዳንዱን ቃል ፍች ካነበቡ በኋላ ቀጥሎ በራሳቸው ቃል እንዲተረጉሙ አድርግ። የቃላቱን ትርጉም በትክክል እስኪገነዘቡ ድረስ መጀመሪያ ፍችውን በማንበብ ቀጥለው ደግሞ የራሳቸውን ቃላት ተጠቅመው በመግለጽ ደጋግመው ይተርጉሙ። ካስፈለገ እርስ በርስ ተራ በተራ ይህንን ያድርጉ። ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ ታዳጊዎች የተጻፈውን ብቻ መልሰው እየተናገሩ ከሆነ፣ አስቀድመው የሁሉንም ቃላት ፍች በአንድ ጊዜ እንዲያነቡና ከዚያ ምንም ሳያዩ ሁሉንም በራሳቸው እንዲተረጉሙ አድርግ። በመቀጠል የእምነት መግለጫ ጥያቄና መልሶችን በድጋሚ ካነበቡ በኋላ በራሳቸው መንገድ ስለ መግቦት እንዲያብራሩ ጠይቃቸው።

በመቀጠል ታዳጊዎች ሁለት የእምነት መግለጫ ጥያቄና መልሶችን በራሳቸው ቃላት በድጋሚ እንዲጽፉና ስለ ቃላቱ ትርጉም የገባቸውን ነገር እንዲያስረዱ አድርግ። ቀጥሎ ያለው ምሳሌ የእምነት መግለጫ እንዴት በራስ አገላለጽ ሊጻፍ እንደሚችል ያስረዳል።

ጥያቄ፡ *እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሚንከባበውና ሚጠብቀው በምን መንገድ ነው?*

መልስ፡ *የእግዚአብሔር ቅድስና፣ ጥበብ እና ብርታት ፍጥረትን ደግፎ ይመራል*

ጥያቄ፡ *አዳምና ሔዋን ኃጢአት ከመስራታቸው በፊት ከእነርሱ ጋር የበረው ልዩ የእግዚአብሔር ጥበቃና እንክብካቤምን ይመስላል?*

መልስ፡ *እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ከተከለከለው ዛፍ ካልበሉ ሀይወትን* እንደሚሰጣቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር፤ ነገር ግን ይህን ትዕዛዝ ከተላለፉ ሞትን እንደሚሞቱም አስጠንቅቋቸው ነበር።

<u>መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ</u>

ቀጥለው ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ለየትኛው የእምነት አንቀጽ ቃል/ሀረግ መሰረት እንደሆኑ እንዲለዩ ታዳጊዎችን ጠይቃቸው።

ዘፍ 2፡16-17፣ "እግዚአብሔር አምላክ *(ያህዌ ኤሎሂም)* ሰውን እንዲህ በማለት አዘዘው፤ "በአትክልት ስፍራው ውስጥ ከሚገኝ ከማንኛውም ዛፍ ፍሬ ትበላለህ። ነገር ግን መልካምና ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ አትብላ፤ ምክንያቱም ከእርሱ በበላህ ቀን በርግጥ ትሞታለህ።"

ሰው መልካምና ክፉ የምታሳውቀውን የህይወት ዛፍ እንዳይበላና ሞትን እንዳይሞት መከልከሉ

መዝ 31፡15፣ "ዘመኔ ያለው በእጅህ ነው፤"

ፍጥረታቱንና እንቅስቃሴአቸውን የሚጠብቅና የሚቆጣጠር
መዝ 46፡1፣ "አምላካችን መጠጊያችንና ኃይላችን፣ በሚደርስብን መከራ ሁሉ የቅርብ ረዳታችን ነው።"

ፍጥረታቱን የሚጠብቅ...
መዝ 103:19 ፣ "እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አጽንቶአል፤ መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች።"

ፍጥረታቱን የሚያስተዳድር

ምሳ 8:15, "ነገሥታት በእኔ [በጥበብ]ይነግሣሉ፤ ገዦችም ትክክል የሆነውን ሕግ ይደነግጋሉ፤"

ፍጥሩቱን የሚያስተዳድርበት እጅግ ቅዱስ፣ ጠቢብ እና ብርቱ የሆነ አሰራሩ
ዳንኤል 12፡21፣ "[የሰማዩ አምላክ] ነገሥታትን በዙፋን ያስቀምጣል፣ ደግሞም ያወርዳቸዋል፤"

ፍጥረታቱን የሚያስተዳድር

ሆሴዕ 6:7፤ "እንደ አዳም [እስራኤላውያን] ቃል ኪዳንን ተላለፉ፤ በዚያም ለእኔ ታማኝ አልነበሩም።"

ከአዳም ጋር የህይወት ቃል ኪዳን አደረገ

ማቴዎስ 5፡45፤"እርሱ [የሰማዩ አባት] ፀሓዩን ለክፉዎችና ለደጎች ያወጣል፤ ዝናቡንም ለጎኪአተኞችና ለጻድቃን ያዘንባል።"

ፍጥረታቱን የሚጠበቅና የማስተዳደር

ማቴዎስ 10፡29፤ "በአንድ ሳንቲም ከሚሸጡት ሁለት ድንቢጦች አንዲቷ እንኳ ያለ አባታችሁ ፈቃድ ምድር ላይ አትወድቅም።"

ፍጥረታቱን የሚጠብቅ

ቆላስይስ 1፡17፤ "እርሱ [ክርስቶስ] ከሁሉ በፊት ነው፤ ሁሉም ነገር በአንድ ላይ ተያይዞ የጸናው በእርሱ ነው።"

እጅግ ብርቱ ጥበቃው

ዕብራውያን 1፡3፤ "እርሱ የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅና የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ ሆኖ፣ በኀያል ቃሉ ሁሉን ደግፎ ይዞአል፤"

እጅግ ብርቱ ጥበቃው

<u>የእምነት መግለጫ ጥያቄዎች</u>

1. "መግቦት" ማለት ምን ማለት ነው?

ቃሉ "መገበ"ከሚለው ስርዎ ቃል የመጣ ሲሆን መንከባከብን፣ መጠበቅንና የሚያስፈልገውን ማሟላትን ያመለክታል። በሥነ መለኮት መግቦት እግዚአብሔር በበጎ ፈቃዱ ፍጥረቱን የሚጠብቅበትንና የሚያስተዳድርበትን አሰራር ያመለክታል። ይህን መግቦት አንዳንዶች ጠቅላላ መግቦትና ልዩ መግቦት በማለት በሁለት ይከፍሉታል። "ጠቅላላ መግቦት" እግዚብሔር ፍጥረተ-ዓለሙን የሚደግፍበትንና የሚያጸናበትን መንገድ ሲያመለክት "ልዩ መግቦት" ግን በቀጥታ በሰዎች ህይወት ውስጥ ጣልቃ በመግባት ፈቃዱን የሚፈጽምበትን አደራረግ ያሳያል።

2. እግዚአብሔር መግቦቱን የሚገልጥባቸው ሁለት ተግባራት ምን ምን ናቸው?

እግዚአብሔር ሁለን ይጠብቃል፤ ደግሞም ያስተዳድራል።

3. የእግዚአብሔር የመግቦት ስራ ተደራሽ ማነው?

እግዚአብሔር በመግቦቱ ለፍጥረት ሁሉ፣ በተለይም ለህዝቡና ለእንቅስቃሴያቸው ይጠነቀቃል። ሁሉ በእርሱ ላይ ጥገኛ ናቸው፤ ያለ እርሱ አንዳቸውም መኖር አይችሉም። በአጭሩ የእግዚአብሔር የመግቦት ስራ ለሁሉ ነው።

4. በርካታ ጊዜ እግዚአብሔር ለሙሴና ለእስራኤል መግቦቱን በልዩ መንገድ ገልጧል። ኢሳያስ 63፡11-14ን በማንበብ የእግዚአብሔርን ልዩ ክብካቤና መለኮታዊ ጥበቃ ለማስተዋል ሞክር። እግዚአብሔር ህዝቡን በልዩ መንገድ "በመግቦት ስራው" የሚባርከው ለምንድን ነው?

ኢሳያስ 63፡14 ስሙ ይመሰገን ዘንድ ወይም ክብሩ ይገለጥ ዘንድ እግዚአብሔር ህዝቡን እንደመራ ይነግረናል። (በተጨማሪ ሮሜ 11:36 ተመልከቱ)

5. እግዚአብሔር "ፍጥረታትንና እንቅስቃሴያቸውን" ሁሉ ይቆጣጠራል። በግልጽ መረዳት እንደሚቻለው ሰዎች የእግዚብሔርን ህግ ሲከተሉ መግቦቱ ያገኛቸዋል። ነገር ግን ሰዎች ጠማማ መንገድን ቢከተሉስ? ለመሆኑ እግዚአብሔር ክፉ ድርጊትን ይቆጣጠራል?

ሁሉም ሰው በአዳም መተላለፍ ምክንያት ኃጢአታዊ ባህርይ ይዞ የሚወለድ ሲሆን ፣ እያንዳንዱ ሰው በግሉ ለሚሰራው ኃጢአት ተጠያቂ ነው። እግዚአብሔር የማንንም ሰው እጅ ጠምዝዞ ኃጢአት አያሰራ፤ ስለዚህ ወደ አለም ለገባውና በሰው ሁሉ ላይ ለሰለጠነው ኃጢአት እርሱ ተጠያቂ አይደለም። (ይልቁንም በተቃራኒው በመጽሐፍ ቅዱሳችን ከምናገኛቸው ቁልፍ ርዕሰ ጉዳዮች መካከል መቤዠት አንዱ ሲሆን ይህም እግዚአብሔር ወልድ በሰው ምትክ ሆኖ ኃጢአትን ድል ያደረገበት ማዳን ነው።) ሆኖም ግን እግዚአብሔር በመግቦት ስራው የኃጢአትን ውጤት ለእርሱ ቅዱስ ፈቃድ መፈጽሚያ መንገድ ሆኖ እንዲያገለግል ያደርጋል። በዚህ ረገድ እግዚአብሔር ኃጢአታዊ ምልልስን ሳይቀር የሚቆጣጠር ሲሆን "ነገር ሁሉ" (ኃጢአትን ጨምሮ) የእርሱ በሆኑት ህይወት ውስጥ በጎ የሆነውን ለመስራት ይጠቀምበታል (ሮሜ 8:28)። ከቅዱሳት መጽሐፍት ውስጥ ሁለት ምሳሌዎችን እንመልከት። ዮሴፍን ወንድሞቹ ለባርነት ከሸጡት በኋላ አባታቸው ያዕቆብ በውሸት ልጁ እንደሞተ እንዲያምን አድርገውት ነበር። ምንም እንኳ ይህን ኃጢአት በወንድማቸው ላይ ቢፈጽሙም ፣ እግዚአብሔር በጊዜው በዮሴፍ ህይወት ውስጥ የሆኑትን ነገሮች ተጠቅሞ ህይወቱን እንደቀረጸ እናያለን። እንዲሁም ነገሩን እግዚአብሔር ሊመጣ ካለው የረሃብ አደጋ ቤተሰቡ ሁሉ የሚተርፍበት ምክንያት አድርጎ እንደተጠቀመው እንመለከታለን (ዘፍጥረት 45:4-15፤ 50:15-21)። በአዲስ ኪዳን ስንመለከት ደግሞ ሄሮድስ፣ ጲላጦስ እና የእስራኤል ህዝብ ኢየሱስን ለመግደል አሲረው ነበር። እግዚአብሔር ግን ኃጢአታቸውን ተጠቅሞ ኃጢአትን ድል የሚያደርግበትንና የእርሱ የሆኑትን የሚያድንበትን እቅዱን ፈጽሟል (ሐዋ 4:27-28)።

6. ኪዳን ምንድን ነው?
በአጠቃላይ ኪዳን ማለት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አካላት መካከል የሚፈጸም ስምምነት ነው።

7. በጊዜው የነበረው "የህይወት ኪዳን" ምንድን ነው?

እግዚአብሔር የሰውን ዘር ሁሉ ከሚወክለው ከአዳም ጋር የህይወት ኪዳን ገብቶ ነበር። በኪዳኑም መሰረት እግዘዚአብሔር ለአዳም የዘላለምን ህይወት የሚሰጠው ሲሆን፣ ይህ ግን በእንድ ቅድመ ሁኔታ ላይ ይተመሰረተ ነበር። ይህም አዳም መልካምና ክፉን ከምታሳውቀው ዛፍ እንዳይበላ በመከልከል ነበር፤ ምክንያቱም ይህን መተላለፍ ሞትን ያስከትል ነበር (ዘፍጥረት 2:6-17)። አዳም ይህን ትዕዛዝ በመተላለፍ ከዚያች ዛፍ ከበላበት ጊዜ አንስቶ የሰው ዘር ሁሉ ከኃጢአታዊ ባህርይና መንፈሳዊ ሞት ቀንበር ስር ወድቋል (ሮሜ 5:12)። እዚህ ጋር ለታዳጊዎች የ ሲ. ኤስ. ሉዊስ ን ስፔስ ትሪኦሎጂ (space trilogy) መጽሐፍ ልትጠቅስ ትችላለህ። Out of the Silent Planet የተሰኘው የመጀመሪያው መጽሐፍ፣ አዳምና ሔዋን ኃጢአት ባይሰሩ ኖሮ ህይወት ምን ልትመስል እንደምትችል ሲያሳይ ፤ Perelandraየተባለው ሁለተኛው መጽሐፍ ደግሞ አዳምና ሔዋን በዲያቢሎስ በተፈነኩት ሰዓት የነበረው ሁኔታ ምን ሊመስል እንደሚችል ያትታል።

8. አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህን የህይወት ኪዳንን “የስራ ኪዳን” በማለት የሚገልጹት ለምንድን ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ በጊዜው የነበረውን ስምምነት የህይወት ኪዳንም ሆነ የስራ ኪዳን በማለት አይገልጸውም። አንዳንድ ክርስቲያኖች በተሰጠው የዘላለም ህይወት በረከት ላይ በማተኮር የህይወት ኪዳን ሲሉት፣ ሌሎች ደግሞ ለአዳም በተሰጠው ፍጹም የመታዘዝ ቅድመ ሁኔታ ላይ በማተኮር “የስራ ኪዳን” በማለት ይገልተጹታል።

የማሰላሰያ ጥቅስ

ሮሜ 8፡28፤ “እግዚአብሔር፣ ለሚወዱትና እንደ ሐሳቡ ለተጠሩት፣ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲሠራ እንደሚያደርግላቸው እናውቃለን።”

ብዙ ክርስቲያኖች ይህን ጥቅስ በሚገባ ያውቁታል። በርግጥ ጥቅሱ ከሚሰጠው ትልቅ ተስፋና መጽናናት አንጻር ክፍሉን በቃል መያዛቸው አይገርምም። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ይህን ክፍል አላግባብ ሲተረጉሙት፣ ሲረዱት ወይም ሲያዛምዱት ይስተዋላል።የጥቅሱን ትክክለኛ ትርጉምና ፋይዳ ለመረዳት በመጀመሪያ ክፍሉ ምን እንዳማይል መገንዘብ ያስፈልጋል። ከዚያም ክፍሉ ምን እንደሚል ወይም የሚያስተላልፈውን መልዕክትና የሚሰጠውን ተስፋ ምን እንደሆነ በቅጡ መረዳት ትችላለህ።

በመጀመሪያ ደረጃ፣ ክፍሉ በእያንዳንዱ ሰው ህይወት ውስጥ የሚከናወነውን ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ለበጎ ያውለዋል አይልም። ይልቁኑ ክፍሉ ይህን ተስፋ የሚሰጠው “እግዚአብሔርን፣ ለሚወዱትና እንደ ሐሳቡ ለተጠሩት ነው”። የማያምኑ ሰዎች በዚህ ውስጥ ድርሻ የላቸውም፤ ምክንያቱም ተስፋው ለተመረጡት የእግዚአብሔር ህዝቦች፣ ይኸውም በክርስቶስ ጌትነትና አዳኝነት ላመኑት ብቻ ነው።

ሁለተኛ፣ ክፍሉ ጥሩ ጥሩ ነገሮች ብቻ ናቸው በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሱት አይልም። ይልቁኑ እግዚአብሔር በህይወታቸው የሚከሰቱትን ነገሮች ሁሉ (መልካም ሆነ ክፉ፣ በኃጢአታቸው ምክንያት የመጣውንም ጭምር) ለመልካም እንደሚለውጠው ያስረግጣል እንጂ። መስፈሪያ በሌለው በጎ ጥበቡና ኃይሉ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ደስ የማያሰኝ ሁኔታ ለህዝቡ እጅግ በጎ ለሆነ ዓላማ ያውለዋል። “እናውቃለን” የሚለው የክፍሉ የመጨሻው ቃል፣ ክርስቲያኖች በዙሪያቸው ያሉትን ፈታኝ ሁኔታዎችን በሙሉ በእግዚአብሔር እጅ ከተያዘውና ከጻናው ብሩኅ ተስፋቸው አንጻር እንዲመለከቱ ያበረታታል። ይህ ድነትን ላገኘች ነፍስ ምንኛ ታላቅ መጽናናነትን በየዕለቱ የሚሰጥ ድንቅ ተስፋ ነው! ይህን በአንድ ቀላል ምሳሌ መመልከት እንችላለን። ህጻናት ብዙ ጊዜ ክትባት መከተብ ይፈራሉ። በርግጥ መርፌው ያማል፤ ነገር ግን ወላጆች ሀመሙ ለአጭር ጊዜ እንሆነና ክትባቱ ግን በአደገኛ ህመሞች የመያዝ እድላቸውን በእጅጉ እንደሚቀንስላቸው በማስረዳት ልጆቻቸውን ለማረጋጋት ይሞክራሉ። መከተብ የሚያስከትለው የአጭር ጊዜ ህመም፣ ሰውን ለረጅም ጊዜ ያለ በሽታ ስጋት እንዲኖር ያስችለዋል።በአጠቃላይ በወላጆቻቸው ላይ እምነት ያላቸው ልጆች ወደ ሃኪም ቤት ለመሄድ ብዙ አይፈሩም። በየትኛውም የህይወት ጎዳና የሰማዩን አባት ማመንም እንዲሁ ከብዙ ፍርሃትና ጭንቀት ይገላግላል።

ሶስተኛ፣ በማሰላሰያ ጥቅሱ ውስጥ “ለበጎ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ህዝብ የግድ ሁልጊዜ ጤነኛ፣ ሀብታም እና ደስተኛ እንደሚሆን አያሳይም። እግዚአብሔር እንዲህ አይነት ተስፋ አልሰጠም። እውነት ነው ብዙ ክርስቲያኖች እነዚህ በረከቶች ሊበዙላቸው ይችላል፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በረከቶቹ ሁልጊዜ እንደሚኖሩ ተስፋ አልሰጠም። ይልቁኑ በህይወታቸው የሚያልፉትን ነገሮች ሁሉ አያይዞ ለእነርሱ እጅግ በጎ ለሆነ ዓላማ ወይም መልካም ፍሬ እንደሚሰራላቸው ነው ተስፋ የሰጠው። በርግጠኝነት እግዚአብሔር ቅዱሳኑን ሊባርክ ከሚፈልግባቸው ድንቅ ፍሬዎች መካከል ቅድስና አንዱ ነው፤ ይህም ሰው ክርስቶስን እየመሰለ የሚያድግበት ረጅም የህይወት ዘመን ለውጥ ነው። በ ዮሐ 17፡17 ኢየሱስ የእርሱን ምርጦች እንዲቀድሳቸው አባቱን ይለምናል። በእግዚብሔር መቀደስ ከሁሉ የሚልቅ ድንቅ በረከት ነው! አስታውስ፣ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር አያይዞ ለአማኞች ጤንነት፣ ብልጽግናና ደስታ አይሰራም፤ ይልቁን ሁሉን ለራሱ ዓላማ፣ ለእነርሱ ጥቅም እንዲሁም ለእርሱ ክብር በሚያመጣ መልኩ አያይዞ ይሰራል። ሮሜ 8፡28 ን ስታጠኑ የክፍሉ ሃሳብ ምን እንደሆነና ለህይወታችሁ ያለው ፋይዳ ምን እንደሆነ አሰላስሉ። ምናልባት በሕይወታችሁ ከባድ ጊዜ ከመጣ፣ በእግዚአብሔር ጽኑ ተስፋ ላይ ልባችሁን ጣሉ።

አሁን የማሰላሰያ ጥቅሱ ምን እንደማይል ተገንዝባችኋል፤ በመቀጠል ክፍሉ እግዚአብሔር ለመረጣቸው ሰዎች የሚሰጠውን ታላቅ ተስፋ፣ ዋስትና እና መጽናናት ምን እንደሆነ አስቡ። እግዚአብሔር ነገርን ሁሉ ለበጎ ይሰራዋል። በሆነ ውስን የህይወታችን ክፍል ውስጥ የሚከናወኑትን ነገሮች ብቻ ሳይሆን፣ በሁለንተናችን የሚሆነውን ሁሉ ለበጎ ይሰራዋል። የእርሱ ስራ በአንዳንድ ጉልህ የህይወት ክስተቶች እና አጋጣሚዎች ብቻ የተገደበም አይደለም፤ በፍጹም። እጅግ ጥቃቅንና ትርጉም የሌላቸው የሚመስሉ ጉዳዮችንም እርሱ ይጠቀማል። አዎ፤ እግዚአብሔር በመልካምም ሆነ ክፉ ሁኔታዎች ውስጥ ለክርስቲያኖች በጎ የሆነውን ነገር ይሰራል። እርሱ ሁልጊዜ በሁሉ ነገር ውስጥ በጎ የሆነውን ይሰራል።

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር በአማኞች ህይወት የሚከናወኑ ነገሮችን እንዴት አድርጎ ለበጎ እንደሚለውጣቸው እንድንረዳ የሚያግዙ የበረከት ቅምሻዎችን ያሳየናል። ሆኖም ግን የነገሩን የመጨረሻ መልካም ፍሬ ማየት የተስፋ ቃሉ አንድ አካል አይደለም። አንዳንድ ጊዜ ቅዱሳን ነገሮች ለመልካም ሲለወጡ ላያስተውሉ ይችላሉ፤ ወይም ዛሬ በህይወታቸው ያለ መልካም ነገር እግዚአብሔር ከትናንት አስቸጋሪ ሁኔታዎቻቸው ውስጥ ያወጣው በጎ ፍሬ እንደሆነ ላይገነዘቡ ይችላሉ። ያም ሆነ ይህ ግን የማይዋሽ እግዚአብሔር ተስፋን ስለሰጠ ነገር ሁሉ ለበጎ እንደሚለወጥ እርግጥ ነው። ስለዚህ ደስ የማያሰኙ ነገሮች ውስጥ ስታልፍ፣ እግዚአብሔርን የምትወድና እንደ ሃሳቡ የተጠራህ አማኝ እንደመሆንህ መጠን፣ እርሱ ሁሉን ለበጎ እንደሚያደርግልህ በፍጹም ልብህ ታመን። በዚህ ተስፋ ላይ ሙሉ በሙሉ ልብህን በመጣል፣ ሊመጣ ያለውን በጎ ፍሬ እያሰብክ እርሱን አመስግን፣ ስሙን ባርክ።

<u>የማሰላሰያ ጥቅስ ጥያቄዎች</u>

1. እግዚአብሔር በሁሉ ሰው ህይወትው የሚከናወኑ ነገሮችን አያይዞ ለበጎ እንዲሰሩ ያደርግላቸዋል?

   በፍጹም፣ ነገሮች ተያይዘው ለበጎ እንዲሰሩ እንደሚያደርግ እግዚአብሔር ተስፋ የሰጠው የእርሱ ለሆኑት ለምርጦቹ ብቻ ነው።

2. ሰዎች ልክ ኢየሱስን የህይወታቸው ጌታና አዳኝ አድርገው ሲቀበሉ፣ እግዚአብሔር ክፉ ነገሮችን በሙሉ ከህይወታቸው ይከለክላል ?

   አይከለክልም፤ ይልቁኑ እግዚአብሔር በህይወታቸው የሚያልፉ ክፉ ነገሮችን እንኳ ሳይቀር ተጠቅሞ ለበጎ ፍሬ ይሰራላቸዋል።

3. ስለ ሁሉ ነገር በፍጹም ልብ በክርስቶስ ላይ መደገፍ ምንም አይነት የኢኮኖሚ ችግር የሌለበት ህይወት እንድንመራ ያስችለናል?

በፍጹም፣ መጽሐፍ ቅዱስ "የጤና እና የሀብት" ወይንም የብልጽግና ወንጌልን አያስተምርም።

4. እግዚአብሔር ደስ ከማያሰኙ ሁኔታዎቻችን ውስጥ ምን መልካም ነገር ያወጣ ይሆን ብሎ በጉጉት መጠባበቅ ችግር አለው? ለምሳሌ፣ ለህክምና ወደ ሃኪም የሄደን አንድን የካንሰር ታማሚ ክርስቲያን አስቡ። ይህ ክርስቲያን በካንሰር ከመታመሙ የተነሳ ምን መልካም ነገር ሊያገኝ እንደሚችል እያሰላሰለ መጠበቅ ይኖርበታል?

ምንም እንኳ እግዚአብሔር በካንሰር ህመሙ አማካኝነት በጎ የሆነን ነገር ቢሰራም፣ ታማሚው ይህን መልካም ነገር ሊያየው ወይም ሊረዳው እንደሚችል ግን ቃል አልገባም። ከህመሙጋር ተያይዞ ሊኖር ሚችለውን በጎ ነገር ለማየት ወይም ለመረዳት መሞከር በራሱ ክፋት የለውም። ነገር ግን ከሁሉ ሚሻለው እግዚአብሔር በካንሰሩ አማካይነት በህይወታችን የሚሰራው አንዳች መልካም ነገር እንዳለ ማመን ነው፤ ምንም እንኳ በግልጽ በአይናችን ባናየው።

የቃሉ ትምህርት፤ እግዚአብሔር ሁሉን ለበጎ ይሰራል

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ አንድ በእግዚአብሔር መግቦት ስለታመነ አስደናቂ ወጣት የሚናገር ታሪክ እናገኛለን። ይህ ሰው እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ለብዙ አመታት አልፏል። ነገር ግን ይህ ወጣት ክፉ ያደረጉበትን አካላት ከመውቀስና ከመወንጀል ወይም ለበቀል ከመነሳት፣ ይልቅ ባለፈበት መንገድ ውስጥ አብሮት የነበረውን የእግዚአብሔርን ጥበቃና ምሪት በማሰብ ለአምላኩ እውቅና መስጠትን መርጦ ነበር። ይህ መረዳቱ ከብዙ አመታት በኋላ የበደሉትን ሰዎች እንዲህ በማለት እንዲቀበላቸው አስችሎታል፡- "አትፍሩ፤ እኔን በእግዚአብሔር *(ኤሎሂም)* ቦታ ማን አስቀመጠኝ? እናንተ እኔን ለመጉዳት አስባችሁ አድርጋችሁት ነበር፤ እግዚአብሔር *(ኤሎሂም)* ግን ዛሬ እንደሚታየው ሁሉ የብዙዎችን ሕይወት ለማዳን ለበጎ ነገር አዋለው።" (ዘፍ 50፡19-20).

ሁላችንም እንደምናውቀው ይህ ወጣት ዮሴፍ ነው። በዮሴፍ ህይወት ውስጥ እግዚአብሔር የሰራውን ስራ ይበልጥ ለመረዳት ወደ ኋላ ሄዶ የአባቱን የያዕቆብን ታሪክ ማየት ይጠቅማል። ያዕቆብ አስራሁለት ልጆች ነበሩት። ዮሴፍ ደግሞ አስራ አንደኛ ልጁ ሲሆን፣ አባቱ ከሁሉ ይልቅ አብልጦ ይወደው ነበር። ያዕቆብ ዮሴፍን በጣም ከሚዳት ሚስቱ ራሔል ስለወለደው ለእርሱ የአይኑ ማረፊያ ነበር። (ሌላኛቸው የራሔል ልጅ ብንያም ሲሆን እርሱም ለዮሴፍ በእናትም በአባትም ወንድሙ ነው፤ ብንያም ከአስራ ሁለቱ መካከል በእድሜ ትንሹ ነበር።) ያዕቆብ ለልጁ ዮሴፍ የነበረውን ልዩ ፍቅር ለመግለጽ "በጎብረ ቀለማት ያጌጠ እጀ ጠባብ አደረገለት"። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች እንደሚሉት ይህ ልብስ እስከ ቁርጭምጭሚት የሚሸፍን፣ በብዙ ቀለማት ያሸበረቀና በነገስታት ቤተሰብ የሚለበስ ልብስ ነበር። ይህ ልብስ የየሴፍ ወንድሞች ከለበሱት ጋር ለንጽጽር ሚቀርብ አልነበረም። ይህ ጌጠኛ ልብስ ያዕቆብ ለልጁ ዮሴፍ ያለውን ልዩ ፍቅር የገለጸበት ቢሆንም፣ ይህ ግን በሌላ በኩል በዮሴፍ ወንድሞች ልብ ውስጥ አደገኛ የቅናት ስሜትን ጭሮ ነበር። ከዚህም የተነሳ ወንድሞቹ ዮሴፍን ጠሉት (ዘፍጥረት 37፡3-4)።

ታሪኩን ይበልጥ የሚያወሳስበው ደግሞ፣ ዮሴፍ ወጣት ከመሆኑ አንጻር ነገሩን በብስለት ለመያዝ መቸገሩና ወንደሞቹ ራሱን ከፍ ከፍ እንዳደረገ እንዲያስቡ በሚያደርግ መልኩ አንዳንድ ነገሮችን ማድረጉ ነው። ይህ

የብስለት ክፍተት በግልጽ የታየው ዮሴፍ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያያቸውን ሁለት ህልሞች በያዘበት መንገድ ሲሆን፣ ህልሙም ዮሴፍ ታላቅ ገኸ እንደሚሆን የሚያስረዳ ነበር። በመጀመሪያው ህልም ዮሴፍ እና ወንድሞቹ በእርሻ ነዶ ያስሩ ነበር፤ ከዚያም የእነርሱ ነዶ የዮሴፍን ነዶ ከበው ሲሰግዱለት ያያል። በሁለተኛው ህልም ደግሞ ዮሴፍ ፀሐይ፣ ጨረቃ እና አስራ አንድ ከዋክብት ወድቀው ሲሰግዱለት ነበር ያየው። ነገር ግን ዮሴፍ ይህን መለኮታዊና ተምሳሌታዊ መረዳት በልቡ ከመያዝ ይልቅ፣ ያየውን ሁሉ ሄዶ ለቤተሰቦች በኩራት ነገራቸው(ዘፍጥረት 37፡5-11)።

የዮሴፍ መከራ

አንድ ቀን ያዕቆብ ከሰፈር ርቀው በጎችን ያሰማሩ ስለ ነበሩት ወንድሞቹ ሁኔታ እንዲያጣራና መልሱን ይዞለት እንዲመጣ ልጁን ዮሴፍን ላከው። (ምናልባትም ያዕቆብ የቤተሰቡን ሁኔታ የመቆጣጠር ኃላፊነት ለዮሴፍ ሳይሰጠው አይቀርም፤ ምክንያቱም በዘፍጥረት 37፡2 እንደምናነበው ቀደም ብሎ ገና በ 17 ዓመት ዕድሜው ከእርሱ ጋር የአባቱን በጎችና ፍየሎች ይጠብቁ ስለነበሩት ወንድሞቹ ድርጊት ለአባቱ መጥፎ ወሬ ይዞለት ይመጣ ነበር።) በዚያች እለት ዮሴፍ አባቱ የሰጠውን ጌጠኛ ልብስ ለበሶ ነበር ወደ ወንድሞቹ የሄደው። ወንድሞቹም ገና ከሩቅ ሲያዩት "ይህን ህልመኛ" እንዴት ማስወገድ እንዳለባቸው አሴሩ። በዚህም ዮሴፍን ክፉ አውሬ ነጥቆ እንደበላው በውሸት አባታቸውን ለማሳመን ወሰኑ። ሆኖም ግን የሁሉም ታላቅ የሆነው ሮቤል ዮሴፍን ሊገድሉት እንደማይገባ ወንድሞቹን አሳመናቸው። ስለዚህም የመግደል ሃሳባቸውን በመተው ጌጠኛ ልብሱን ገፍፈው ወደ ደረቅ ጉድጓድ ጣሉት። ሮቤል ይህን ሃሳብ ያመጣው ዮሴፍን ከእጃቸው ለመታደግና፣ ከጉድጓድ አውጥቶ ወደ አባቱ ለመመለስ ነበር (ዘፍ 37፡12-24)

ነገር ግን ሮቤል በቅርብ ባልነበረበት ሰዓት ወንድሞቹ ከሰሜን የሚመጡ የእስማኤል ነጋዴዎችን አዩ። ነጋዴዎቹ በግመሎቻቸው ሽቶ፣ በለሳን እና ከርቤ ጭነው ወደ ግብጽ የሚጓዙ ነበሩ። ከዚያም ይሁዳ ዮሴፍን እንደ ባሪያ ለእነዚህ እስማኤላውያን ነጋዴዎች መሸጥ እንደሚሻል ወንድሞቹን አሳመናቸው። ወንድሞቹ ይህን ሲያደርጉ ዮሴፍ በግብጽ ሀገር እንደሚጠፋና ከዚህም የተነሳ ዳግመኛ እንደማያዩት በማሰብ ነበር። ይህን ክፉ ድርጊታቸውን ለመሸፈን የዮሴፍን ጌጠኛ ልብስ በፍየል ደም በመንከር ልብሱን እንዲህ ሆኖ እንዳገኙት ለአባታቸው አረዱት፤ በዚህም ዮሴፍን ክፉ አውሬ እንደገደለው አሳመኑት። ያዕቆብ ይህን ሲሰማ ልቡ እጅግ አዘነ፤ አያሌ ቀንም ስለ ልጁ አለቀሰ። በዮሴፍ ላይ ያደረጉት ክፉ ነገር ሳያንስ፣ አባታቸውን ከባድ ሀዘንና የልብ ስብራት ውስጥ ጣሉት (ዘፍጥረት 25-35)። ለዮሴፍ የነበራቸውን መራራ ጥላቻ በማፈን፣ ለግድያ በማሴር እና በመዋሸት ክፉ ድርጊቶች ገለጡት። ዮሴፍ የገዛ ወንድሞቹ ሲከዱትና ለባርነት ወደ ግብጽ ሲሸጡት፣ ከዚህም የተነሳ ዳግመኛ ቤተሰቡና ወዳጆቹን ማየት በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ሲወድቅ ምን የሚሰማው ይመስላኃል? ይህም ሆኖ ግን እግዚአብሔር በስራ ላይ ነበር።

ነጋዴዎቹ ግብጽ ሲደርሱ ዮሴፍን ከፈርያን ሹማምንት አንዱ ለነበረው ለዘበኞቹ አለቃ ለጲጥፋራ ሸጡት።ዮሴፍ በዚያ በባዕድ ምድር ጠንካራ ሰራተኛ ሆነ፤ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበርና የሚሰራው ሁሉ ተከናወነለት። ጲጥፋራም የዮሴፍን ችሎታና ስኬት በማየት በቤቱ፣ በእርሻውና ንብረቱ ሁሉ ላይ አስተዳደሪ አድርጎ ሾመው። ከዚህ የተነሳ እግዚአብሔር ጲጥፋራን እጅግ ባረከው (ዘፍጥረት 39፡1-6)። ዳሩ ግን የዮሴፍ መከራ ገና አላበቃም ነበር።

ዮሴፍ ጠንካራ፣ መልከ መልካም እና ስኬታማ ወጣት መሆኑ የጲጥፋራ ሚስት ዐይኗን እንድትጥልበት አደረገ። ክፉ ቅሌቷ የተገለጠው ዮሴፍን አፍ አውጥታ "አብረኸኝ ተኛ"እያለች በየቀኑ መጎትጎት ስትጀምር ነበር። ዮሴፍ ግን እግዚአብሔርን በመፍራትና ጲጥፋራን በማክበር የእርሷን አሳች የኃጢአት ግብዣ እምቢ በማለት ጸና።

በዚህም ዮሴፍ አላስፈላጊ ፈተና ውስጥ ላለመግባት ሲል በተቻለ መጠን ወደ እርሷ ዘንድ ሳይቀርብ ስራውን መስራት ቀጠለ። ነገር ግን አንድ ቀን ጲጥፋራም ሆነ ሰራተኞቹ ማንም ቤት ውስጥ ባልነበረበት ወቅት፣ ይህች ሴት ከዮሴፍ ጋር ለማመንዘር በድጋሚ ሞከረች። በዚህ ጊዜ የዮሴፍን ልብስ ጨምድዳ በመያዝ አምልጧት እንዳይሄድ በማድረግ መሻቷን ልትፈጽም ሞከረች። ዮሴፍ ግን በምላሹ የወሰደው እርምጃ እግዚአብሔርን ለመታዘዝና ጌታውን ለማክበር ስለነበረው ቁርጠኝነት ብዙ ይናገራል። ለጲጥፋራ ሚስት ጋር ለመከራከርም ሆነ ለማስረዳት አልሞከረም፣ ወይም ደግሞ ልብሱን እንድተለቅለት ለማሳመን ጊዜ አልወሰደም። በፍጹም! ይልቁኑ ዮሴፍ ከዚህ አደገኛ ወጥመድ ለማምለጥ ሸሸ፤ ልብሱን ጥሎሏት ሸሸ! (ይህንን እርምጃ በ 1 ቆሮንቶስ 6፡18 ላይ ከተሰጠው "ከዝሙት ሽሹ" የሚል ትዕዛዝ ጋር አነጻጽሩ።) በአንጻሩ ዮሴፍ ግብዣዋን ውድቅ ማድረጉ የጲፋራን ሚስት በእጅጉ አበሳጫት። ከዚህም የተነሳ በንዴት በውጭ የነበሩትን አገልጋዮች በመጥራት ዮሴፍ ሊደፍራት እንደሞከረ አድርጋ ከሰሰችው። በመቀጠል ጲጥፋራ ወደ ቤቱ ሲመለስ ይህንኑ ክስ ደገመችለት። ጲጥፋራም የውሸት ክሷን በመቀበል ዮሴፍን ወደ ወህኒ ወረወረው (ዘፍጥረት 39፡6-20)።

ምንም እንኳ ዮሴፍ በወህኒ ቢጣልም፣ እግዚአብሔር አልጣውም ነበር፤ ብቻውንም አልተወውም ነበር። ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር የወህኒው አዛዥ ለዮሴፍ ቸርነት እንዲያደርግለትና በመልካም እንዲይዘው አደረገው። ከዚያም ብዙም ሳይቆይ አዛዡ ዮሴፍን የእስረኞች አለቃ አደረገው። ልክ በጲጥፋራ ቤት እንደሆነው ሁሉ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከመሆኑ የተነሳ ዮሴፍ በስራው ሁሉ ስኬታማ ሆነ (ዘፍጥረት 39፡21-23)።

በርግጥ በዚህ ሁሉ ውስጥ ዮሴፍ መሪነትን ወይም አስተዳዳሪነትን እየተማረ ነበር። በመጀመሪያ ያዕቆብ በበግ ጥበቃ ላይ ስለ ነበሩት ወንድሞቹ የማጣራት ኃላፊነት ከያዕቆብ ተሰጦት ነበር። በመቀጠል የጲጥፋራን ቤት እንዲያስተዳደር ተሹሞ ነበር፤ ይህንም በብቃት ፈጽሞ ነበር። ከዚያም በወህኒ ቤት ውስጥ የእስረኞች አስተዳዳሪ ሆኖ ተመርጦ ነበር። ቀጥሎስ ዮሴፍ ምን እንዲያስዳድር እግዚአብሔር የፈለገ ይመስላችኋል? የኃላፊነት ቦታው ምንም ይሁን ምን እግዚአብሔር አሁንም ከዮሴፍ ጋር በአብሮነቱ ይቀጥላል? እግዚአብሔር በዮሴፍ ህይወት ውስጥ ያለፉትን መልካም ሆነ ክፉ ነገሮች ሁሉ ለበጎ የሚያውላቸው ይመስላችኋል?

የዮሴፍ መክበር

አንድ ቀን ፈርያን በመጠጥ አሳላፊውና እንጀራ ቤት ኃላፊው ላይ ስለተቆጣ ሁለቱንም ዮሴፍ ታስሮ ወደ ሚገኝበት ወህኒ ወረወራቸው። በዚያም የተወሰነ ጊዜ ከቆዩ በኋላ አንድ ሌሊት ሁለቱም የሚያስጨንቅ ህልም አለሙ። በማግስቱ ጠዋት ሁለቱም በሃዘን ነበር ከመኝታቸው የተነሱት፤ ምክንያቱም ያዩትን ህልም ፍች መረዳት አልቻሉም ነበርና። ሁኔታቸውን የተመለከተው ዮሴፍ ግን እንዲህ ሲል ጠየቃቸው "ሁልጊዜስ ቢሆን የሕልም ትርጓሜ ከእግዚአብሔር *(ኤሎሂም)* የሚገኝ አይደለምን? እስቲ ያያችሁትን ሕልም ንገሩኝ"። ዮሴፍ የእያንዳንዳቸውን ህልም ከሰማ በኋላ በሶስት ቀን ውስጥ ፈርኦን መጠጥ አሳላፊውን ወደ ስራው እንደሚመልሰውና በአንጻሩ እንጀራ ቤቱን ግን በስቅላት እንደሚገድለው በመንገር ህልማቸውን ፈታላቸው። ቀጥሎም ዮሴፍ ለመጠጥ አሳላፊው እንዴት ያለ ጥፋቱ በእስር ላይ እንደሚገኝ በመንገር ይህንን ለፈርኦን በማስረዳት ከእስር እንዲያስፈታው ተማጸነው። ቀጥሎም ልክ እግዚአብሔር ለዮሴፍ እንዳስረዳው መጠጥ

አሳላፊው ወደ ነበረበት ኃላፊነት ሲመለስ፣ እንጀራ ቤቱ ግን በስቅላት ሞተ። ዳሩ ግን መጠጥ አሳላፊው ከወህኒ ሲውጣ ዮሴፍን ረሳው (ዘፍጥረት 40፡1-23)።

ከሁለት አመታት በኋላ ፈርዖን ሁለት የሚረብሹ ህልሞችን አለመ። በመጀመሪያው ህልሙ መልካቸው ያማረ፣ ሥጋቸው የወፈረ ሰባት ላሞች ከአባይ ወንዝ ሲወጡ አየ። በመቀጠል ሰባት እጅግ የከሱ ላሞች ሲወጡና እነዚያን የወፈሩትን ላሞች ሲበሏቸው አየ። በሁለተኛው ህልሙ ደግሞ ሰባት ፍሬያቸው የተንዠረገገና ያማሩ ዛላዎች በአንድ የእህል አገዳ ላይ ሲበቅሉ አየ። ቀጥሎ ሰባት የቀጨጩ ዛላዎች ወጥተው እነዚያን የተንዠረገጉ ዛላዎች ሲውጧቸው ተመለከተ። ፈርዖን ጢባበኑንና ለአስማተኞቹን አስጠርቶ ያየውን ህልም ቢነግራቸውም አንዳቸውም የህልሙን ፍች ሊነግሩት አልቻሉም።ከዚያም የመጠጥ አሳላፊው ከሁለት አመት በፊት እርሱና የእንጀራ ቤት ኃላፊው ያዩትን ህልም እንዴት ዮሴፍ በትክክል እንደተረጎመላቸው በማስታወስ ይህንኑ ለፈርዖን ነገረው። ስለዚህ ፈርዖን ዮሴፍን ከወህኒ በማስመጣት እንዲህ አለው፤ “አንተ ግን ሕልም ሲነገርህ የመተርጐም ችሎታ እንዳለህ ሰማሁ”። ዮሴፍ ግን እንዲህ ሲል መለሰለት፣ “እኔ የመተርጐም ችሎታ የለኝም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር *(ኤሎሂም)* ለፈርዖን የሚሻውን ትርጉም ይሰጠዋል”። ፈርዖን ህልሙን ከነገረው በኋላ ዮሴፍ ፍችውን አስረዳው፤ ፍችውም እግዚብሔር አስቀድሞ ሰባት የጥጋብ አመታት እንደሚያመጣና ቀጥሎ ግብጽን የሚያጠፋ ሰባት የርሃብ አመታት እንደሚያመጣ ነው። በዚህም እግዚአብሔር ለዮሴፍ ግብጽን የሚያድንበትን እቅድ ገለጠለት። በመቀጠልም ፈርዖን ጥበበኛና አስተዋይ ሰው እንዲመድብና ይህም ሰው በስሩ ከሚመደቡ ሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን በሚመጡት የጥጋብ አመታት እህል በብዛት እንዲያከማች፣ ቀጥለው በሚመጡት የርሃብ አመታት ደግሞ የተካማቸውን እህል በጥንቃቄ እንዲያከፋፈል ዮሴፍ ምክር ሰጠ። ፈርዖን ዮሴፍ በሰጠው ምክር በመደነቅ በቀጥታ ይህን እቅድ እንዲያከናውን ራሱን ዮሴፍን ሾመው። በዚህም ፈርዖን ዮሴፍን በ30 ዓመቱ የግዛቱ ምክትል ገዥ አደረገው፤ እንዲህ በማለት፡- “በመላዪቱ የግብፅ ምድር ላይ ኀላፊ አድርጌሃለሁ”። . . . “እኔ ፈርዖን ነኝ፤ ሆኖም በመላዪቱ ግብፅ ያላንተ ትእዛዝ እጁንም ሆነ እግሩን ልውስ የሚያደርግ አይኖርም”። (ዘፍጥረት 41፡1-46)

በሰባቱ የጥጋብ አመታት ዮሴፍ እጅግ ብዙ እህል ስለሰበሰበ፣ በግብጽ ከተሞች የእህል ማከማቻዎች ለረሃብ ጊዜ በሚሆን በቂ ምርት ተሞልተው ነበር። ነገር ግን በከነዓን ያዕቆብና አስራ አንድ ልጆቹ የነበራቸው ምግብ በፍጥነት እያለቀ በመምጣቱ ከረሃብ ጋር ተፋጠው ነበር። ያዕቆብ ቤተሰቡን ለማዳን ቢንያምን ከእርሱ ጋር በማስቀረት አስሩን ታላላቅ ልጆቹን ምግብ እንዲገዙ ወደ ግብጽ ላካቸው። ይህ የሆነው ዮሴፍን ወንድሞቹ ለባርነት ከሸጡት ከ20 ዓመታት በኋላ ነው። በርግጥ እነርሱም ዮሴፍን ድጋሚ በህይወት እናየዋለን ብለው በጭራሽ አያስቡም ነበር። ሆኖም ግን ልክ ግብጽ ሲደርሱ፣ የምድሪቱ ገዥና የእህል ሽያጭ አዛዥ በሆነው ባለስልጣን ወንድማቸው ፊት ነበር የቆሙት። ከዚህ የተነሳ በመሬት ላይ ለጥ ብለው በመስገድ እጅ ነሱት። እነርሱ ማን እንደሆነ ባይለዩትም ዮሴፍ ግን አውቋቸው ነበር (ዘፍጥረት 41፡53 – 42፡8)።

ዮሴፍ ትክክለኛ ማንነቱ በመሰወር የወንድሞቹ ጠባይ ተለውጦ እንደሆነ ሊፈትናቸው ወሰነ። ስለዚህም ዮሴፍ አስተርጓሚ በመጠቀም ወንድሞቹን በቁጣ ቃል ተናገራቸው፤ ግብጽን ለመሰለል የመጡ ሰላዮች እንደሆኑ በመክሰስም አስፈራራቸው።ወንድሞቹም ይህን ግብጻዊ አገረ ገዥ ሰላዪች እንዳልሆኑ ለማሳመን ሲሉ በቤት ትተዋቸው ስለመጡት አዛውንት አባታቸውና ታናሽ ወንድማቸው ነገሩት። ቢሆንም ግን ዮሱፍ ለሶስት ቀን በወህኒ እንዲቆዩ አዘዘ። ከዚያም ይህ አገረ ገዥ ስምዖንን ብቻ በማስቀረት ዘጠኙን ከወህኒ በማውጣት ለጊዜው ርሃባቸውን ሊያስታግስ የሚችል እህል አስይዞ ወደ ከነዓን ላካቸው። ነገር ግን ታማኝነታቸውን ለማስመስከርና

ስምዖንም እንዲፈታላቸው ከፈለጉ ታናሽ ወንድማቸውን ይዘው ወደ ግብጽ መመለስ እንዳለባቸው ነገራቸው። ልክ የቢንያም ስም ሲነሳ ወንድሞቹ እርስ በርስ እንዲህ ተባባሉ፡- “ይኸው በወንድማችን ላይ ባደረስነው በደል ምክንያት ቅጣታችንን እየተቀበልን ነው። እርሱ እንደዚያ ተጨንቆ ስለ ሕይወቱ ሲማጠነን፣ እኛ አልሰማነውም ነበር፤ ይህ መከራ የደረሰብንም በዚሁ ምክንያት ነው”። ሮቤልም መልሶ “በዚህ ልጅ ላይ፣ ‘ክፉ ነገር አታድርጉ’ ብዬ አልነበረምን? እናንተ ግን አልሰማችሁኝም፤ ስለዚህም ደሙ ከእጃችን ይፈለጋል” አላቸው። አዛዡ እርስ በርስ እየተናገገሩ ያሉትን የሚሰማ አልመሰላቸውም ነበር፤ ዮሴፍ ግን እያንዳንዷን ቃል በትክክል ያዳምጥ ነበር (ዘፍጥረት 42፡7-24)።

ወደ ከነዓን ከተመለሱ በኋላ ከግብጽ ያመጡት እህል በቶሎ አለቀ። ስለዚህ ያዕቆብ ብር በመያዝ ተጨማሪ እህል ለመሸምቱ ወደ ግብጽ እንዲውርዱ ጠያቃቸው። በመጀመሪያ ብንያምን ከእነርሱ ጋር ለመላክ አልፈለገም፤ ምክንያቱም ከ20 ዓመት በፊት ዮሴፍን በማጣት የደረሰበትን ሀዘን አይዘነጋውም። አሁን ደግሞ ስሞዖንን እስከወዲያኛው ሊያጣው ነው። ከብዙ ጭንቀት በኋላ ይሁዳ ለብንያም ደህንነት ሙሉ ሀኃላፊነቱን እንደሚወስድ ካስረገጠለት በኋላ የመጨረሻ ልጁም ከእነርሱ ጋር ለመላክ ተስማማ (ዘፍጥረት 42፡36 - 43፡14) ።

ከዚያም ወንድማማቾቹ በድጋሚ ወደ ግብጽ በመውረድ ብንያምን በአገረ ገዥው ፊት አቀረቡት። ዮሴፍም በቀጥታ የፈለጉትን እህል ከመስጠት ይልቅ ወንድማማቾቹን ለራት ግብዣ ወደ ራሱ ቤቱ ላካቸው። ይህ ልዩ እንክብካቤ ግን አንዳች የተለየ ነገር መኖሩን እንዲጠረጥሩ አድርጓቸዋል። በመቀጠልም ዮሴፍ ስምዖንን ከወህኒ በማውጣት ወደ እነርሱ እንዲመጣ አደረገ። ከዚያም ዮሴፍም ወደ ቤት ሲመጣ፣ ወንድማማቾቹ ለጥ ብለው በመስገድ እጅ ነሱ። ቀጥሎም ዮሴፍ ከታላቁ ሮቤል ጀምሮ አስከ ታናሹ ብንያም ድረስ ሁሉንም እንደየ እድሜያቸው በማዕድ ዙሪያ በቅደም ተከተል አስቀመጣቸው። ዮሴፍ ይህን ያለ እነርሱ እርዳታ ማድረጉ ወንድሞቹን በእጅጉ አስገርሟቸዋል። እንዴት ይህ አገረ ገዥ የዕድሜ ቅደም ተከተላቸውን ሊያውቅ ቻለ? አገልጋዮቹ ምግብ ሲያስተናግዱ፣ ለብንያምን ከሌሎቹ ወንድሞቹ አምስት እጥፍ ድርሻ አቀረቡለት (ዘፍጥረት 43፡ 15-34)። ዮሴፍ ይህን ሲያደርግ ለብንያም የተደረገው ያለ መስተንግዶ በታላላቆቹ ላይ የቅናት ስሜት ይፈጥር እንደሆነ ለማየት ስለፈለገ ይሆናል። ነገር ግን ይህ ስሜት በእነርሱ ላይ አልተስተዋለም። ሆኖም ግን ዮሴፍ አንድ የመጨረሻ ፈተና አዘጋጅቶላቸው ነበር።

በማግስቱ ጠዋት አስራ አንዱ ወንድማማቾች በእህል የተሞሉ ስልቻዎቻቸውን በመያዝ ወደ ከነዓን ጉዞ ጀመሩ። ነገር ግን ዮሴፍ በእያንዳንዳቸው ስልቻ ውስጥ የእህሉን መግዣ ብር መልሶ እንዳስገባ አላወቁም ነበር። በተለይም ደግሞ ዮሴፍ የራሱን የብር ዋንጫ/ መጠጫ በታናሹ ብንያም ስልቻ ውስጥ አስገብቶት ነበር። ገና ብዙ ርቀው ሳይጓዙ ዮሴፍ የቤቱን አዛዥ ተከትሎ በመሄድ ገንዘብ እንደሰረቁ በመንገር እንዲከሳቸው ወደ እነርሱ ላከው። አዛዡ ይህን ሲላቸው ወንድማማቾቹ ክሱን በመቃወም ይህን ነገር ፈጽሞ እንዳላደረጉ ለማስረዳት ሞከሩ። ቀጥለውም የአገረ ገዥውን መጠጫ የወሰደ ሰው ቢኖር እንኳ ይህ ሰው ለዘላለም የአገረ ገዥው ባሪያ በመሆን በግብጽ እንደሚቀር በመሃላ አስረዱ። ከዚያም የብር መጠጫው በብንያም ስልቻ ውስጥ ሲገኝ ሁሉ በድንጋጤ ክው ብለው ቀሩ፤ በመሪር ሃዘንም ልብሳቸውን ቀደዱ። የቤቱ አዛዥም መልሶ ወደ ዮሴፍ ሲያመጣቸው፣ ሁሉም በአንድ ላይ በእግሩ ስር ወደቁ። ከዚያም ይሁዳ ወደ ፊት ቀርቦ፣ ነፍሱን በብንያም ነፍስ ምትክ ለማስያዝ እንዲህ ሲል ቃሉን ሰጠ፡-“ስለዚህም እኔ ባሪያህ በጌታዬ ዘንድ ባሪያ ሆኜ በብላቴናው [ብንያም] ፋንታ ልቀመጥ፤ ብላቴናውም ከወንድሞቹ ጋር ይውጣ።አለዚያም ብላቴናው ከእኔ ጋር ከሌለ ወደ አባቴ እንዴት እወጣለሁ? አባቴን የሚያገኘውን መከራ እንዳላይ” (ዘፍጥረት 41፡ 1-34)።

ዮሴፍ ይሁዳ ራሱን ስለ ወንድሙ መስዋዕት አድርጎ ለመስጠት ያሳየው ቆራጥነት ሲመለከት ስሜቱን መቆጣጠር አልቻለም ። ስለዚህም ዮሴፍ በቤት የነበሩትን ሌሎች ሰዎች ሁሉ ካስወጣ በኃላ እንዲህ ሲል በእምባ ጮኸ፡- "እኔ ዮሴፍ ነኝ!" ዮሴፍ ይህን ሲናገር የሰሙት ወንድሞቹ በድንጋጤ ክው ብለው ቀሩ። ከ20 ዓመት በፊት ዮሴፍ እንዲታደጉት ቢለምናቸውም እምቢ በማለት ከጉድጓድ አውጥተው ለእስማኤላውያን ነጋዴ የሸጡበትን የጭካኔ ተግባር ትዝ አላቸው። ዮሴፍ ግን በርህራሔ እንዲህ ሲል ተናገራቸው፡- "እስቲ ወደ እኔ ቀረብ በሉ" አላቸው፤ ወደ እርሱም በቀረቡ ጊዜ እንዲህ አለ፤ "ወደ ግብፅ የሸጣችሁኝ ወንድማችሁ እኔ ዮሴፍ ነኝ፤ አሁንም በመሸጣችሁ አትቈጩ፤ በራሳችሁም ዐትዘኑ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር *(ኤሎሂም)* ሕይወት ለማዳን ሲል ከእናንተ አስቀድሞ እኔን ወደዚህ ልኮኛል። በምድር ላይ ራብ ከገባ ይኸው ሁለት ዓመት ሆነ፤ ከዚህ በኋላም የማይታረስባቸውና ሰብል የማይሰበሰ ብባቸው አምስት ዓመታት ገና አሉ። 7ነገር ግን እግዚአብሔር *(ኤሎሂም)* ሕይወታችሁን በታላቅ ማዳን ለመታደግና ዘራችሁ ከምድር ላይ እንዳይጠፋ በማሰብ ከእናንተ አስቀድሞ ወደዚህ ላከኝ።"ስለዚህ አሁን ወደዚህ የላከኝ እግዚአብሔር *(ኤሎሂም)* እንጂ እናንተ አይደላችሁም፤ እርሱም ለፈርዖን እንደ አባት፣ በቤት ንብረቱ ላይ ጌታ፣ እንዲሁም በግብፅ ምድር ላይ ገዥ አደረገኝ" (ዘፍጥረት 45፡1-8)። ከዚህም ዮሴፍ ምን ያክል በእግዚአብሔር መግቦት ያምን እንደነበር ማስተዋል እንችላለን።

በጊዜው ተከስቶ የነበረው ርሃብ ገና ለ 5 ዓመታት የሚቀጥል ነበር። ስለዚህም ዮሴፍ አባቱን፣ ወንድሞቹን እና ቤተሰቦቻቸውን ለመጠበቅ ወደ ግብጽ በማስመጣት ከእርሱ ጋር እንዲኖሩ አደረገ። ከ 17 ዓመታት በኋላ ያዕቆብ ሞተ። ወንድሞቹም የአባታቸውን ሞት ተከትሎ ዮሴፍ በእነርሱ ላይ ለበቀል ሊነሳ ይችላል ብለው ስለፈሩ፣ በፊቱ በመደፋት እንዲህ ሲሉ ተማጸኑት፡- "እኛ የአንተ ባሮች ነን"።ዮሴፍ ግን እንዲህ ሲል መለሰላቸው፡- "አትፍሩ፤ እኔን በእግዚአብሔር *(ኤሎሂም)* ቦታ ማን አስቀመጠኝ? እናንተ እኔን ለመጉዳት አስባችሁ አድርጋችሁት ነበር፤ እግዚአብሔር *(ኤሎሂም)* ግን ዛሬ እንደሚታየው ሁሉ የብዙዎችን ሕይወት ለማዳን ለበጎ ነገር አዋለው። አሁንም ቢሆን አትፍሩ፤ ለእናንተና ለልጆቻችሁ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አደርግላችኋለሁ" (ዘፍ 50፡ 18-21)።

እግዚአብሔር በመግቦታዊ አሰራሩ በዮሴፍ እና በወንድሞቹ ህይወት ውስጥ የተከናወኑ ገሮችንና ድርጊቶችን ይቆጣጠር ነበር። እግዚአብሔር እጅግ የሚያሙ ክስተቶችንና ሁኔታዎችን በመጠቀም የእርሱን ዘላለማዊ ዕቅድ ፈጽሟል።ከዮሴፍ ህይወት የሚከተለውን ጠቃሚ ትምህርት እናገኛለን፡- እግዚአብሔር በታላቅ ቅድስናው፣ ጥበቡና ኃይሉ ቅዱሳኑንና እርምጃቸውን ይቆጣጠራል፤ በዚህም በህይወታቸው የሚሆነው ነገር ሁሉ ተያይዞ ለእነርሱ ለበጎ እንዲሰራ ያደርግላቸዋል። በእግዚአብሔር መግቦት መታመን ለክርስቲያን የዕለት ተዕለት ህይወት እንዴት ያለ ታላቅ መጽናናትን የሚሰጥ ነገር ነው!

የቃል ጥናት ጥያቄዎች

1. የዬሴፍ ወንድሞች በእርሱ ላይ የተቆጡት ለምንድን ነው?

በሁለት ምክንያቶች ነበር የተቆጡት፡ አንደኛ፣ አባታቸው ዮሴፍን ከእነርሱ ይልቅ አብልጦ ስለወደደው እና ዋጋው ውድ የሆነ ጌጠኛ ልብስ ስለሰጠው ነበር። ሁለተኛ፣ ዮሴፍ ቤተሰቡ በሙሉ ለእርሱ ወድቆ ሲሰግድ ያየውን ህልም ስለነገራቸው ነው።

2. ሁለቱን የዮሴፍ ህልሞች አብራራ

ዮሴፍና ወንድሞቹ በእርሻ ውስጥ ነዶ ያስሩ ነበር። ከዚያም የወንደሞቹ ነዶዎች ለዮሴፍ ነዶ ሰገዱ፤ ይህም እርሱ በእነርሱ ላይ አንድ ቀን ገሸ እንደሚሆን የሚያስረዳ ነበር።

ፀሃይ፣ ጨረቃ እና አስራ አንድ ከዋክብት ለዮሴፍ ሰገዱ፤ ይህም ወላጆቹና ወንድሞቹ ለእርሱ እንደሚግዱለት የሚያመለክት ነበር።

3. ዮሴፍ እነዚህን ህልሞች ሲያልም ዕድሜው በአማካይ 17 ገደማ ነበር። ማለም በራሱ ስህተት አይደለም። ዮሴፍ ህልሙን ለቤተሰቦቹ መንገሩ ስለ ባህርይው ምን ይናገራል?

የትምክህትና የኩራት ስሜት የተሰማው ይመስላል።

4. እግዚአብሔር ዮሴፍ ለባርነት እንዲሸጥ ለምን ፈቀደ?
እግዚአብሔር ዮሴፍ በግብጽ የቤተሰቦቹን ጨምሮ የብዙዎቹን ህይወት እንዲታደግ ወድዶ ነበር።

5. እግዚአብሔር ዮሴፍ ያለጥፋቱ ወህኒ እንዲወርድ ለምን ፈቀደ?
ምናልባትም እግዚአብሔር የሴፍን በእስር ቤት ቆይታው ትህትናንና ስለሌሎች ግድ መሰኘትን ሊያስተምረው ስለወደደ ይሆናል። ዮሴፍ ወህኒ መግባቱ በፈርዖን እይታ ውስጥ እንዲገባ እንዳደረገው ግልጽ ነው፤ ይህም በግብጽ ላይ ከፈርዖን በታች ሁለተኛው የበላይ አዛዥ እንዲሆን መንገድ ጠርጎለታል። በተጨማሪ ያዕቆብ 4፡10 እና 1 ጴጥ 5፡6 ይመልከቱ።

6. እግዚአብሔር ለመጠጥ አሳላፊውና የእንጀራ ቤቱ ህልም ትክክለኛውን ፍች ሰጥቷል፤ እውነትነቱም በተግባር ተረጋግጧል። ዮሴፍ ህልማቸውን ከፈታላቸው በኋላ እነዚህ አዛዦች ምን ሆኑ?

በሶስት ቀን ውስጥ፣ ፈርዖን መጠጥ አሳላፊውን ወደ ስልጣኑ ሲመልሰው፣ እንጀራ ቤቱን ግን በስቅላት ገደለው።

7. የፈርዖን ሁሉት ህልሞች ፍች ምን ነበር?

ሰባት የጥጋብ አመታት እና ተከትለው የሚመጡ ሌላ ሰባት የርሃብ አመታት

8. እግዚአብሔር በዮሴፍ ህይወት ውስጥ ያለፉትን መጥፎ ነገሮች ሁሉ ለበጎ ያደረገለት በምን መንገድ ነው?

ምንም እንኳ በጊዜው ነገሮቹ እጅግ ፈታኝ ቢሆኑበትም፣ እግዚአብሔር በዮሴፍ ህይወት ውስጥ ያለፉ ደስ የማያሰኙ ክስተቶችን ተጠቅሞ ግብጽንና መላ ቤተሰቡን ሊመጣ ካለው ረሃብ የሚታደግ ሰው አድርጎ ዮሴፍን እያዘጋጀው ነበር።

9. ዮሴፍ ስለ ወንድሞቹ ያያቸው ህልሞች እውን የሆኑት እንዴት ነው?

የዮሴፍ ወንድሞች እህል ፍለጋ ወደ ግብጽ ሲመጡ በፊቱ ወድቀው ሰግደውለት ነበር።

10. ከዮሴፍ ህይወት ምን ትማራላችሁ?

እግዚአብሔር በአማኞች ህይወት ውስጥ የሚከናወኑ ነገሮችን ሁሉ እንደሚቆጣጠር፤ እንዲሁም ነገሮቹን ለአማኞች በረከትና ለእርሱ ክብር እንደሚያወላቸው እንማራለን።

በመጨረሻም ከእነዚህ መዝሙሮች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ መርጣችሁ ዘምሩ፣ አንዱን መዝሙር ደግሞ እንደ መዝጊያ ጸሎት በመጠቀም አጠናቁ።

1. “ህመምህን አሁን ለእርሱ አሰማ” / “Commit Now All Your Griefs”
2. “ትንሽ ድንቢጥ ስትወድቅ እግዚአብሔር ያያል” / “God Sees the Little Sparrow Fall”
3. “የእግዚአብሔር ህግጋት እንዴት በጎ ናቸው”/ “How Gentle God’s Commands”
4. “መከራው ቢንጠንም” / “Though Troubles Assail Us”

ክፍል 2
የእግዚአብሔር እቅድ ለዓለም

አባሪ

የታዳጊዎች መልመጃ

ምዕራፍ 1: እግዚአብሔር ሁሉን ነገር አቅዷል.....52
ምዕራፍ 2: እግዚአብሔር ሁሉን ፈጥሯል.....60
ምዕራፍ 3: እግዚአብሔር ሁሉን ይቆጣጠራል.....68

ክፍል ሁለት 2: የእግዚአብሔር እቅድ ለዓለም
ምዕራፍ 1: እግዚአብሔር ሁሉን አቅዷል

የእምነት መግለጫ

ጥያቄ፡ የእግዚአብሔር ድንጋጌዎች (the decrees of God) ምንድን ነው?

መልስ፡ የእግዚአብሔር ድንጋጌ ፡- በዘላለም እቅዱ፣ እንደ ፈቃዱ ምክር፣ ለእርሱ ክብር፣ የሚሆነውን ነገር ሁሉ አስቀድሞ ወስኗል የሚል ነው።

ጥያቄ፡ እግዚአብሔር አዋጁን/ምክሩን የሚፈጽመው እንዴት ነው

መልስ፡ እግዚአብሔር በመፍጠርና በመግቦት ተግባሩ አማካይነት አዋጁን ይፈጽማል

ቃላትን አጥርቶ መረዳት (Clear Terms)

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት መዝገበ ቃላት በመጠቀም የእያንዳንዳቸውን ትርጉም ጻፉ። ከዚያም የጻፋችሁትን ሳትመለከቱ ቃላቶችን በራሳችሁ መንገድ ለመተርጎም ሞክሩ። በመቀጠል ተመልሳችሁ የጻፋችሁትን ትርጉም አንብቡ፤ ከዚያም እንደገና በራሳችሁ ቃላት ግለጹተረ። ይህን ከሌላ ሰው ጋር በመሆን ተራ በተራ አድርጉ። በራሳችሁ በምትተረጉሙበት ጊዜ የተጻፈውን ራሱን ከሆነ እያላችሁ ያላችሁት፣ አንድ ጊዜ ሁሉንም ትርጉሞች አንብቡና ቀጥላችሁ ምንም ሳታዩ በራሳች ሁሉንም ተርጉሙ። ከዚያም የእምነት መግለጫ ጥያቄዎችንና መልሶችን ደጋግማችሁ በማንበብ በገባችሁ መጠን የእግዚአብሔርን አዋጅ በራሳችሁ ቃላት አስረዱ።

ድንጋጌዎች

ምክር

አስቀድሞ መወሰን

መፈጸም

መፍጠር

መግቦት

<u>በድጋሚ መጻፍ</u>

ሀሳቡን በተረዳችሁት መሰረት የእምነት መግለጫውን በድጋሚ በራሳችሁ አገላለጽ ጻፉ፣

ጥያቄ

መልስ

ጥያቄ

መልስ

<u>መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ</u>

እያንዳንዱ ጥቅስ ለየትኛው የእምነት መግለጫ ቃል/ ሀረግ መሰረት እንደሆነ ለዩ።

ኢዮብ 14፡5፤ “የሰው ዕድሜ አስቀድሞ የተወሰነ ነው፣ የወራቱንም ብዛት ወስነህ አስቀምጠሃል፤ ሊያልፈው የማይችለውንም ገደብ አኖርህለት።”

መዝሙር 33፡11፤ “የእግዚአብሔር ሐሳብ ግን ለዘላለም ይጸናል፤ የልቡም ሐሳብ ለትውልድ ሁሉ ነው።”

ምሳሌ 16፡9፤ “ሰው በልቡ መንገዱን ያቅዳል፤ እግዚአብሔር ግን ርምጃውን ይወስንለታል።”

ኢሳያስ 46፡10፤ “የመጨረሻውን ከመጀመሪያው፣ ገና የሚመጣውንም ከጥንቱ ተናግሬአለሁ፤ ‘ዐላማዬ የጸና ነው፤ ደስ የሚያሰኝኝንም ሁሉ አደርጋለሁ’ እላለሁ።”
ሐዋ 2፡23፤ “እግዚአብሔር በጥንት ውሳኔውና በቀደመው ዕውቀቱ ይህን ሰው አሳልፎ በእጃችሁ ሰጣችሁ፤ እናንተም በክፉ ሰዎች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት።”

ሮሜ 11፡34፤ ““የጌታን ልብ ያወቀ ማነው? አማካሪውስ የነበረ ማን ነው?””

ሮሜ 11፡36፤ “ሁሉም ከእርሱ፣ በእርሱ፣ ለእርሱ ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።”

ኤፌሶን 1፡4፤ “በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በእርሱ መርጦናልና። በፍቅር፣”

ኤፌሶን 1፡11፤ “ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሠራው እንደ እርሱ ዕቅድ አስቀድሞ የተወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል.”

ኤፌሶን 2፡10፤ “ምክንያቱም፣ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድንሠራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን።”

የጋራ የአንድነት ጊዜ እቅድ (Party Plan)

የአንድ ጓደኛችሁን ወይም የቤተሰባችሁ አባል የልደት፣ ምርቃት፣ የጋብቻ ዘመን፣ ወይም የጡረታ በዓል ለማክበር አቅዱ። (እንደአስፈላጊነቱ ከከተማ ወጣ ብላችሁ ልታከብሩት ትችላላችሁ።) የምትሰሯቸውን ስራዎችና ለመርሃ

ግብሩ አስፈላጊ የሆኑና መገዛት ያለባቸውን እቃዎች ለዩ ። የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ ልታስገቢቸው ትችላላችሁ።

በዝግጅቱ ላይ የሚጋበዙት እነማን ናቸው ? እንዴት ነው ሚጋበዙት?

የዝግጅቱ መሪ ሃሳብ ምንድን ነወ?

ምን አይነት የዝግጅት ማሳመሪያዎችን ትጠቀማላችሁ?

ምን አይነት ሪፍሬሽመንቶችን ታቀርባላችሁ?

ምን አይነት ጨዋታዎች ይኖራሉ?

ፕሮግራሙ ሚደረገው ውጭ ላይ ከሆነ ድንገት ዝናብ ቢመጣስ ምን አይነት አማራጭ ይኖራል?

ቦታውን በማስተካከልና ከፕሮግራም በኋላ የማጽዳት በመስራት የሚረዷችሁ ሰዎች አዘጋጅታችኋል?

እቅዳችሁን ወደ ተግባር ከመለወጣችሁ በፊት የምታማክሩት ሰው አለ?

በመቀጠል ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ስጡ፡-

1. እግዚአብሔር በራሱ መልክ ፈጥሯችኋል። ምንም እንኳ ኃጢአት ይህንን መልክ ቢያበላሸውም ፣ በብዙ ረገድ በአስተሳሰባችሁና በድርጊታችሁ ላይ የእርሱ መልክ ይታያል። (በክፍል 1፣ ምዕራፍ 1 ስለ ተበላሸው መልክ ያየነውን አስታውሱ።) የምታዘጋጁት የጋራ የአንድነት ፕሮግራም የእግዚአብሔርን መልክ በምን መንገድ ሊያንጸባርቅ ይችላል? ቀደም ሲል ያየናቸውን ሃሳቦች ለማስታወስ እንዲረዳችሁ የሚከተሉትን የእምነት አንቀጽ ጥያቄና መልሶች ተመልከቱ።

2. የምታዘጋጁት የአንድነት ፕሮግራም ዕቅድና አፈጻጸም ከእግዚአብሔር ዕቅድና አፈጻጸም በምን ይለያል?

3. ፕሮግራሙን ለማዘጋጀት ስታቅዱ ወይም ስትወስኑ ይህ ውሳኔያችሁ የራሳችሁ ውሳኔ ነው ወይስ የእግዚአብሔር ዕቅድ አንድ አካል ነው? ጥያቄውን ከመመለሳችሁ በፊት 2 ዜና 18፡ 19 ፣ 33 አንብቡ።

4. እንደዚህ አይነት ፕሮግራሞችን ስታቀዱና ስትፈጽሙ በምን መንገድ እግዚአብሔርን ልታከብሩ ትችላላችሁ?

<u>የእምነት መግለጫ ጥያቄዎች</u>

1. በእምነት መግለጫው መሰረት እግዚአብሔር ለምን እያንዳንዱን ነገር አስቀድሞ እንዳቀደ እና ይህም ፈጽም ዘንድ አስቀድሞ እንደወሰነ አስረዱ።

2. “እንደ ፈቃዱ ምክር” የሚለው ሃረግ ምንን ያመለክታል?

3. እግዚአብሔር “የሚሆነውን ነገር ሁሉ አስቀድሞ ስለ ወሰነ” ሰው ኃጢአት እንዲያደርግ አቅዶል ወይም እንዲፈጽመው ምክንያት ሆኗል ማለት እንችላለንን? በአጭሩ፣ እግዚአብሔር የኃጢአት ደራሲ/ ጠንሳሽ ነው?

4. እግዚአብሔር አዋጁን ወይም እቅዱን እንዴት ነው ሚፈጽመው?

5. እግዚአብሔ ሁሉን ነገር ፈጥሯል፤ ግን ደግሞ ሰውም ነገሮችን “ይፈጥራል”። የእግዚአብሔር አፈጣጠር ከሰው አፈጣጠር የሚለየው በምንድን ነው?

6. “መግቦት” ምንድን ነው?

የማሰላሰያ ጥቅሶች

ኤፌሶን 1፡4 ፣ 11፤ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ በእርሱ መርጦናልና። በፍቅር፣. . . ሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሠራው እንደ እርሱ ዕቅድ አስቀድሞ የተወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል፤

1. እግዚአብሔር እነማንን እንደሚያድን የወሰነው መቼ ነው?

2. የሰው ስራ ወይም ተግባር እግዚአብሔር ሰውን በማዳን ውሳኔው ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ ምንድን ነው?

3. “ቅዱሳን” ማለት ምን ማለት ነው?

4. “ነውር አልባ” ህይወት መኖር ማለት ምንም አይነት ታጢያት የሌለበት ህይወት መኖር ማለት ነው?

5. “ኢየሱስ ጌታ ነው፤ እግዚአብሔር ሁሉን ይቆጣጠራል” ማለት ምን ማለት ነው?

የቃል ትምህርት፤ እግዚአብሔር የሚሆነውን እያንዳንዱን ነገር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ወስኗል

1. ኢዮብ ምን አይነት ሰው ነበር?

2. ኢዮብ በየትኛው ዘመን ነበር የኖረው?

3. ሰይጣን በመጀመሪያው በኢዮብ ላይ ያመጣቸው ጥፋቶች ምን ምን ነበሩ?

4. ኢዮብ የነበረውን ሀብት ሁሉ፣ አገልጋዮችና ልጆች ሁሉ ሲያጣ ምላሹ ምን ነበር?

5. ቀጥሎ በኢዮብ ላይ የመጣው መከራ ምን ነበር?

6. ኢዮብ ሚስቱ እግዚአብሔርን ሰድቦ እንዲሞት መክራው ነበር፤ የእርሱ ምላሽስ ምን ነበር?

7. ሶስቱ የኢዮብ ጓደኞች ይህ መከራ በምን ምክንያት እንደደረሰበት አስበው ነበር?

8. የኢዮብን መከራ አስመልክቶ የነበራቸው የተሳሳተ አረዳድ ምን ነበር?

9. በታሪኩ ውስጥ ከተጠቀሱ የመፍጠር ስራዎች መካከል ቢያንስ ሁለቱን ጥቀሱ።

10. በታሪኩ ውስጥ ከተጠቀሱ የመግቦት ተግባራት መካከል ቢያንስ ሁለቱን ጥቀስ።

11. እግዚአብሔር ሶስቱን ሰዎች እንደነቀፈ ኤሊሁን ያልነቀፈው ለምንድን ነው?

12. በኢዮብ ህይወት ውስጥ የተከናወኑትን ነገሮች በበላይነት ይቆጣጠር የነበረው አካል ማን ነው?

13. እግዚአብሔር ይህ ሁሉ መዓት በኢዮብ ላይ እንዲወርድ ለምን ፈቀደ?

ክፍል 2: የእግዚአብሔር እቅድ ለዓለም
ምዕራፍ 2: እግዚአብሔር ሁሉን ፈጥሯል

<u>የእምነት መግለጫ</u>

ጥያቄ፡ የመፍጠር ስራ ምንድን ነው?

መልስ፡ የመፍጠር ስራ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በቃሉ ኃይል፣ በስድስት ቀን ውስጥ ካለመኖር ወደ መኖር

ያመጣበት እና ሀሉም መልካም ሆኖ የተበጀበት መለኮታዊ አሰራር ነው።

ጥያቄ፡ እግዚአብሔር ሰውን እንዴት ነው የፈጠረው?

መልስ፡ እግዚአብሔር ሰውን በመልኩና በምሳሌው ወንድና ሴት አድርጎ ፣ እውቀትን፣ ጽድቅንና ቅድስናን አካፍሎ

እንዲሁም የፍጥረት አስተዳዳሪ አድርጎ ፈጥሮታል።

ቃላትን አጥርቶ መረዳት (Clear Terms)

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት መዝገበ ቃላት ወይም ኢንተርኔት በመጠቀም የእያንዳንዳቸውን ትርጉም ጻፉ። ከዚያም የጻፋችሁትን ሳትመለከቱ ቃላቶችን በራሳችሁ መንገድ ለመተርጎም ሞክሩ። በመቀጠል ተመልሳችሁ የጻፋችሁትን ትርጉም አንብቡ፤ ከዚያም እንደገና በራሳችሁ ቃላት ግለጹተረ። ይህን ከሌላ ሰው ጋር በመሆን ተራ በተራ አድርጉ። በራሳችሁ በምትተረጉሙበት ጊዜ የተጻፈውን ራሱን ከሆነ እያላችሁ ያላችሁት፣ አንድ ጊዜ ሁሉንም ትርጉሞች አንብቡና ቀጥላችሁ ምንም ሳታዩ በራሳች ሁሉንም ተርጉሙ። ከዚያም የእምነት መግለጫ ጥያቄዎችንና መልሶችን ደጋግማችሁ በማንበብ በገባችሁ መጠን የመፍጠርን ስራ በራሳችሁ ቃላት አስረዱ።

ፍጥረት

መልክ

እውቀት

ጽድቅ

ቅድስና

መግዛት

<u>በድጋሚ መጻፍ</u>

በተረዳችሁት መሰረት የእምነት መግለጫውን በድጋሚ በራሳችሁ አገላለጽ ጻፉት፣

 ጥያቄ

መልስ

ጥያቄ

መልስ

<u>መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ</u>

እያንዳንዱ ጥቅስ ለየትኛው የእምነት መግለጫ ቃል/ሀረግ መሰረት እንደሆነ ለዩ።

ዘፍጥረት 1፡1፤ “በመጀመሪያ እግዚአብሔር *(ኤሎሂም)* ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ።”

ዘፍጥረት 1፡27-28፤ “ስለዚህ እግዚአብሔር *(ኤሎሂም)* ሰውን በራሱ መልክ ፈጠረው
በእግዚአብሔር *(ኤሎሂም)* መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።እግዚአብሔርም *(ኤሎሂም)*፣ “ብዙ ተባዙ፤ ምድርን ሙሏት፤ ግዟትም፤ የባሕርን ዓሦች፣ የሰማይን ወፎች፣ እንዲሁም በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሕያዋን ፍጡራንን ሁሉ ግዟቸው” ብሎ ባረካቸው።’”

ዘፍጥረት 1፡31፤ “እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፤ እነሆም፣ እጅግ መልካም ነበረ። መሸ፤ ነጋም፤ ስድስተኛ ቀን።”

ነህምያ 9:6፤ “አንተ ብቻ እግዚአብሔር ነህ። ሰማያትን፣ ከሰማያት በላይ ያሉትን ሰማያትና የከዋክብታቸውን ሰራዊት ሁሉ፣ ምድርንና በላይዋ ያለውን ሁሉ፣ ባሕሮችንና በውስጣቸው ያሉትንም ሁሉ ፈጥረሃል። ለሁሉም ሕይወትን ትሰጣለህ፤ የሰማይ ሰራዊትም ይሰግዱልሃል።”

ኢሳያስ 42:5፤ “ሰማያትን የፈጠረ፣ የዘረጋቸውም፣ ምድርንና በውስጧ ያሉትን ሁሉ ያበጀ፣ ለሕዝቧ እስትንፋስን፣ ለሚኖሩባትም ሕይወትን የሚሰጥ፣ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤”

ኤፌሶን 4:24፤ “እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንድትለብሱ ነው።”

ቆላስይስ 1:16-17፤ “ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፤ በሰማይና በምድር ያሉ፣ የሚታዩና የማይታዩ፣ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጎይላት፣ ገዦች ቢሆኑ ወይም ባለ ሥልጣናት፣ ሁሉም ነገር በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል። እርሱ ከሁሉ በፊት ነው፤ ሁሉም ነገር በአንድ ላይ ተያይዘ የጸናው በእርሱ ነው።”

ቆላስይስ 3:10፤ “የፈጣሪውን መልክ እንዲመስል በዕውቀት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችኋል፤”

ዕብራውያን 11:3፤ “ለማት በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተፈጠሩ በእምነት እንረዳለን፤ ስለዚህ የሚታየው ነገር የተፈጠረው ከሚታየው እንዳልሆነ እንገነዘባለን።”

ራዕይ 4:11፤ “ጌታችንና አምላካችን ሆይ፤ ክብርና ሞገስ፣ ኀይልም ልትቀበል ይገባሃል፤ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና፤ በፈቃድህም ተፈጥረዋልና፤ ሆነዋልምና።”

የእምነት መግለጫ ጥያቄዎች

1. የዚህን ምዕራፍ ለመጀመሪያው የእምነት መግለጫ ጥያቄ የተሰጠውን መልስ እና ዕብራውያን 11፡3 በማነጻጸር በእግዚአብሔር የእጅ ስራ ስራ እና በሰው የእጅ ስራ (ለምሳሌ፣ ቤት) መካከል ያለውን ልዩነት አስረዱ።

2. የእግዚአብሔር የእጅ ስራዎች ስለ እግዚአብሔር ምን ይናገራሉ?

3. የዚህን ምዕራፍ ለመጀመሪያው የእምነት መግለጫ ጥያቄ የተሰጠውን መልስ እና መዝሙር 33፡9 በማነጻጸር፣ በእግዚአብሔር የእጅ ስራ ስራ እና በሰው የእጅ ስራ መካከል ያለውን ልዩነት አስረዱ።

4. “በስድስት ቀናት ውስጥ” የሚለው ሃረግ ምን ያመለክታል?

5. ስለ ተጠናቀቀው የእግዚአብሔር ፍጥረት አስደናቂነት ምን ያክል ተረድተሃል ?

6. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደምናነበው፣ እግዚአብሔር ሰውን ለየት ባለ ትኩረት የፈጠረው ለምንድን ነው?

7. “ፍጡራን ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራቸው” የሚለው ሀረግ ምንን ያመለክታል?

8. በዘፍጥረት 2፡19-20 ላይ አዳም ለፍጥረታት ስም ሲያወጣላቸው እናያለን። ይህ አዳም ምን አይነት ችሎታን ከእግዚአብሔር እንደተካፈለ ያሳያል?

9. ዘፍጥረት 1፡27 ላይ "እግዚአብሔር *(ኤሎሂም)* ሰውን በራሱ መልክ ፈጠረው፤" ይላል። ይህ ምን ማለት ነው?

10. የሰው ልጅ አሁንም የእግዚአብሔርን መልክ የተሸከመ ነው?

11. በመክብብ 7፡29 መሰረት እግዚአብሔርን ሰውን እንዴት ነው የፈጠረው?

12. በዘፍጥረት 2፡23 አዳም ሄዋንን "ሴት" ብሎ የተጣራት ለምንድን ነው? በዘፍጥረት 3፡20 ላይስ "ሄዋን" ብሎ የጠራት ለምንድን ነው?

13. እግዚአብሔር ሁሉን እንደፈጠረ መገንዘብ ለምን ይጠቅማል?

የማሰላሰያ ጥቅስ

ዕብራውያን 11፡3፤ “ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተፈጠሩ በእምነት እንረዳለን፤ ስለዚህ የሚታየው ነገር የተፈጠረው ከሚታየው እንዳልሆነ እንገነዘባለን።”

1. እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ከምንም ነገር እንደፈጠረ / ካለመኖር ወደ መኖር እንዳመጣ ለመረዳት የግዴታ የሚያስፈልገን ነገር ምንድን ነው?

2. ይህ የማሰላሰያ ጥቅስ ከዝግመተ ለውጥ ጽንሰ ሃሳብ ጋር ይጋጫል?

3. መጽሐፍ ቅዱሳዊው የፍጥረት አስተምህሮ ከሳይንስ ጋር ይጋጫል?

የቃሉ ትምህርት፡ እግዚአብሔር ሁሉን ፈጥሯል

1. የዘፍጥረት መጽሐፍ የፍጥረት ታሪክ ስለ እግዚአብሔር ምን ይናገራል?

2. መንፈስ ቅዱስ በፍጥረት ስራ ላይ ተሳትፎ እንደነበረው እንዴት ልንረዳ እንችላለን? በዚህ ስራ ውስጥ የእርሱ ሚና ምን ሊሆን ይችላል?

3. እግዚአብሔር ወልድ በፍጥረት ስራ ውስጥ መሳተፉን በምን ልናውቅ እንችላለን?

4. በፍጥረት ሁለተኛ ቀን፣ ውሃን ከውሃ የሚለየውን ክፈተት ምን ብሎ ጠራው?

5. እግዚአብሔር ደረቅ መሬት (የብስ) እንዲወጣ ያደረገው እንዴት ነው?

6. እግዚአብሔር በአራተኛው ቀን ምን ፈጠረ?

7. የእነዚህ የሰማይ ፍጥረታት ተግባር ምንድን ነው?

8. እግዚአብሔር ሰውን በስንተኛው ቀን ነው የፈጠረው?

9. እግዚአብሔር በምን መንገድ ነው ሰውን ከእንስሳት ልዩ አድርጎ የፈጠረው?

10. እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ለምን አረፈ? የእናንተ ምላሽ ለዚህ ምን መሆን አለበት?

11. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ሁሉን ፈጣሪነት የሚያስተምረውን የማይቀበሉ ሰዎች የፍጥረትን አመጣጥ አስመልክቶ የሚያምኑት ምንድን ነው?

12. የዝግመተ ለውጥ አስተሳሰብ አራማጆች የሚከተሉትን ሁለት እውነታዎች ይክዳሉ፡- ሀ) እግዚአብሔር ከዘላለም በፊት ጀምሮ አለ፤ ለ) እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከምንም ነው የፈጠረው። እነዚህ ሃሳቦች ሳይንሳዊ ማረጋገጫ የሌላቸው ተራ የእምነት ጉዳዮች እንደሆኑ ይከራከራሉ። ለእንደዚህ አይነት አስተሳሰብ የእናንተ ምላሽ ምንድን ነው?

13. የዝግመተ ለውጥ አቀንቃኞች ምድር የብዙ ቢሊየን አመታት ዕድሜ ያላት እንደሆነች ያምናሉ፤ ይህን አቋማቸውንም በጂኦሎጂ ማስረጃዎች ለመደገፍ ይጥራሉ። በዝግመተ ለውጥ ጽንሰ ሃሳብ መሰረት የሚታዩ ነገሮች ሁሉ እጅግ ብዙ አመታትን በፈጀ ዝግመተ ለውጥ ነው አሁን ያለበት ደረጃ ላይ የደረሱት። በአንጻሩ ይህ አለም የተፈጠረ ነው ብሎ የሚያምን ሰው ይህን የዝግመተ ለውጥን ጥንታዊ ምድር አስተሳሰብ በምን መንገድ መቃወም ይችላል?

14. ቴስቲክ ዝግመተ ለውጥ (theistic evolution) ምንድን ነው?

15. ስለ ቴስቲክ ዝግመተ ለውጥ ሊኖራችሁ የሚገባው አመለካከት ምንድን ነው?

ክፍል 2: የእግዚአብሔር እቅድ ለዓለም

ምዕራፍ 3: እግዚአብሔር ሁሉን ይቆጣጠራል

<u>የእምነት መግለጫ</u>

ጥያቄ፡ የእግዚአብሔር የመግቦት ምንድን ነው

መልስ፡ የእግዚአብሔር የመግቦት ስራ፡- ፍጥረታትንና እንቅስቃሴያቸውን ሁሉ የሚጠብቅበትና የሚያስተዳድርበት እጅግ ቅዱስ፣ ጠቢብ እና ብርቱ የሆነ አሰራሩ ነው።

ጥያቄ. እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረበት ስፍራ ለአዳም የገለጠው ልዩ የመግቦት ስራ ምንድን ነው?

መልስ፡ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው ከእርሱ ጋር የሕይወት ኪዳን ገብቷል፤ ይህ ኪዳን በፍጹም መታዘዝ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ይኸውም መልካምና ክፉን ከምታስታውቀው የህይወት ዛፍ እንዳይበላ በመከልከል ነበር፤ ምክንያቱም ይህን ማድረግ ሞትን ያስከትል ነበርና።

ቃላትን አጥርቶ መረዳት

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት መዝገበ ቃላት ወይም ኢንተርኔት በመጠቀም የእያንዳንዳቸውን ትርጉም ጻፉ። ከዚያም የጻፋችሁትን ሳትመለከቱ ቃላቶችን በራሳችሁ መንገድ ለመተርጎም ሞክሩ። በመቀጠል ተመልሳችሁ የጻፋችሁትን ትርጉም አንብቡ፤ ከዚያም እንደገና በራሳችሁ ቃላት ግለጹተረ። ይህን ከሌላ ሰው ጋር በመሆን ተራ በተራ አድርጉ። በራሳችሁ በምትተረጉሙበት ጊዜ የተጻፈውን ራሱን ከሆነ እያላችሁ ያላችሁት፣ አንድ ጊዜ ሁሉንም ትርጉሞች አንብቡና ቀጥላችሁ ምንም ሳታዩ በራሳች ሁሉንም ተርጉሙ። ከዚያም የእምነት መግለጫ ጥያቄዎችንና መልሶችን ደጋግማችሁ በማንበብ በገባችሁ መጠን የመግቦትን ስራ በራሳችሁ ቃላት ግለጹ።

መግቦት

መጠበቅ

ማስተዳደር

ስፍራ

ኪዳን

<u>በድጋሚ መጻፍ</u>

በተረዳችሁት መሰረት የእምነት መግለጫውን በድጋሚ በራሳችሁ አገላለጽ ጻፉት፣

 ጥያቄ

መልስ

ጥያቄ

መልስ

<u>መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ</u>

እያንዳንዱ ጥቅስ ለየትኛው የእምነት መግለጫ ቃል/ሀረግ መሰረት እንደሆነ ለዩ።

ዘፍጥረት 2፡16-17፤ “እግዚአብሔር አምላክ ሰውን እንዲህ በማለት አዘዘው፤ “በአትክልት ስፍራው ውስጥ ከሚገኝ ከማንኛውም ዛፍ ፍሬ ትበላለህ። ነገር ግን መልካምና ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ አትብላ፤ ምክንያቱም ከእርሱ በበላህ ቀን በርግጥ ትሞታለህ።”

መዝሙር 3:15፤ “ዘመኔ ያለው በእጅህ ነው፤”

መዝሙር 46፡1፤ “አምላካችን መጠጊያችንና ኀይላችን፣ በሚደርስብን መከራ ሁሉ የቅርብ ረዳታችን ነው።”

መዝሙር 103፡19፤ “እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አጽንቶአል፤ መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች።”

ምሳሌ 8፡15፤ “ነገሥታት በእኔ [በጥበብ] ይነግሣሉ፤ ገዦችም ትክክል የሆነውን ሕግ ይደነግጋሉ፤”

ዳንኤል 2፡21፤ “[የሰማይ አምላክ] ነገሥታትን በዙፋን ያስቀምጣል፣ ደግሞም ያወርዳቸዋል፤”

ሆሴዕ 6፡7፤ “[እስራኤላውያን] እንደ አዳም ቃል ኪዳንን ተላለፉ፤ በዚያም ለእኔ ታማኝ አልነበሩም።”

ማቴዎስ 5፡45፤ “[የሰማዩ አባት] እርሱ ፀሓዩን ለክፉዎችና ለደጎች ያወጣል፤ ዝናቡንም ለጎጢአተኞችና ለጻድቃን ያዘንባል።”

ማቴዎስ 10፡29፤ “በአንድ ሳንቲም ከሚሸጡት ሁለት ድንቢጦች አንዲቷ እንኳ ያለ አባታችሁ ፈቃድ ምድር ላይ አትወድቅም።”

ቆላስይስ 1:17፤ “[ክርስቶስ]እርሱ ከሁሉ በፊት ነው፤ ሁሉም ነገር በአንድ ላይ ተያይዞ የጸናው በእርሱ ነው።”

ዕብራውያን 1፡3፤ “እርሱ የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራ ቅና የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ ሆኖ፣ በኀያል ቃሉ ሁሉን ደግፎ ይዞአል፤”

<u>የእምነት መግለጫ ጥያቄዎ ች</u>

1. “መግቦት” ማለት ምን ማለት ነው?

2. እግዚአብሔር መግቦቱን የሚገልጥባቸው ሁለት ተግባራት ምን ምን ናቸው?

3. የእግዚአብሔር የመግቦት ስራ ተደራሽ ማነው?

4. በርካታ ጊዜ እግዚአብሔር ለሙሴና ለእስራኤል በልዩ ሁኔታ መግቦቱን ገልጧል። ኢሳያስ 63፡11-14 ን በማንበብ የእግዚአብሔርን ልዩ ክብካቤና መለኮታዊ ጥበቃ ለማስተዋል ሞክር። እግዚአብሔር ህዝቡን በልዩ መንገድ "በመግቦት ስራው" የሚባርከው ለምንድን ነው?

5. እግዚአብሔር "ፍጥረታትንና እንቅስቃሴአቸውን" ሁሉ ይቆጣጠራል። በግልጽ መረዳት እንደሚቻለው ሰዎች የእግዚብሔርን ህግ ሲከተሉ መግቦቱ ያገኛቸዋል። ነገር ግን ሰዎች ጠማማ መንገድን ቢከተሉስ? እግዚአብሔር ክፉ ድርጊትን ይቆጣጠራል?

6. ኪዳን ምንድን ነው?

7. በጊዜው የነበረው "የህይወትኪዳን" ምንድን ነው?

8. አንዳንድ ክርስቲያኖች የህይወት ኪዳንን "የስራ ኪዳን" በማለት የሚገልጹት ለምንድን ነው?

የማሰላሰያ ጥቅስ

ሮሜ 8፡28፤ “እግዚአብሔር፣ ለሚወዱትና እንደ ሐሳቡ ለተጠሩት፣ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲሠራ እንደሚያደርግላቸው እናውቃለን።”

1. እግዚአብሔር በሁሉ በሰው ህይወት ውስጥ የሚከናወኑ ነገሮችን አያይዞ ለበጎ እንዲሰሩ ያደርግላቸዋል?

2. ሰዎች ልክ ኢየሱስን የህይወታቸው ጌታና አዳኝ አድርገው ሲቀበሉ እግዚአብሔር ከህይወታቸው ክፉ ነገሮችን በሙሉ ይከለክላል ?

3. ስለ ሁሉም ነገር በፍጹም ልብ በክርስቶስ ላይ መደገፍ ምን አይነት የኢኮኖሚ ችግር የሌለበት ህይወት እንድንመራ ያስችለናል?

4. እግዚአብሔር ደስ ከማያሰኙ ሁኔታዎቻችን ውስጥ ምን አይነት መልካም ነገር ያውጣ ይሆን ብሎ በጉጉት መጠባበቅ ችግር አለው? ለምሳሌ፣ ለህክምና ወደ ሃኪም የሄደን አንድን የካንሰር ታማሚ ክርስቲያን አስቡ። ይህ ክርስቲያን በካንሰር ህመሙ

ምክንያት ምን መልካም ነገር ሊያገኝ እንደሚችል ማሰላሰል ይኖርበታል?

የቃሉ ትምህርት: እግዚአብሔር ሁሉን ለበጎ ይሰራል

1. ዩሴፍ ወንድሞቹ በእርሱ ላይ የተቆጡት ለምንድን ነው?

2. ሁለቱን የዮሴፍ ህልሞች አብራራ

3. ዮሴፍ እነዚህን ህልሞች ሲያልም በአማካይ የ17 ዓመት ልጅ ነበር። ማለም በራሱ ስህተት አይደለም። ነገር ግን ዮሴፍ ህልሙን ሄዶ ለቤተሰቦቹ መናገሩ ስለ ባህርይው ምን ይናገራል?

4. ዮሴፍ ለባርነት እንዲሸጥ እግዚአብሔር ለምን ፈቀደ?

5. ዮሴፍ ያለጥፋቱ ወህኒ እንዲወርድ እግዚአብሔር ለምን ፈቀደ?

6. እግዚአብሔር ለመጠጥ አሳላፊውና የእንጀራ ቤቱ ህልም ትክክለኛውን ፍች ሰጥቷል፤ ይህም በተግባር ተረጋግጧል። ዮሴፍ ህልማቸውን ከፈታላቸው በኋላ እነዚህ አዛኞች ምን ሆኑ?

7. የፈርዖን ሁሉት ህልሞች ፍች ምን ነበር?

8. እግዚአብሔር በዮሴፍ ህይወት ውስጥ ያለፉትን መጥፎ ነገሮች ሁሉ ለበጎ ያዋለው እንዴት ነው?

9. ዮሴፍ ስለ ወንድሞቹ ያያቸው ህልሞች በምን መንገድ ነው የተፈጸሙት?

10. ከዮሴፍ ህይወት ምን ትማራላችሁ?

ማስታወሻ